አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

# አዲስ ልሳን

ቅጽ 32 ቁጥር 3593 | ቅዳሜ መስከረም 23 ቀን 2019 ዓ.ም | ዋጋው 10.00 ብር




# ለኢትዮጵያ መውጣት የጀመረው

## “የለውጥ ብርሃን በየትኛውም የክረምት ጨለማ፣ ዶፍና ጭቃ ተንሸራትቶ ሊደናቀፍ አይችልም”

**የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)**

**በቶለሳ መብራቴ**

ለኢትዮጵያ መውጣት የጀመረው የለውጥ ብርሃን በየትኛውም የክረምት ጨለማ፣ ዶፍና ጭቃ ተንሸራትቶ ሊደናቀፍ አይችልም ሲሉ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ተናገሩ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የ2019 ዓ.ም የኢሬቻ በዓልን በማስመልከት ባስተላለፉት መልዕክት፣ ለኢትዮጵያ መውጣት የጀመረው ይህ የለውጥ ብርሃን በየትኛውም የክረምት ጨለማ፣ ዶፍና ጭቃ ተንሸራትቶ ሊደናቀፍ አይችልም። ፈተናዎች ግን አሁንም ይኖራሉ። እነዚህ ፈተናዎች ግን ከኢትዮጵያና ህዝቦቿ አቅም በታች ናቸው ብለዋል።

**የመልዕክቱን ሙሉ ቃል እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡-**

እንኳን የክረምቱን አስቸጋሪ ወቅት በሰላም አሳልፋችሁ ለብሩሁ ብራ አደረሳችሁ። የክረምቱ ጨለማ አልፎ የብራዋ ጀንበር ስትወጣ ኦሮሞ

ወደ ገጽ 3 ዞሯል



ፎቶ- ከገፀ ድር

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የ2019 ዓ.ም የኢሬቻ በዓልን በማስመልከት የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት አስተላልፈዋል

## ከከተማ ውበት እስከ ዜጎች እፎይታ

4



ፎቶ- ከገፀ ድር

ከንቲባ አዳነች አቤቤ በ4ኛው ዙር የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ምስረታ ላይ መልዕክት ባስተላለፉበት ወቅት

## የባህል አልባሳቱ መታያ መድረክ

12



ፎቶ- ከገፀ ድር

በበዓሉ ከሚለበሱ አልባሳት መካከል ጥቂቶቹ

## የጽናት ተምሳሌትነት

24



ፎቶ- ከፋይል

አትሌት ትዕግስት አሰፋ በበርሊኑ የማራቶን ውድድር የደረሰባትን ጉዳት ተቋቁማ ድል ባስመዘገበችበት ወቅት

# የኢሬቻ በዓል

## “የሁላችን መድመቂያ፣ የመዲናችንን ጥልቅ የቱሪስት መስህብ፣ አቅምና ጸጋ ለዓለም የሚያንጸባርቅ ልዩ መድረክ ነው”

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ**



ፎቶ- ከገፀ ድር

ከንቲባ አዳነች አቤቤ የ2019 ዓ.ም የኢሬቻ በዓልን በማስመልከት የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት አስተላልፈዋል

**በቶለሳ መብራቴ**

የኢሬቻ በዓል የሁላችን መድመቂያ፣ ለመዲናችን ጥልቅ የቱሪስት መስብ፣ አቅምና ጸጋ፣ ለዓለም የሚያንጸባርቅ ልዩ መድረክ ነው ሲሉ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ ተናገሩ።

ከንቲባ አዳነች አቤቤ የ2019 ዓ.ም የኢሬቻ በዓልን አስመልክቶ ባስተላለፉት መልዕክት፣ ኢሬቻ የፈጣሪ ጸጋና ለጋስነት የሚመሰገንበት፣ ከተፈጥሮ ጋር ቃል ኪዳን የሚታደስበት፣ የሰላም፣ የፍቅር፣ የይቅርታና የአብሮነት በዓል ነው ብለዋል።

የኢሬቻ በዓል ልክ ከክረምቱ ጭጋግ ወደ ፈካውና በአደይ አበባ ወደአሸበረቀው መስከረም መሸጋገርን እንደሚያበስር ነው ያሉት ከንቲባ አዳነች፣ ከተማችን በኢሬቻ በዓል አሸብርቃ፣ ከምንጊዜውም በላይ ለቱሪዝም ዘርፍ ዕድገትና ለእንግዳ ተቀባይነት የተመቸች፣ የሰላምና የውበት መገለጫ ሆና በደስታ ኢኮኖሚዋን እያነቃቃችበት ነው ሲሉ አክለዋል።

ወደ ገጽ 3 ዞሯል




**አድራሻ** +251 111 112 218 +251 111 267 266 www.amn.gov.et 5 kilo infront of St. Mary Church Addis Ababa Ethiopia

# ርዕሰ አንቀፅ



## የአብሮነት እሴቶቻችንን እናጎልብታቸው!

ኢትዮጵያ በበርካታ ባህሎች፣ ቋንቋዎች እና ኃይማኖታዊ ሀብቶች የተዋበች፣ የብዝሃነት ውበት በድምቀት የሚታይባት ውብ ምድር ናት። የሀገራችን ህዝቦች ከትውልድ ትውልድ በተሻገሩ ማህበራዊ እሴቶቻቸው አማካኝነት አንድነታቸውን፣ ሰላማቸውን እና መተሳሰባቸውን ሲያጠናክሩ ኖረዋል። በእነዚህ የጋራ እሴቶች ውስጥ የሚንጸባረቀው ህብረ-ቀለማዊ ትስስር የሀገራችን ህልውናና የጸና ማህበራዊ መሰረት ነው። ለዚህ ማሳያ የሚሆኑን በአደባባይ በድምቀት የምንከውናቸውና ለአብነት ማንሳት የምንችላቸው እንደ መስቀል፣ ኢሬቻ እና ጥምቀት ያሉ በዓላት ናቸው። በእነዚህ ታላላቅ ክብረ በዓላት ላይ የሚታዩ ደማቅ ትዕይንቶች የኢትዮጵያን ህዝቦች የዘመናት አብሮነት፣ ፍቅር እና መከባበር በግልጽ የሚያሳዩ ህያው ምሳሌዎች ናቸው። ባህላዊ እና ኃይማኖታዊ በዓሎቻችን የጋራ መስተጋብራችንን በማጠናከር ረገድ ያላቸው ድርሻ እጅግ የላቀ ነው።

ዛሬ በአዲስ አበባ በድምቀት የሚከበረው የሆራ ፊንፊኔ እና ነገ በቢሾፍቱ የሚከበረው የሆራ ሀር-ሰዴ በዓል ለሀገራችን ሰላም፣ ዕድገት እና ማህበራዊ ትስስር እጅግ ጠቃሚ የሆኑ እሴቶችን የያዘ ነው። የኢሬቻ በዓል ከገዳ ሥርዓት ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያለው ሲሆን፣ በኦሮሞ ማኅበረሰብ ዘንድ ለዘመናት ሲከበር ቆይቷል። ኢሬቻ የምስጋና እና የሰላም በዓል ነው። የኦሮሞ ሕዝብ ምድር እና ሰማይን ለፈጠረው ፈጣሪው (ዋቃ) ምስጋናውን ለማድረስ እንዲሁም ከዘመን ወደ ዘመን በሰላም ላሸጋገረው አምላክ ውለታ ይህንን በዓል ያከብራል። ታሪክ አዋቂዎች እንደሚያብራሩት፣ ኢሬቻ ማለት ዋቃ የፈጠረውን ማመስገን ማለት ነው። በዚህ ዕለት ማህበራዊ ደረጃ እና የእድሜ ልዩነት ሳይፈጠር መላው ህዝብ በአንድነት በመሆን ምስጋናውን ያቀርባል።

በተጨማሪም ኢሬቻ የብርሃን በዓል ነው። ክረምት ለሊት ነው። ለሊት ደግሞ ጨለማ ነው። ጨለማው ሲነጋ ብርሃን ነው። ህዝቡ ከጨለማው የክረምት ወቅት ወጥቶ ወደ ብርሃኑ የመስከረም ወር መሸጋገሩን በደስታ ያበስራል። በክረምት ወራት ተራርቆ የቆየ ዘመድ አዝማድ በዚህ ዕለት ተገናኝቶ ፍቅሩን ያድሳል። በበዓሉ ላይ የሚታየው ሌላው ውብ እሴት ሰላም እና መዋደድ ነው። በተመሳሳይ የኢሬቻ በዓል ቀልብ የሚነጻበት፣ የተጣላ የሚታረቅበት እና ቂም የሚረሳበት ታላቅ የእርቅ ቀን ነው።

የኢሬቻ በዓል መልካ (በውሃ ዳርቻ) እና ቱሉ (በተራራማ ቦታ) በመባል በሁለት መልኩ ይከበራል። መልካ የምስጋና ሲሆን፣ ቱሉ ደግሞ በበጋው የፀሐይ ሀሩር ወቅት ወቅቱን ጠብቆ ዝናብ እንዲዘንብ ፈጣሪ የሚለመንበት ነው። ይህ ሁሉ ስነ-ሥርዓት ከሰው ልጆች ባለፈ ለተፈጥሮ እንክብካቤ እና ለህብረተሰቡ ሰላም ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጥ መሆኑን ያሳያል። በመሆኑም የአዲስ አበባ ነዋሪዎች እነዚህን የሀገር ጠቃሚ እሴቶች የጋራ ማድረግ እና ማጎልበት ይጠበቅብናል። የባህል እና የታሪክ ሀብቶቻችንን በመንከባከብ፣ ልዩነቶቻችንን በይቅርታና በፍቅር በማሸነፍ ሀገራችንን ወደ ላቀ አብሮነት፣ ሰላምና ብልጽግና ማሸጋገር እንችላለን።

ከበዓላት የምንወስደው ትልቁ ትርጉም እሴቱን ወደ ዕለት ተዕለት ኑሯችን ማስገባት ነው። የኢሬቻን ምስጋናና እርቅ እንደ የጋራ ኢትዮጵያዊ እሴት ማጎልበት ይገባናል። በዚህ መሰረት ዕርስ በዕርስ መከባበርን፣ መረዳዳትንና ልዩነታችንን እንደ ሀብት መቁጠርን እንማር። ከዚያም በላይ፣ ለልጆቻችን የምናስተላልፈው ትልቁ ቅርስ ከዚህ በዓል የተማርናቸው ሰላም፣ ፍቅር፣ ይቅርታ፣ መተሳሰብና አብሮነት ይሆናል። የአብሮነት እሴቶቻችንን እናጎልብታቸው፤ አዲስ አበባንም በእነዚህ እሴቶች የበለጠ የምትታወቅ የሰላምና የአብሮነት ከተማ እናድርጋት።

# የእኔ እይታ

**ይህ ገፅ ዜጎች በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሃሳባቸውን በነፃነት የሚያንፀባርቁበት ሲሆን ይህም የጋዜጣዋን የዝግጅት ክፍል አቋም አይገልፅም።**

## የአደባባይ በዓላትን የገቢ ምንጭ የማድረግ ጥረታችን እስከምን?

**በሳሌም ከአዲስ አበባ**

የብራዚሏ መዲና ሪዮ ዲ ጄኔሮ በህብረ ቀለማት ደምቃ የምታከብራቸው በርካታ የአደባባይ በዓላት አሏት፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ በአደባባይ በዓላት ብዛት በቀዳሚነትም ትጠቀሳለች። በተለይ የአደባባይ ካርኒቫሎች ሪዮን ለጎበኙ ሁሉ ሀሴትን ያጎናፅፋሉ፡፡ በሪዮ ጎዳናዎች ላይ ለአራት ቀናት በሚከበረው ካርኒቫል ላይ ለመታደም እስከ 2 ሚሊዮን የሚደርሱ ጎብኚዎች እንደሚገኙባት መረጃዎች ያመላክታሉ። በበዓሉ ላይ በሺህ የሚቆጠሩ ወጣት ዳንሰኞች የዳንስና የሙዚቃ ትዕይንት ያቀርባሉ። ብራዚላውያኑ ይህንን ፌስቲቫል ዋነኛ የገቢ ምንጫቸው አድርገው ይጠቀሙታል፡፡

በሪዮ ዲ ጄኔሮ የካቲት ወር ላይ በሚከወነው በዚህ ካርኒቫል ብቻ ከተማዋ ከምትሰበስበው 655 ሚሊዮን ዶላር ውጪ፣ ከአንድ ቢሊዮን ዶላር በላይ ገቢ የሚያስገኝ የንግድ ልውውጥ ይከወናል። እስከ 25 ሺህ የሚደርሱ ዜጎችም በዚሁ የንግድ ልውውጥ ውስጥ የስራ ዕድል ይፈጠርላቸዋል፡፡

እኛ ኢትዮጵያውያንስ የአደባባይ በዓላትን በምን ልክ የገቢ ምንጭ አድርገናቸዋል? የሚለው ጥያቄ መልስ ይሻል፡፡ በሀገራችን ከነሐሴ ጀምሮ እስከ ጥር ወር ድረስ በቁጥር የበረከቱ የአደባባይ በዓላት ይከበራሉ፡፡ እንደአሸንዳ፣ ሻደይ፣ ሶለል፣ ጎቤና ሸኖዬ፣ የመስቀል ዳመራ፣ ኢሬቻ፣ ፊቼ ጨንበላላ፣ ጥምቀት ያሉ የአደባባይ በዓላትን በቅጡ አስተዋውቀን የገቢ ምንጭ ልናደርጋቸው ይገባል የሚል አቋም አለኝ፡፡

የአደባባይ በዓላት የአንድን ሀገር ባህልና ማንነት ለዓለም ከማስተዋወቅ ባለፈ በቢሊዮን የሚቆጠር ዶላር የሚያስገኙ ታላላቅ የቱሪዝም እና የኢኮኖሚ ምንጮች ናቸው። ኢትዮጵያ በዩኔስኮ የተመዘገቡትን የመስቀል ደመራ፣ የጥምቀት፣ የፊቼ ጨምበላላ እንዲሁም የሸዋሮብ እና የኢድ አደባባይ በዓላትን ጨምሮ በርካታ ህዝባዊና ኃይማኖታዊ የአደባባይ ኩነቶች ያሏት ባለጸጋ ሀገር ናት። እነዚህ በዓላት በሚሊዮን የሚቆጠሩ የአገር ውስጥ ታዳሚዎችን በአንድ ማዕከል የመሰብሰብና ድንቅ ባህላዊ እሴቶችን የማሳየት አቅም አላቸው። ሆኖም ግን ሀገራችን ካሏት የባህልና የኃይማኖት በዓላት ብዛትና ስፋት አንፃር ሲመዘን፣ ከዘርፉ የምታገኘው ኢኮኖሚያዊ ጥቅም እጅግ አነስተኛና እምብዛም የሚያኮራ አይደለም። ይህ ክፍተት የሚመነጨው በዓላቱን ወደ ኢኮኖሚያዊ ሀብት ከመቀየር ይልቅ ለኃይማኖታዊና ባህላዊ ስነ-ስርዓቱ ብቻ ትኩረት ከመስጠት ነው።

ከእነዚህ ታላላቅ የአደባባይ በዓላት የሚገባትን ጥቅም ለማግኘት ሀገራችን የተቀናጀ የቱሪዝም እና የመሰረተ ልማት ስትራቴጂ መንደፍ ይኖርባታል። በመጀመሪያ ደረጃ በዓላቱን ማእከል ያደረገ ዓለም አቀፍ የማስተዋወቅ ስራ በሰፊው መስራትና የቅድመ-ጉዞ ፓኬጆችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል። ከዚህ በተጨማሪ የሆቴል፣ የትራንስፖርት እና የአየር መንገድ አገልግሎቶችን ከተለያዩ ሀገራት ለሚመጡ እንግዶች ምቹ፣ አስተማማኝና ጥራት ያላቸው ማድረግ ይገባል። ቱሪስቶች በበዓላቱ ወቅት መጥተው የሚመለሱ ብቻ ሳይሆኑ፣ የሀገር ውስጥ ምርቶችን የሚገዙበትና የሚገበያዩበት ሰፊ የንግድና የባህል ባዛሮችን ማደራጀት አስፈላጊ ነው።

ስለዚህ መንግሥትና የግሉ ዘርፎች ቅንጅት መጠናከር ለአደባባይ በዓላቱ በጀትና ዘመናዊ አደረጃጀት መስጠት ወሳኝ ነው። የደህንነት፣ የፅዳት እና የሞቀ የእንግዳ ተቀባይነት ባህል በማሳደግ የቱሪስቶችን ቆይታ ማራዘም ይቻላል። ኢትዮጵያ የተቀደሱና ማህበራዊ እሴቶቿን እንደጠበቁ፣ እነዚህን የአደባባይ በዓላት ወደ ታላቅ የቱሪዝም ኢንዱስትሪ በመቀየር የውጭ ምንዛሬ እና የሥራ እድል ማበልጸጊያ ማድረግ አለባት።

**አድራሻ**
አምስት ኪሎ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት
በሚገኘው ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጎን
ስልክ ቁጥር 0111-574923
ፖ.ሣ.ቁ 27080 code 1000
ፋክስ - 559368
addislisan1985@gmail.com

**የገበያ አገልግሎት እና የማስታወቂያ ዝግጅት ዳይሬክቶሬት**
ስልክ 0111 - 112218

**አታሚ**
ሜጋ ማተሚያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር**
**አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ**

**እየተዘጋጀች ዘወትር ቅዳሜ ወደ አንባቢያን የምትደርሰው ይህች ጋዜጣ ግንቦት 1985 ዓ.ም ተመሰረተች**

**ግራፊክስ ዲዛይን**
እዮብ ተፈራ

**ሌይአውትና ዲዛይን**
ፍልሰታ አየለ
መና ዮሐንስ

**የእርምት ባለሙያ**
ቸርነት ዋለልኝ
ገነት መላኩ

**የዕለቱ አዘጋጆች**
ፋንታነሽ ተፈራ
ሸዋርካብሽ ቦጋለ
አብርሃም ገብሬ

**ዋና አዘጋጅ**
ተካልኝ አማረ
Tekalignteke123@gmail.com
አድራሻ ለሚ ኩራ ክ/ከተማ
ወረዳ 3 የቤት ቁጥር B91/17

**ም/ዋና አዘጋጅ**
ሰውነት ኃ/ጊዮርጊስ
መለስ ተሰጋ

**ከፍተኛ አርታኢያን**
ደረጀ ታደሰ
ጊዜው አማረ
ስንታየሁ ምትኩ
ሳህሉ ብርሃኑ
ቶለሳ መብራቴ

## ለኢትዮጵያ... ከገጽ 1 የዞረ



ፎቶ- ከገፀ ድር

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የ2019 ዓ.ም የኢሬቻ በዓልን በማስመልከት የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት አስተላልፈዋል

በአንድነት ወጥቶ በባህሉ ስርዓት ወደ መልካ ይሄድና የክረምቱን ጨለማ ያሳለፈውን ፈጣሪውን ያመሰግናል። ለሚመጣውም ጊዜ ተስፋን ይሰንቃል። አባቶች “ማሬሆ” እናቶች ደግሞ “አራሮ” በማለት ለቸሩ አምላክ ምስጋና ያቀርባሉ። ወደ መልካው በመውረድም የምስጋና ስርዓቱን ያስጀምራሉ።

የክረምቱ ጨለማ በርካታ የማይመቹ ነገሮች አሉት። የሰውንና የእንስሳትን እንቅስቃሴ በመገደብ ያሰቡበት እንዳይደርሱ ያደርጋል። የክረምቱ ዶፍ ዝናብ፣ ጎርፉ፣ ጭቃውና አንሸራታቹ ድጥ ብራን በእጅጉ ተናፋቂ ያደርጋል። ለዘመናት የቆየው አብዛኛው የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ እድገት፣ የፖለቲካ ባህርይና አስተዳደርን ከክረምቱ አስቸጋሪ ወቅት ጋር ማመሳሰል እንችላለን።

ኢትዮጵያ ትልቅ ሀገር ሆና ሳለች የስሟን ያክል መሆን ሳትችል ቆይታለች። በርካታ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ሀብቶች እያሏት በዕውቀትና በስርዓት ስላልተመራ ብቻ ወደ ተጨባጭ አቅም መቀየር ባለመቻሏ የድህነት ተምሳሌትነት ሆና ስትጠቀስ ኖራለች። የረጅም ዘመናት ሀገረ መንግስትነት ቢኖራትም የህዝብን ችግር የሚፈታና ሀገርን የሚያሻግር ዘመናዊ አስተዳደር ለመገንባት ግን ስትቸገር ቆይታለች። ከራሷ አልፎ ዓለም አቀፍ ተጽዕኖ ማሳደር የሚችል መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ ቢኖራትም አልተጠቀመችበትም። ከዚህ የተነሳ በእህል ጎተራ ላይ ተቀምጣ የምትራብ፣ ውሃ እያላት የምትጠማና እያለው ያጣ ህዝብ ሆነን ኖረናል።

የክረምቱ ጨለማ ማለፉ የተፈጥሮ ህግ ነው። የክረምቱ ዝናብ ሲያልፍ በጎ ነገርም ትቶ ይሄዳል። የዝናቡ ውሃ መሬት ውስጥ ዘልቆ አፈሩን አርሶ አዝርዕት ያበቅላል፤ የተዘራውን ዘር አብቅሎ እንዲያፈራ ያደርጋል፤ የብራውን አበባ አፍክቶ ተስፋን ያለመልማል። የብራው አበባ መዓዛው ያውዳል፤ ቀለሙም ይማርካል፤ የተዘራው ሰብልም በብራ ወቅት ፍሬው ይሞላል፤ ለዚህ ነው ኦሮሞ ለብራ ትልቅ ስፍራ ያለው።

ህዝባችን በትግሉ ያመጣው ለውጥም ከብራ ጋር ይመሳሰላል። ለኢትዮጵያ የሰነቅነው የብራ ራዕይ፡ ጠንካራ አንድነት ላይ የተመሠረተች፣ ሉዓላዊነቷ የተከበረ፣ በስፋት የምታመርትና ማንኛውንም ዓይነት ፈተና የምትቋቋም ለአፍሪካ ግንባር ቀደም ተምሳሌት የሆነ ሀገር መገንባት ነው። ኢትዮጵያን ወደ ስልጣኔ የማሻገር ስትራቴጂያዊ እቅድ በተግባር ላይ እየዋለ ነው። በእቅዱ መሠረትም የለውጡ መንግስት የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ችግሮችን ወደ ዕድል እየቀየረ በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና በፖለቲካው መስክ ታላላቅ ውጤቶችን እያስመዘገበ ነው። የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ መጠናቀቅ፣ ሀገራዊ ምክክር በተሳካ ሁኔታ መከናወኑ፣ እንደ ማዳበሪያ ፋብሪካና የነዳጅ ፕሮጀክቶች እንዲሁም የቢሾፍቱ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ መጀመራቸው የስልጣኔ ጀንበር ለኢትዮጵያ ብቅ እያለች ለመሆኗ ጥቂት ማሳያዎች ናቸው።

የኦሮሞ ህዝብ ቋንቋውን፣ ባህሉንና እሴቱን ለማሳደግ ያነሣውን ጥያቄ ሙሉ በሙሉ ለመመለስ በባህል ልማት ረገድ የሆራ ፊንፊኔ ኢሬቻ ወደ መልካው ተመልሶ ስርዓት ውስጥ መግባቱ፤ የሆራ ሀርሰዴ ኢሬቻ ደግሞ በቢሾፍቱ ውበት ደምቆ ከፍ ብሎ መከበሩ ለዚህ ጥሩ ማሳያ ነው።

አሁን የምንገነባው ስልጣኔ በጥንታዊ እሴቶቻችን ላይ የተመሠረተ እንዲሆን በመደመር ፍልስፍና አቅደን ለጋራ እውቀት፣ የገዳና የሰፉ ትምህርት፣ ለጋራ ፍትሕ ባህላዊ ሸንጎዎችን አቋቁመን፣ ለጋራ ልማት የዜግነት አገልግሎትን ዘርግተን፣ ለጋራ ደህንነት ደግሞ የስርዓቱን ጠባቂዎች አደራጅተን ስርዓት እየገነባን እንገኛለን።

ለኢትዮጵያ መውጣት የጀመረው ይህ የለውጥ ብርሃን በየትኛውም የክረምት ጨለማ፣ ዶፍና ጭቃ ተንሸራትቶ ሊደናቀፍ አይችልም። ፈተናዎች ግን አሁንም ይኖራሉ። እነዚህ ፈተናዎች ግን ከኢትዮጵያና ህዝቦቿ አቅም በታች ናቸው፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ አሁን አንድነቱን አጠናክሮ፣ ወንድማማችነትን አስፋፍቶ በፍቅር በመደመር የኢትዮጵያን ስልጣኔ እውን ለማድረግ እየተባበረ ይገኛል። እኛም በህዝብ ድምፅ እንደተመረጠ መንግስት ከእሴታችን በፈለቀው የመደመር እሳቤ ላይ ተመስርተን የኢትዮጵያን ስልጣኔ ዕውን ለማድረግ ተግተን በመስራት ላይ እንገኛለን። የአድዋ አባቶቻችንን ጀግንነት በማስቀጠል ኢትዮጵያን ከጠላት እየጠበቅን ነን። እነርሱ ባሰመሩልን ድንበር ውስጥ እኩልነት፣ ሰላምና ብልፅግና እንዲረጋገጥ በፅናት እየሠራን እንገኛለን። የገዳ ስርዓት እሴትን መነሻ በማድረግ የሀሳብ ልዩነትን በመደማመጥ ለማስተካከል ሀገራዊ ውይይት አድርገናል።

በሌላ በኩል ደግሞ “እኔ ስጋ ብቻ ልብላ፤ እንስሳዬ ግን እንዳይነካ” የሚል ጠላትና ባንዳ ፊት ቆመን የሀገራችንን ጥቅም እናስከብራለን። መንገድ ስተው ከሀገራቸው በተቃራኒ ለቆሙ ወንድሞቻችን ያለን መልዕክት ኦሮሞ ‘ከሚያመሹበት የሚያድሩበት ቤት ይሻላል’ ብሎ እንደሚተርት አሁንም ፊታቸውን ወደ ሰላም ከመለሱ፤ የሰላም በር እንደተከፈተ ያለ መሆኑን ላረጋግጥላቸው እወዳለሁ።

ኦሮሞ በትግሉ ነፃ ወጥቷል። ከዚህ በኋላ በጠብመንጃ አፈሙዝና ከጠላት ጋራ በመወገን የሚመለስ የኦሮሞ ጥያቄ ፈፅሞ አይኖርም።

### የተከበርከው ህዝባችን ሆይ፣

የኢሬቻን በዓል ስናከብር እንደ እሴቱ አንድነትን አጥብቀን፣ እጃችንን ለሰላምና ለዕርቅ ዘርግተን፣ ቀልባችንን ወደ ይቅርታ መልሰን ስላገኘነው ነገር ፈጣሪን እያመሰገንንና እየተንከባከብን ያጣነውን ደግሞ በትዕግስት በመጠበቅ፤ ልክ ትናንት ኦሮሞ በአባቶቹ ደምና አጥንት ኢትዮጵያን እንደገነባ፣ ዛሬም የኢትዮጵያን ስልጣኔ ዕውን ለማድረግ ባለን ዕውቀት፣ አቅምና ሀብት ሁሉ ከሌሎች ወንድም የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ጋር በመሆን በግንባር ቀደምነት ኢትዮጵያን እንድናፀና ጥሪዬን አቀርባለሁ ብለዋል፡፡

## የኢሬቻ... ከገጽ 1 የዞረ

እንደ ከንቲባ አዳነች መልዕክት፣ “ኢሬቻ ለሀገራዊ መግባባት” በሚል መሪ ቃል የሚከበረው የዘንድሮው በዓል በድምቀትና ባማረ ድባብ እንዲከበር አዲስ አበባ የተለያዩ የስነ-ጥበብና የኪነ-ጥበብ ዝግጅቶችን፣ ኮንሰርቶችን፣ የፓናል ውይይቶችን፣ የስፖርት ውድድሮችን፣ ፌስቲቫሎችን፣ የፎቶ ኤግዚቢሽኖችን እና የመሳሰሉትን አዘጋጅታ በዓሉ በከፍተኛ ድምቀት እንዲከበር እየተደረገ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ፣ የከተማዋ ነዋሪዎች ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች እና ከውጭ ሀገር የሚመጡ ክቡራን እንግዶቻቸውን ለመቀበል ዝግጅታቸውን አጠናቅቀው በትብብርና በላቀ መስተንግዶ ላይ ይገኛሉ።

“የኢሬቻ በዓል በዓሉ የሁላችን መድመቂያ፣ ለመዲናችን ጥልቅ የቱሪስት መስብ፣ አቅምና ጸጋ፣ ለዓለም የሚያንጸባርቅ ልዩ መድረክ ነው”

ስለሆነም፣ ይህ የጋራ ኩራት የሆነው ድንቅ በዓል፣ መላው የከተማችን ነዋሪዎች ያካበቱትን የላቀ የእንግዳ ተቀባይነት ባህል በተግባር በማሳየት፣ ከየአካባቢው የሚመጡ ወገኖቻችንን በክብር በመቀበል፣ በፍቅር እና በከፍተኛ የአብሮነት ስሜት በድምቀት እንዲከበር ጥሪዬን በአክብሮት አቀርባለሁ ብለዋል።

# ከከተማ ውበት እስከ ዜጎች እፎይታ

**በቶለሳ መብራቴ**

አዲሱ የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ባሳለፍነው ረቡዕ መስከረም 20 ቀን 2019 ዓ.ም በይፋ ሥራ ጀምሯል። በመክፈቻው ሥነ-ሥርዓት ላይ የምክር ቤቱን አፈ ጉባኤ እና ምክትል አፈ ጉባኤ የመረጠ ሲሆን፣ በመቀጠልም ወይዘሮ አዳነች አቤቤን የከተማዋ ከንቲባ አድርጎ በሙሉ ድምፅ እንደገና መርጧቸዋል።



ፎቶ- ከገፀ ድር

ከንቲባ አዳነች አቤቤ በ4ኛው ዙር የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ምስረታ ላይ መልዕክት ባስተላለፉበት ወቅት

ከንቲባ አዳነች አቤቤ በዚሁ በ4ኛው ዙር የመንግሥት ምስረታ የመክፈቻ መርሃ-ግብር ላይ ባስተላለፉት መልዕክት፣ ከእንግዲህ ወዲያ የከተማዋ ልማትስኬት መለኪያ የፕሮጀክቶች ብዛት ሳይሆን በሰው ልጆች ሕይወት ላይ ያመጡት ተጨባጭ ለውጥ እንደሚሆን አፅንኦት ሰጥተው ተናግረዋል።

ባለፉት ጥቂት ዓመታት በአዲስ አበባ የታዩት ሰፊ የኮሪደር ልማቶች፣ የወንዝ ዳርቻ ፕሮጀክቶች እና በርካታ አረንጓዴ ፓርኮች የከተማዋን ገጽታ በመቀየር ረገድ ጉልህ ሚና ተጫውተዋል። እነዚህ ግዙፍ ፕሮጀክቶች የተከናወኑበት የ24/7 (ሳምንቱን በሙሉ ለ24 ሰዓታት) የሥራ ባህል ለውጥን በማምጣት ሲሆን፣ የአዲሱ መንግሥት ምስረታ ዋና ግብ ድግሞ ከዚያ የላቀ መሆን እንዳለበት ከንቲባ አዳነች ገልጸዋል። ይህም የመንግሥት ስኬት የሚለካው በተገነቡ ህንፃዎች እና በወረቀት ላይ በሚሰፈሩ ቁጥራዊ ሪፖርቶች ሳይሆን፣ በዜጎች የቀን ተቀን ሕይወት ላይ በሚታይ በእውነተኛ እና ዘላቂ ለውጥ መሆን አለበት የሚለው ጥልቅ መርህ ነው።

የዚህ ቃል ኪዳን ዋና አንድምታ በአንድ ከተማ ውስጥ በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ወጥቶባቸው የተገነቡ ፕሮጀክቶች ቢኖሩም፣ የዜጎችን የኑሮ ውድነት መቅረፍ፣ የሥራ አጥነትን ችግር ማቃለል ወይም አገልግሎት የመቀበል እንግልትን ማስቀረት ካልቻሉ የልማቱ ዋና ዓላማ አልተሳካም። ከንቲባዋ ያነሷቸው ነጥቦች በሙሉ የልማትን ትርጉም ከወረቀት ሪፖርት አውጥቶ የዜጎችን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ አስፈላጊ መሆኑን ያመለክታሉ። በመሆኑም ይህ አቅጣጫ ማንኛውም የልማት ፕሮጀክት ከመታቀዱና በጀቱ ከመፅደቁ በፊት "ይህ ፕሮጀክት በሰው ሕይወት ላይ ምን ያህል ተጨባጭ ለውጥ ያመጣል?" የሚለው ጥያቄ ቀዳሚውና ዋናው የፖሊሲ መለኪያ እንዲሆን የሚያስገድድ ነው።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ ልማት ጥናት መምህርና ተመራማሪ መሳይ ሙሉጌታ፣ ከዝግጅት ክፍላችን ጋር በነበራቸው ቆይታ እንደገለጹት፣ በብዙ አዳጊ አገራት የሚታየው የመንግሥት አሰራር ትልቁ ድክመት በወረቀት ሪፖርት እና በቁጥሮች ላይ ብቻ የተንተራሰ ስኬት ነው። የተገነቡ መንገዶች፣ የወጣ ቢሊዮን ገንዘብ ወይም የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች ብዛት በራሳቸው የሕዝብን የዕለት ተዕለት ሕይወት በቀጥታ ሊቀይሩ አይችሉም። ከንቲባ አዳነች አቤቤ ያሰመሩበት ዋና ነጥብ ይህንን አስተሳሰብ የመቀየር አስፈላጊነት ሲሆን፣ ይህም ልማትን ከቁጥር መለኪያ ወደ ሰው-ተኮር ውጤት ማሸጋገር ነው።

መምህር መሳይ እንደሚያስረዱት፣ ሰው-ተኮር ልማት ማለት የከተማዋ መሠረተ ልማቶች በዜጎች ጤና፣ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት፣ አካላዊ ደህንነት፣ ሥነ-ልቦናዊ እፎይታ እና ማኅበራዊ ትስስር ላይ የሚያመጡትን አዎንታዊ ለውጥ በቀጥታ መመዘንና ማረጋገጥ ማለት ነው።

በከተማዋ ውስጥ የሚታየው የኑሮ ውድነትና የዋጋ ንረት በዋናነት የሚጫነው እናቶችን በመሆኑ፣ ይህንን ጫና መቀነስ የሰው-ተኮር ልማት የመጀመሪያው እርምጃ እንደሆነ መምህሩ ጠቁመዋል። ይህንን ተጨባጭ ለውጥ ለማምጣት ከተማ አስተዳደሩ ባለፉት ዓመታት የጀመራቸውን የእሁድ ገበያዎች፣ የትምህርት ቤት ምግብ ፕሮግራሞችን፣ የዳቦ ፋብሪካዎች ግንባታ እንዲሁም የሕፃናት ማቆያ ማዕከላትን በስፋትና በጥራት ማስቀጠል ይኖርበታል። እናቶች የልጆቻቸውን የምግብና የደብተር ወጪ ሳያስቡ ወደ ትምህርት ቤት መላክ ሲችሉ እና የሕፃናት ማቆያ በማግኘታቸው ወደ ምርታማ ሥራ መሰማራት ሲችሉ፣ የተገባው ቃል በዕለታዊ ሕይወታቸው ላይ ትርጉም ያለው ለውጥ አምጥቷል ማለት ይቻላል።

በተጨማሪም ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ዜጎች የሚመገቡባቸው የምግብ ማዕከላት መስፋፋታቸው እና የአቅመ ደካሞች መኖሪያ ቤቶች መታደሳቸውና ዳግም መገንባታቸው ለነዋሪዎች ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ያጎናጽፋሉ። በተመሳሳይ መልኩ የኮሪደር ልማቶች ለአካል ጉዳተኞች፣ ለሕፃናት እና ለአረጋውያን ምቹ እንዲሆኑ ተደርገው መሰራታቸው የከተማዋን ተደራሽነት እና አሳታፊነት በተግባር ያረጋገጠ አካሄድ ነው።

ለወጣቶች የተገባው ቃልም የልማቱን ዘላቂነት እና የከተማዋን የነገ ተስፋ የሚወስን ነው። "አንድ ወጣት ምን ዓይነት ኑሮውን የሚያሻሽል ጥራት ያለው የሥራ ዕድል አገኘ?" የሚለው ጉዳይ በትኩረት እየታየና ምላሽ እያገኘ እንደሚሄድ የሚገልጸው የከንቲባ አዳነች ሀሳብ፣ ወጣቶችን በጊዜያዊና ዘላቂነት በሌላቸው ተግባራት ብቻ ከመወሰን አሰራር መውጣት እንዳለበት ይጠቁማል።

> " የከተማዋ ልማቶች ስኬት መለኪያ የዜጎችን የኑሮ ውድነት መቀነስ፣ ጥራት ያለው የሥራ ዕድል መፍጠር፣ ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት እና ሰብዓዊ ክብርን ማስጠበቅ ላይ ያተኮረ ይሆናል"

ጥራት ያለው የሥራ ዕድል ማለት የወጣቱን እውቀት፣ ክህሎትና የፈጠራ አቅም የሚያጎለብት፣ በቂ የሆነ ገቢ የሚያስገኝ እና የወደፊት ሕይወቱን በራሱ አቅም እንዲገነባ የሚያስችለው ነው። ይህንንእውንለማድረግየከተማአስተዳደሩ ወጣቶችን በኢንዱስትሪ፣ በቴክኖሎጂ፣ በዲጂታል ኤኮኖሚ፣ በፈጠራ ሥራዎችና በአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ውስጥ በስፋት የሚያሳትፉ መዋቅሮችን መዘርጋት አለበት። ወጣቶች የብድር አቅርቦት፣ የመስሪያና የመሸጫ ቦታዎችን በፍትሐዊነትና በግልፅነት ማግኘት ሲችሉና በገበያ ውስጥ ተወዳዳሪ የሚሆኑበትን አቅም ሲገነቡ ተጠቃሚነታቸውን ያረጋግጣል።

ከንቲባዋ ሌላው ያነሱት ወሳኝ ነጥብ የመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥ እና የዜጎች ሰብዓዊ ክብር ጉዳይ ነው። "አንድ ዜጋ የመንግሥት አገልግሎት ሳይንገላታ በክብር አገኘ ወይ?" የሚለው ጉዳይ በቂ ምላሽ በሚያገኝበት ልክ እንደሚሰራ የተናገሩት ከንቲባዋ ሥር የሰደደ የመልካም አስተዳደር ችግርን ለመፍታት በቁርጠኝነት የሚሰራ መሆኑን አመላካች ነው። በመንግሥት ቢሮዎች አካባቢ የሚታዩ የአገልግሎት መዘግየቶችንና ሙስናዎችን በማስወገድ ረገድ በብቃትና በችሎታ ላይ የተመሰረተ አሰራር ማስፈን ይገባል። አገልግሎትን በክብር መስጠት ማለት የአገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓቱን ዲጂታላይዝ ማድረግ፣ አሰራርን ማቃለል እና የአገልግሎት ሰጪዎችን የአስተሳሰብ ለውጥ ማምጣት ነው። ዜጎች የመንግሥት አገልግሎትን እንደ ችሮታ ሳይሆን እንደ መብታቸው በክብር ማግኘት ሲጀምሩ የመንግሥትና የሕዝብ ትስስር ይጠናከራል።

የመኖሪያ ቤት፣ የጤና፣ የውሃ እና የትራንስፖርት አገልግሎቶች ተዳራሽነትና ጥራት ጉዳይ የከተማዋን ሁለንተናዊ አኗኗር የሚያንፀባርቅ መሆኑን ከንቲባዋ በንግግራቸው አንስተዋል። መምህር መሳይ በበኩላቸው በከተማ ውስጥ መኖሪያ ቤት ማግኘት፣ ንፁህ የመጠጥ ውሃ፣ ቀልጣፋ የትራንስፖርት ተጠቃሚ መሆን እና ደረጃውን የጠበቀ የጤና አገልግሎት ማግኘት መሠረታዊ ሰብዓዊ መብቶች መሆናቸውን ጠቁመዋል።

የከተማ አስተዳደሩ የሚያካሂዳቸው የኮሪደር ልማትና የመልሶ ማልማት ሥራዎች ለዜጎች የተሻለ ንፁህ አካባቢ፣ ደረጃቸን የጠበቁ መኖሪያ ቤቶች እና የተደራጀ መሠረተ ልማቶች ማዕከል ማድረጉ ይበል የሚያሰኝ በመሆኑ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት ብለዋል።

እነዚህ ቃል የተገቡ እና የሰው-ተኮር ልማት እሳቤዎች በወረቀት ላይ ከተቀመጠ መልካም ምኞት አልፈው በምድር ላይ ተጨባጭ ውጤት ማምጣት የሚችሉት ጠንካራ መዋቅራዊና የአሰራር ማሻሻያዎች ሲኖሩ ብቻ ነው። የከተማ አስተዳደሩ አንድን ፕሮጀክት ከመጀመሩ በፊትና ከተጠናቀቀ በኋላ በዜጎች ሕይወት ላይ ያመጣውን ለውጥ በሳይንሳዊ መንገድ መገምገም እንዳለበት የማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ ምሁሩ አሳስበዋል።

ከንቲባ አዳነች አቤቤ ባስቀመጡት አቅጣጫ፣ አዲስ አበባን በህንፃና በመንገድ ውበት ብቻ ሳይሆን በማኅበራዊ ፍትህ፣ በሰብዓዊ ክብር እና በዜጎች ደስታ የጎለበተች ከተማ ለማድረግ የተያዘ ትልቅ ራዕይ ነው። ይህ ሰው-ተኮር የለውጥ አቅጣጫ በተግባር ሲተረጎም፣ አዲስ አበባ ለዜጎቿ ምቹ፣ ፍትሐዊ እና ሰብዓዊ ክብርን የምታስከብር የአፍሪካ መዲና የመሆን ራዕይዋን እውን ታደርጋለች።

# አሰባሳቢው የአደባባይ በዓል

- **በዓሉ በኢትዮጵያውያን መካከል የአንድነት፣ የወንድማማችነት፣ የትብብርና የመደጋገፍ ባህል እንዲዳብር የጎላ አስተዋፅኦ እንዳለው ተመላክቷል**

**በመለሰ ተሰጋ**

ኢሬቻ የምስጋና በዓል ነው፤ የተፈጥሮን በረከት ማሰቢያ፣ ለፈጣሪ ምስጋና ማቅረቢያ፣ ለሰላም መሻትና ለአብሮነት መሰባሰቢያ ነው፣ ኢሬቻ። የኦሮሞ ሕዝብ ባህላዊ ማንነት የሚገለጥበት ይህ በዓል፣ ዛሬ የባህል እሴትን ከማስተላለፍ ባሻገር ሰዎች የሚገናኙበት፣ የሚተዋወቁበትና የሚቀራረቡበት ሕያው አደባባይ ሆኗል። የኢሬቻ በዓል እየተከናወነ ያለበትን ስፍራ ሲመለከቱት ብዙ ታሪኮች ይታያሉ። በአልባሳቱ ቀለም ውስጥ ባህል ይናገራል፤ በዜማ ውስጥ የትውልድ ቅብብሎሽ ይታያል፤ በጭፈራው ውስጥ የማኅበረሰብ ስሜት ይገለጣል፤ በምስጋና ውስጥ ደግሞ የሰው ልብ ከተፈጥሮና ከፈጣሪ ጋር ያለው ግንኙነት ነፍስ ይዘራል።



በሆራ ፊንፊኔ የተከበረው የ2018 ዓ.ም የኢሬቻ በዓል ከፊል ገፅታ
ፎቶ- ከገፀ ድር

ኢሬቻ ላይ አንድ ሰው ብቻ አይመጣም፤ ይልቅ ቋንቋውን፣ አለባበሱን፣ ወግና ልማዱን፣ ፍቅሩንና ዘመድ አዝማዱን፣ አንድነቱን በጥቅሉ ቱባ ማንነቱን ይዞ በህብር ይመጣል እንጂ። ሁሉም በዚህ ልክና ከፍታ ሲመጣ አንዱ ካንዱ መልካም ነገሮችን ያያል፣ ይሰማል፣ ይጠይቃል፣ ይማራል። በዚህ ውስጥ የህዝቦች አብሮነት በፅኑ መሰረት ላይ ይቆማል፤ ከፍ ይላል። ይህ ደግሞ የኢሬቻ በዓል ሌላኛው ገፀ-በረከት ነው። በአዲስ አበባ አዲሱ ገበያ አካባቢ ነዋሪ የሆነው ወጣት ሰይድ እሸቱ የዛሬ ሁለት ዓመት በኦሮሞ ወንድሞቹ ግብዣ በሆራ ፊንፊኔ ኢሬቻ በዓል ላይ መሳተፍ መጀመሩን ከዝግጅት ክፍላችን ጋር በነበረው ቆይታ አጫውቶናል። ያኔ፣ በበዓሉ ያየው ደስታ፣ ሰላምና አንድነት ስለ ኢሬቻ ያለውን ግንዛቤ እንዳሳደገለትም ይናገራል።

ወጣቱ እንደሚለው አንድ ሰው በወዳጁ ተጋብዞ፣ “ና፣ በዓሌን እይ” መባል ትርጉሙ ከዕለት መጠራራት ያለፈ ነው። “ባህሌን እንድታውቅ፣ እኔም የአንተን እንድማር እንገናኝ” ማለት ነውና የበለጠ ወዳጅነትን፣ መተሳሰብንና አብሮነትን ማፅናት የሚያስችል ነው። በመሆኑም አንዳችን የሌላውን ባህልና ማንነት አብረን ስናከብር እንደ ሀገር ትስስራችን የበለጠ ይጎለብታል ይላል ወጣት ሰይድ። ኢሬቻ፣ እንዲህ ያሉ ትናንሽ ግንኙነቶችን ወደ ትልቅ የማኅበራዊ ትስስር ይለውጣል። በበዓሉ ድንገት የሚገናኙ ሰዎች ትውውቅ ይጀምራሉ። ስለ አለባበሳቸው፣ ስለ አመጋገባቸው፣ ስለ ጭፈራቸው እና መሰል ነገሮች እርስ በእርስ ይደናነቃሉ። ይህን መሰል ትውውቅና ግንኙነት ከበዓሉ በኋላም ወዙን ጠብቆ የሚቀጥልበት ዕድል አለ። ይህ እንዲሆን መስራት ደግሞ ከሁሉም ይጠበቃል። ለዚህም ነው የማህበራዊ ሳይንስ ምሁራን አንዳንድ በዓላት የአንድ ቀን ስብሰባ ብቻ ሳይሆኑ የረጅም ጊዜ ግንኙነት መነሻ ናቸው የሚሉት።

የፎክሎር ባለሙያው ግርማ ጃለታ (ዶ/ር) ባህል አንድ ማኅበረሰብ ማንነቱን፣ እሴቱን፣ አስተሳሰቡን፣ ደስታና ሀዘኑን በክዋኔ፣ በዜማ፣ በቁሳቁስና በሌሎች መንገዶች የሚገልጽበት መሣሪያ መሆኑን ያብራራሉ። ኢሬቻ ይህ ሀቅ በአደባባይ የሚታይበት ነው። ኢሬቻ የግል ስሜትን ወደ የጋራ መተሳሰብ የሚያሸጋግር ሥርዓትም አለው። ሰዎች በአንድ ቦታ ሲሰበሰቡ፣ በአንድ የምስጋና መንፈስ ሲሳተፉ፣ በጋራ ሲዘምሩና ሲደሰቱ ከግል ስሜት በላይ የሆነ የጋራ መተሳሰብ ይፈጠራል። በበዓሉ የተለያዩ ህዝቦች ከአራቱም ማዕዘን ይታደማሉ። ይህ እሴት በኢትዮጵያውያን መካከል የአንድነት፣ የወንድማማችነት፣ የትብብርና የመደጋገፍ ባህል እንዲዳብር ስለሚያደርግ የበለጠ መጠናከር እንዳለበት ግርማ (ዶ/ር) ገልፀዋል።

ኢሬቻ ሰዎች በእኩል መንፈስ የሚገናኙበት ሲሆን፣ የመከባበር እሴትም በተግባር ይገለጥበታል። በበዓሉ ላይ በሚደረጉ ክዋኔዎች ውስጥ ሕፃናት፣ አረጋውያን፣ ሴቶችና አካል ጉዳተኞች ልዩ ቦታና ክብር ይሰጣቸዋል። ይህም በማህበረሰቡ ዘንድ ያለውን ትስስር የበለጠ ያጎለብተዋል። ኢሬቻ የራስን ማንነት እያስጠበቀ ለሌሎች ማኅበረሰቦች የሚከፈት የባህል ድልድይ ነው የሚሉት የፎክሎር ባለሙያው ግርማ ጃለታ (ዶ/ር)፣ አንድ ባህል ራሱን ለሌላው ሲያሳይ የሚፈጠረው ነገር ትውውቅ ነው። ትውውቅ ሲጨምር መረዳት ይጨምራል። መረዳት ሲጨምር መከባበር ይጠናከራል። መከባበር ሲጠናከር ደግሞ አብሮነት የበለጠ ይጸናል።

በመሆኑም እንደ ኢሬቻ ያሉ የአደባባይ በዓላት ለጋራ ትርክት ግንባታና ለአንድነት ማጠናከር ጠቃሚ ሚና እንዳላቸውም ያስረዳሉ። የጋራ ትርክት ማለት ሁሉም ሰው አንድ ታሪክ ብቻ እንዲናገር ማድረግ አይደለም። የተለያዩ ታሪኮች በአንድ ማኅበራዊ ቦታ ተገናኝተው የጋራ ነገር እንዲፈልጉ ማድረግ ነው።

ኢሬቻ የሚያስተምረው ትልቁ ትምህርት ለተደረገልን በጎ ነገር ሁሉ ማመስገንን፣ ሰላምን፣ መከባበርን እና አንድነትን ነው።

> **“ኢሬቻ የአሁኑን ትውልድ ከትናንቱ የሚያገናኝ የባህል ድልድይም ነው፤ አዛውንት ከወጣት፣ ወላጅ ከልጅ፣ አንድ ትውልድ ከሌላው ትውልድ፣ አንዱ ህዝብ ከሌላው ጋር የሚገናኝበት በዓል ነው”**

በመሆኑም ኢሬቻ የአሁኑን ትውልድ ከትናንቱ የሚያገናኝ የባህል ድልድይም ነው። አዛውንት ከወጣት ጋር፣ ወላጅ ከልጅ ጋር፣ አንድ ትውልድ ከሌላው ትውልድ ጋር፣ አንዱ ህዝብ ከሌላው የሚገናኝበት ሥርዓት ነው። በመሆኑም ይህን ትልቅ ሀብት በኢትዮጵያውያን መካከል የአንድነት፣ የወንድማማችነት፣ የትብብርና የመደጋገፍ ባህል እንዲዳብር በተለያዩ መንገዶች መጠቀም ይገባል።

ኢሬቻ የሚካሄድበት ማንኛውም ቀዬ፣ ሐይቅ ወይም ስፍራ የሰላምና የእርቅ ስፍራ ነው። በንፁህ ልብ፣ ያላንዳች ቂምና በቀል ሰላምና እርቅን የሚያውጁበት ነው። ቂምና በቀል፣ አለመግባባትና ጥላቻ ያለው ማንኛውም ግለሰብ ጥላቻውን ሳይሽር፣ እርቅ ሳያወርድ፣ የገደለ ሳይክስ፣ እጁ ንፁህ ያልሆነ ግለሰብ ወደ ኢሬቻ አይሄድም።

እንደ የኦሮሞ ህዝብ ባህልም የተከለከለ ነው። ኢሬቻ ከመድረሱ በፊት አባ ገዳዎች በየአካባቢያቸው በየደረጃው ባለው መዋቅር ያለውን ችግር ይፈታሉ፤ የተጣላውን ያስታርቃሉ፤ ነፍስ ያጠፋ እንዲክስ ያደርጋሉ። ይህም የሚሆነው ሰላምና እርቅ ኢሬቻ ካለው እሴት መካከል አንዱ ስለሆነ ነው ይላል መረጃው።

በኢትዮጵያ የማይዳሰሱ ቅርሶች ተመራማሪ አቶ ገዛኸኝ ግርማ እንደሚሉት ኢሬቻ ሳያስቡ የተጋጩ ሰዎች እንኳን እርቅ የሚያወርዱበት ነው። ስለዚህ ኢሬቻ የእርቅና የአምላክ ምህረት የሚወርድበት ስፍራ ነው። ይህም በመሆኑ የኦሮሞ ህዝብ “ሰው እርስ በርሱ ከታረቀ ፈጣሪም ይታረቃል” የሚል አባባል አለው። ኦሮሞ “በንፁህ ልቦና ወደ ንፁህ መልካ ይወረዳል” ብሎ በምሳሌው የሚናገረውም ለዚህ ነው ይላሉ።

የገዳ ስርዓት የማይዳሰስ ቅርስ ሆኖ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት (ዩኔስኮ) ቅርስነት ከተመዘገበ ወዲህ የኢሬቻ በዓል የኦሮሞና የአገሪቷ ከመሆን አልፎ ዓለም አቀፍ ለመሆን እንደበቃም ይነገራል። ይህ ደግሞ ወንድማማችነትና ከብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ጋር መቀራረብ፣ በህዝቦች መካከል መተማመን እንዲኖር በማድረግ ለሀገር ሰላም ዋስትና በመሆን የተረጋጋች አገር በመገንባት ሂደት ውስጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው። በዚህ በዓልም የኦሮሞ ህዝብም ሆነ ሌሎች ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች በባህላዊ ልብስ አጊጠው ወደ በዓሉ ስፍራ እንደሚሄዱም የማይዳሰሱ ቅርሶች ተመራማሪው አቶ ገዛኸኝ ግርማ ጠቅሰዋል።

በመሆኑም ኢሬቻን ከኦሮሞ ህዝብ ባሻገር የተለያዩ ባህሎችን ማስተዋወቂያ መድረክ ማድረግ፣ የጋራ ማንነትን ለማጠናከር መጠቀም፣ ልዩ ባህሎች ሊኖሩን ቢችሉም በሰላም፣ በክብርና በአብሮነት የምንጋራቸውን የጋራ እሴቶች ማጉላት፣ የትብብርና የመደጋገፍ ባህልን ከሥነ-ሥርዓት ወደ ዕለታዊ ሕይወት ማሸጋገር፣ በዓሉ ላይ የሚታየው አብሮ መሰብሰብ በበዓሉ ቀን ብቻ እንዳይቀር በትኩረት መስራት፣ ትውልድ በትውልድ የሚተላለፍ የመከባበር ባህልን ማዳበር፣ በተለይም ኢሬቻን ወጣቶች የራሳቸውን ባህል ብቻ የሚማሩበት ሳይሆን የሌሎችንም ባህሎች በክብር የሚመለከቱበት የትምህርት መድረክ ማድረግ ይገባል። የዘንድሮውም የኢሬቻ በዓል “ኢሬቻ ለሀገራዊ መግባባት” በሚል መሪ ቃል እየተከበረ ነው።

# ከሚመሰረተው መንግሥት በኢኮኖሚው ዘርፍ ምን ይጠበቃል?

**በስንታየሁ ምትኩ**

በግንቦት ወር 2018 ዓ.ም በተካሄደው 7ኛው ጠቅላላ ምርጫ ኢትዮጵያውያን 'ይጠቅመኛል፣ ሀገርን ወደፊት ያራምዳል' ለሚሉት የፖለቲካ ፓርቲ ድምፃቸውን መስጠታቸው ይታወቃል፡፡ በምርጫው የህዝብ ይሁንታ ያገኘው የፖለቲካ ፓርቲ መስከረም 25 ቀን 2019 ዓ.ም ኢትዮጵያን ለሚቀጥሉት አምስት ዓመታት የሚመራውን መንግስት ይመሰርታል፡፡

አዲስ ዓመት አዲስ ተስፋን ይዞ እንደሚመጣ ሁሉ፣ አዲስ የሚዋቀረው መንግሥትም የህዝብን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ፣ በሀገሪቱ ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ እድገት እንዲመጣ የሚያስችል መፍትሔ ይዞ ይመጣል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የምጣኔ ሀብት መምህርና ተመራማሪ ደረጀ ዮሐንስ (ዶ/ር) ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለፁት፣ ባለፉት ዓመታት በኢትዮጵያ የኢኮኖሚ እድገት ለማምጣት በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፋይዳ ያላቸው ከዓመታት በፊት የተጀመሩና አዳዲስ ሜጋ ፕሮጀክቶች ተጠናቅቀዋል፡፡ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብን ብናነሳ ከወደቀበትና ከገባበት ችግር ማውጣት፣ ግንባታውን ማጠናቀቅ፣ ሀይልም እንዲያመነጭ ማድረግ መቻሉ ትልቁ ስኬት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

አዳዲስ፣ ለሀገር የሚጠቅሙ፣ ለአሁኑ ብቻ ሳይሆን ለሚቀጥለው ትውልድ የሚተርፉ፣ የኢኮኖሚ ሉዓላዊነትንና ነጻነትን የሚያረጋግጡ ፕሮጀክቶች ግንባታ ተጀምሯል፡፡ ለምሳሌ፡-የማዳበሪያ ፋብሪካ ግንባታውን ማንሳት ይቻላል። ግብርና የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት ቢሆንም ኢትዮጵያ ለግብርና ግብዓት የሚሆነውን ማዳበሪያ ከውጭ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ነበር የምታስገባው፡፡ ይህንን ቁልፍ ችግር ለመፍታት የአፈር ማዳበሪያ ፋብሪካ ግንባታ የተጀመረ ሲሆን፤ ፋብሪካው የውጭ ምንዛሪን በማዳን እና የሀገር ኢኮኖሚንና ምርታማነትን በማሳደግ ረገድ ከፍተኛ ሚና እንደሚኖረው የምጣኔ ሀብት ምሁሩ ደረጀ (ዶ/ር) ያነሳሉ፡፡

የሲሚንቶ ፋብሪካዎች ተገንብተዋል። በቢሾፍቱም በአፍሪካ ግዙፍ የሆነ፣ በዓመት ከ100 ሚሊዮን በላይ መንገደኞችን ማጓጓዝ የሚችል የአውሮፕላን ማረፊያ ግንባታ ተጀምሯል። እነዚህ ፕሮጀክቶች በቀላሉ የሚታዩ አይደሉም፡፡ የሚፈጥሩት የስራ ዕድልና የሚያስገኙት የውጭ ምንዛሪ ግኝት ከፍተኛ ነው፡፡ በኢኮኖሚክስ ትምህርት ውስጥ "Big Push Theory" በመባል የሚታወቅ ንድፈ-ሀሳብ አለ፡፡ አንድ ሀገር ከድህነት አዙሪት ለመውጣትና መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣት ጥቃቅን ስራዎች ላይ ከመጠመድ ይልቅ ከፍተኛ አቅም ያላቸው፣ በአንድ ጊዜ ወደፊት የሚያስፈነጥሩ ግዙፍ ፕሮጀክቶች ማከናወን ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አኳያ በኢትዮጵያ የተከናወኑና በመሰራት ላይ ያሉ ግዙፍ ፕሮጀክቶች ከድህነት ለመውጣትና ዘላቂ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችሉ ናቸው፡፡



ፎቶ- ከገፀ ድር

በኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ ማህበር ከፍተኛ ተመራማሪ ሞላ አለማየሁ (ዶ/ር)



ፎቶ- ከፋይል

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የምጣኔ ሀብት መምህርና ተመራማሪ ደረጀ ዮሐንስ (ዶ/ር)

በአሁኑ ወቅት በከተሞች እየተከናወኑ የሚገኙት የኮሪደር ልማት ስራዎችና ሌሎች ዘመናዊ የመሰረተ ልማት ግንባታዎች ከተሞችን ለኑሮና ለኢንቨስትመንት ምቹ በማድረግ ብቻ ሳይወሰኑ፣ የዜጎችን አስተሳሰብ በመቀየርና አጠቃላይ የሀገርን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ወደ ላቀ ደረጃ በማሸጋገር ረገድ የጎላ ድርሻ ይጫወታሉ፡፡

ፕሮጀክትን በአግባቡ መምራት፣ ቀንና ሌሊት መስራት ባህል እየሆነ መምጣቱን የገለጹት ደረጀ (ዶ/ር)፣ በተለመደው መንገድ በመሄድ ለውጥ ማምጣት አይቻልም፡፡ ዓለም ወደፊት እየሄደ ነው፡፡ ከዓለም ጋር አብሮ ለመራመድ የስራ ባህል፣ የፕሮጀክት አፈጻጸም ብቃትን መጨመር ግዴታ ነው፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የታዩ ለውጦች ይህንን የሚያመለክቱ እንደሆኑ አብራርተዋል፡፡

## ከሚመሰረተው መንግስት ምን ይጠበቃል?

መንግስት ኢኮኖሚውን የሚመራበት፣ የሚያረጋጋበትና የሚያሳድግበት የኢኮኖሚ ፖሊሲዎችና መሳሪያዎች አሉት፡፡ እነዚህን የፊስካል እና ሞኒታሪ ፖሊሲዎች በጥልቀት ማየት፣ ማጥናትና ትርጉም ባለው መልኩ ስራ ላይ ማዋል ከሚመሰረተው መንግስት እንደሚጠበቅ የምጣኔ ሀብት ምሁራን ያብራራሉ፡፡

የገንዘብ ፖሊሲው ትርጉም ባለው መልኩ ኢኮኖሚው ላይ ያለው ተፅዕኖ በአዎንታዊም ሆነ በአሉታዊ መልኩ መታየት የጀመረው በቅርብ ዓመታት እንደሆነ የሚያነሱት የምጣኔ ሀብት ምሁሩ ደረጀ (ዶ/ር)፣ የብሔራዊ ባንክ፣ የገንዘብ ሚኒስቴርና ሌሎች ተቋማት በሚመሩት የፊስካል ፖሊሲ የታክስ፣ በጀት፣ የመንግስት ገቢና ወጪ፣ የእዳ ጉዳዮችን ይወሰናሉ፡፡ እነዚህ ጉዳዮች የስራ ዕድልን በመፍጠር፣ ምርታማነትን በማሳደግ፣ የገበያ መረጋጋትን በማምጣት በቀጥታና በተዘዋዋሪ ተፅዕኖ አላቸው። እነዚህን መሳሪያዎች በመጠቀም አንገብጋቢ የሆነውን የወጣቶች የስራ ዕድል መፍጠር ላይ መስራት ይገባል፡፡ ወጣቶች ስራ ፈጣሪ እንዲሆኑ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ያስፈልጋል፡፡

የምጣኔ ሀብት ባለሙያው ደረጀ (ዶ/ር) እንደሚናገሩት፣ በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በጥሩ መልኩ እያደገ ነው፡፡ አሁን እያደገበት ካለው ፍጥነት እንዳይወርድ ማድረግ ያስፈልጋል። ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ እድገት እንዲኖር የፊስካልና ሞኒተሪንግ ፖሊሲዎች በጥንቃቄ በማጥናት መተግበር ዘላቂ ልማት ያመጣል፡፡

ከዚህ ባሻገር መንግስት ብቻውን በሚያደርገው የመዋዕለ ንዋይ ፍሰት ዘላቂነት ያለው ልማትን ማረጋገጥ ስለማይቻል የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን በመሳብ፣ በሀገር ውስጥ አቅም የማይሰሩ፣ ለመስራት አቅም የሚጠይቁ ስራዎች ላይ የውጭ ኩባንያዎች መዋዕለ ንዋያቸውን እንዲያፈስሱ ማድረግ ላይ የተጠናከረ ስራ መስራት ይገባል፡፡ ይህም የስራ እድል በመፍጠርና የውጭ ምንዛሪ ግኝትን በማሳደግ ከፍተኛ ፋይዳ ያለው በመሆኑ ኢንቨስትመንትን የሚያበረታቱ ፖሊሲዎችን ማውጣትና መተግበር ያስፈልጋል፡፡

ሌላው ግብርናውን የማዘመን ስራው አሁንም ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት የምጣኔ ሀብት ምሁሩ ደረጀ (ዶ/ር) ያነሳሉ፡፡ በሰው ጉልበትና በሬ ላይ የተንጠለጠለውን የአስተራረስ ዘዴና የምርት ሂደት ወደ መካናይዝድና ዘመናዊ የአመራረት ስርዓት መቀየር ላይ አጠናክሮ ማስቀጠል ይገባል፡፡ በትንሽ መሬት ላይ ዘመናዊ መሳሪያዎችና ግብአቶች በመጠቀም ከፍተኛ ምርት የሚያስገኙ አሰራሮች ያስፈልጋል፡፡ ኢንዱስትሪውም ሆነ የአገልግሎት ዘርፉ ከግብርና ጋር የተቆራኙ ናቸው፡፡ ከውጭ ለግብርና እና ማኑፋክቸሪንግ የሚገቡ ግብአቶችን በተቻለ መጠን በሀገር ውስጥ በማምረት መተካት ይገባል፡፡ እንዲህ አይነት እርምጃዎች የውጭ ምንዛሪን በማዳን፣ የሥራ እድል በመፍጠር፣ የዋጋ ግሽበትን በመቀነስ ለኢኮኖሚው ማደግ ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፡፡

በኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ ማህበር ከፍተኛ ተመራማሪ ሞላ አለማየሁ (ዶ/ር) በበኩላቸው፣ ኢትዮጵያ የማምረት እምቅ አቅም ቢኖራትም የእንስሳትና እንስሳት ተዋፅኦ ምርቶችን ከውጭ በማስገባት እየሸፈነች እንደምትገኝ ያነሳሉ፡፡ ኢትዮጵያ በቀንድ ከብት ብዛት በአፍሪካ አንደኛ ብትሆንም ለሀገር ውስጥ ፍጆታ የሚያስፈልጉ የእንስሳት ተዋፅኦ ውጤቶች ከውጭ እየገቡ ነው፡፡ ይህም ምርትና ምርታማነት በደንብ ካለማደጉ ጋር ይያያዛል፡፡ ዘመናዊ የአሰራር ዘዴዎችንና ቴክኖሎጂን በመጠቀም የግብአት አቅርቦት፣ የገበያ ትስስርና ስርጭት፣ ምርቶችን ገበያ ተኮር በማድረግ የግብርና ምርትና ምርታማነት ማሳደግ ያስፈልጋል።

ደረጀ (ዶ/ር) እንደሚናገሩት፣ የዋጋ ግሽበትን ለመቀነስ በረጅም ጊዜ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ ያስፈልጋል። ምርታማነት ሲጨምር አቅርቦት ያድጋል። ይህም ዋጋ እንዲቀንስ ያደርጋል። ከዚህ ባሻገር ምርት ወደ ገበያ እንዳይወጣ በመደበቅ እና ሰው ሰራሽ የዋጋ ንረት እንዲፈጠር የሚያደርጉትን በመቆጣጠር መንግስት የራሱን ሚና መጫወት አለበት፡፡ እንደ ቅዳሜና እሁድ ያሉ ገበያዎች አምራችና ሸማቹን በማገናኘት፣ በተመጣጣኝ ዋጋ የግብርና እና ኢንዱስትሪ ምርቶች መገኛ በመሆን የህብረተሰቡን ህይወት እያቀለሉና ገበያውን እያረጋጉ በመሆኑ ማስፋፋትና ስርዓት ያለው ግብይት እንዲኖር ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ሞላ አለማየሁ (ዶ/ር) በበኩላቸው፣ የአንድ ሀገር መንግስት እንደ መንግስትነቱ ሊወጣቸው የሚገቡ ዋና ዋና ኃላፊነቶች አሉ፡፡ ግሽበትን መቆጣጠር፣ የስራ ዕድል መፍጠር፣ ሁሉን አካታች የኢኮኖሚ እድገት ማምጣት እና የወጪና ገቢ ንግድ ሚዛንን ማስተካከል ከእነዚህ መካከል ይጠቀሳሉ፡፡ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እየተፈተነባቸው ካሉ ጉዳዮች መካከል የዋጋ ግሽበት ይጠቀሳል፡፡ ይህንን ፈተና ለማቃለል በቀጣይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ያስፈልጋል፡፡

የሥራ ዕድል ፈጠራም ሌላው ከሚመሰረተው መንግስት የሚጠበቅ ኃላፊነት መሆኑን ያነሱት ከፍተኛ ተመራማሪው ሞላ (ዶ/ር)፣ በሌሎች ሀገራት ስንመለከት የዋጋ ግሽበት ካለ፤ የስራ አጥ ዜጎች ቁጥር አነስተኛ ነው የሚሆነው፡፡ ነገር ግን በኢትዮጵያ ሁኔታ

ወደ ገጽ 21 ዞሯል


የሁላችን ከተማ አዲስ አበባ እንኳን ለኢሬቻ በዓል
በሰላም አደረሳችሁ ይላል።
IRREECHAA
ከተማችን አዲስ አበባ ለነገ ትዉልድ የሚተርፍ ስንቅ ሰንቃ ለነዋሪዎቿ ምቹ፣ ለጎብኝዎቿ ሳቢ በመሆን እንደ ስሟ ሁሌም አዲስ ዉብ እና አበባ ሆና እንኳን ለኢሬቻ በዓል በሰላም አደረሳችሁ ትላለች።
የኅብረ-ብሔራዊነታችን መገለጫ የሆነው ይህ በዓል ሲከበር ባህላዊ እሴቱን በማጎልበት፣ አንድነታችንን በማጠናከር፣ ለቱሪዝም ዘርፍ እድገትና ለሀገር ገፅታ ግንባታ ያለውን አስተዋጽኦ በማጉላት ሊከበር ይገባል።
የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
መልካም የኢሬቻ በዓል!


MIDROC INVESTMENT GROUP
ሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ
ሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ እንኳን ለኢሬቻ በዓል አደረሳችሁ!
እያለ መልካም ምኞቱን ይገልፃል!
ሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ በማኒፋክቸሪንግ፣ በግብርና፣ በማዕድን፣ በንግድ ፣ በሆስፒታሊቲ እንዲሁም በኮንስትራክሽንና ሪል እስቴት ዘርፎች የተደራጁ 45 ኩባንያዎችን ያቀፈና ከ80 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የስራ ዕድል መፍጠር የቻለ ተቋም ነው። ማህበራዊ ኃላፊነቱንም ለመወጣት ከትርፉ 10 በመቶውን በመመደብ እየሰራ ይገኛል። በተለያዩ አከባቢዎች ትምህርት ቤቶችን፣ የጤና ተቋማትን፣ መንገድ፣ ንጹህ ውሃ፣ የወንዝ ዳር ልማት፣ የመኖሪያ ቤቶች ግንባታና ሌሎች ስራዎችን እየሰራ ዜጎችን ተጠቃሚ አድርጓል። ወደፊትም ለሀገራችን የሚያበረክተውን አስተዋፅዖ አጠናክሮ ይቀጥላል።

# የበዓሉ አስተሳሳሪ እሴቶች

**በስንታየሁ ምትኩ**



ፎቶ፦ ከገፀ ድር

የኢሬቻ በዓል እሴቶችን ለህዝቦች አብሮነት እና ለሀገር እድገት መጠቀም ያስፈልጋል

የኦሮሞና የተለያዩ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ሳርና አደይ አበባ ይዘው "መሬ ሆ ... መሬ ሆ..." (ዞሮ መጣልን) እያሉ ፈጣሪን የሚያመሰግኑ ዜማዎችን እያሉ፣ ወደ መልካ (ወንዝ) ይወርዳሉ፤ ውሃውንም በሳሩ እየረጩ ፈጣሪን በደስታ ያመሰግናሉ፡፡ ኢሬቻ በታላቅ ድምቀት በሚከበርባቸው ሆራ ፊንፊኔ እና ሆራ አርሴዴ በርካታ ሰዎች በህብረ ቀለማዊ አልባሳት ተውበውና አጊጠው በዓሉ ላይ ይሳተፋሉ፡፡

የኦሮሞ ህዝብ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን የሚመራበት የገዳ ስርዓት አለው፡፡ ይህ ስርዓት በውስጡ ከያዛቸው መካከል ኢሬቻ አንዱ እንደሆነ ለ30 ዓመታት ያህል በኦሮሞ ታሪክና ባህል ዙሪያ ጥናትና ምርምር ያደረጉት፣ የኦሮሞ ጥናት ኢንስቲትዩት ዳይሬክተር በመሆን ያገለገሉት፣ የተለያዩ መጻሕፍትን ያዘጋጁት የማህበራዊ ሳይንስ ተመራማሪው አቶ አለማየሁ ሀይሌ ለዝግጅት ክፍላችን ይገልጻሉ፡፡ ኢሬቻ በዓመት ሁለት ጊዜ ይከበራል። አንደኛው ከመስከረም ወር አጋማሽ በኋላ የሚከበረው ኢሬቻ መልካ ሲሆን፤ ሌላኛው የበጋው ወራት ተገባድዶ በልግ ሲገባ፣ ግንቦት ወር ተራራ ላይ በመውጣት የሚከበረው ኢሬቻ ቱሉ ነው፡፡

የማህበራዊ ሳይንስ ተመራማሪው አቶ አለማየሁ እንደሚገልፁት፣ ኢሬቻ የክረምቱ ድቅድቅ ጨለማ፣ ዶፍ ዝናብ፣ ጎርፍና የመብረቅ ስጋት አልፎ፤ ደመናው ተገፍፎ፣ ሰማዩ ጠርቶ፣ ወንዞች ጎድለው፣ ምድሪቱ በአረንጓዴ አበባ አጊጣ ፀሐይ ስትታይ ለፈጣሪ ቸርነት ምስጋና በማቅረብ ይከበራል። ምስጋና የሚቀርበውም በመሰባሰብ ነው፡፡ ከተለያየ አቅጣጫ ከወንዝ ወዲህ እና ወዲያ ማዶ በወንዝ ሙላት ተለያይተው የነበሩ ቤተሰቦች፣ ወዳጅ ዘመድና ሌሎችም በመገናኘት ፈጣሪን ያመሰግናሉ፡፡ በግንቦት ወር የሚከበረው ኢሬቻ ቱሉ፣ ማህበረሰቡ ለረጅም ጊዜ የዝናብ እጥረት ሲያጋጥመውና ከብቶች ሲጎዱ "ፈጣሪ ሆይ ዝናብህን ላክልን፣ ታረቀን" በማለት በፍጹም ትህትና በጋራ የሚለምንበት ነው፡፡

በኢሬቻ አከባበር ወቅት አባ ገዳዎች፣ ሀደ ሲንቄዎች፣ ወጣቶች፣ ልጃገረዶች፣ ሕፃናት በውብ ባህላዊ አልባሳት ተውበው በደስታ ያከብራሉ፡፡ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ህዝብ የሚሳተፍበት እንደመሆኑም ማህበራዊ ትስስርን ከማጠናከሩ ባለፈ በንግድ፣ በትራንስፖርት፣ በአልባሳትና በምግብ አገልግሎት ዘርፍ ለተሰማሩ በርካታ ዜጎች ከፍተኛ የኢኮኖሚ እድልና ጥቅም ይዞ ይመጣል።

አቶ አለማየሁ እንደሚያስረዱት የኢሬቻ በዓል ሥነ ስርዓት መሪዎች አባ ገዳዎች፣ አባ መልካዎችና አባ ቦኩዎች ሲሆኑ፣ የመሪነታቸው መገለጫ የሆኑ ባህላዊ ምልክቶችን ይይዛሉ፡፡ አክሊል ዓይነት በግንባር ላይ የሚታሰር የክብርና የመሪነት ምልክት (ከለቻ)፣ አበባና ሳር፣ አለንጋና ኦሮሮ (ዘንግ) በመያዝ ነው ወደ መልካ የሚያመሩት፡፡ አበባ የፍሬና የትውልድ ቀጣይነት ማሳያ ሲሆን፣ አረንጓዴው ሳር ደግሞ ለሰው ልጅና እንስሳት ህይወት መደገፍ ፈጣሪ የሰጠው ጸጋ እንደሆነ በመወሰድ ምስጋና ይቀርባል፡፡

በኢሬቻ ወቅት ጦር መያዝ በጥብቅ የተከለከለ ነው። ጦር ራስን ከጠላት የመጠበቂያና የማጥቂያ መሳሪያ ነው። አባ ገዳዎች በዚህ ወቅት የሚይዟቸው አለንጋና ዘንግ ግን ህግና ስርዓት የማስከበር፣ የፍትሕና የሰላም ምልክቶች ናቸው። እናቶችና ሴቶች ደግሞ የሴት ልጅን መብት፣ ክብር መጠበቂያ ምልክት የሆነውን ሲንቄ በመያዝ ወደ መልካው ያመራሉ። በበዓሉ ላይ ዕድሜአቸው ከ15 ዓመት በታች ለሆኑ ያላገቡ ልጃገረዶች፣ እናቶችና አባ ገዳዎች ቅድሚያና ከፍተኛ ክብር ይሰጣቸዋል። በጋራ እየዘመሩና አዲሱ ዓመት የደስታ እንዲሆን እየተመኙ ወደ ወንዙ ያመራሉ፤ አባ ገዳው ችግሮች እንዲፈቱና ሰላም እንዲወርድ ይመርቃሉ። በእጃቸው የያዙትን ወተትና ጠጅ ቀምሰው በአካባቢው ላይ በመርጨት የምስጋናውን ሥነ ሥርዓት ያጠናቅቃሉ።

አቶ አለማየሁ እንደሚያስረዱት፣ ኢሬቻ ከፍ ያለ ማህበራዊ ፋይዳ ያለው የሰላምና የዕርቅ በዓል ነው። በበዓሉ ዋዜማ የተጣሉ ሰዎች ሁሉ ይቅር ተባብለው፣ በሆዳቸው የያዙትን ቅሬታ አውጥተው በመታረቅ እጅ ለእጅ ተያይዘው ወደ ኢሬቻ ይሄዳሉ። ቂም፣ በደልና ጥላቻ ይዞ ወደ መልካ መሄድ ፈጽሞ አይፈቀድም። ኢሬቻ ላይ ከአፍ ከፉ ቃላትን ማውጣትና መጣላት ነውር ነው፡፡ በኢሬቻ መድረክ ፈጣሪን ማሞገስ፣ እናትና አባትን፣ አባ ገዳዎችን፣ ሀደ ሲንቄዎችንና ህጻናትን ማክበር ብቻ ይንጸባረቃል።

የኢሬቻ በዓል ከመድረሱ በፊት አባገዳዎችና የሀገር ሽማግሌዎች በየአካባቢው እየሄዱ በማህበረሰቡ መካከል ቅሬታና አለመግባባት ካለ እንዲፈታ፣ ይቅር እንዲባባሉ፣ ደም የተቃባ ካለ ካሳ እንዲከፍል ያደርጋሉ፡፡ ኢሬቻ በንፁህ ልቦናና አዕምሮ፣ ያለ ቂምና ቁርሾ የሚካሄድ፤ ሠላም የሚሰበክበት ነው፡፡ ኢሬቻ የሚካሄድበት ስፍራ ሁሉ የሠላምና የእርቅ ቦታ ነው፡፡ ለምስጋና መልካ ከተወረደ በኃላም አባገዳዎች "ዕርስ በዕርሳችሁ ይቅር ተባብላችኃል? ዕርስ በዕርሳችሁ ሠላም ናችሁ? ከፍጥረታትና ከፈጣሪ ጋር ሠላም አውርዳችኃል?" ብለው ይጠይቃሉ፡፡ ምናልባት በየአካባቢው እርቅ ሳያወርድ የመጣ ካለ እንኳን በዚህ ወቅት ይቅርታ በመጠያየቅ ምስጋናውን አቅርቦ ይሄዳል፡፡

ሌላው የኢሬቻ እሴት ሰላም እንደሆነ የማህበራዊ ሳይንስ ተመራማሪው አቶ አለማየሁ ያነሳሉ፡፡ በኢሬቻ ሰላም እንዲመጣ ይለመናል፡፡ ከራስ፣ ከማህበረሰብ፣ ከተፈጥሮና ከሀገር ጋር ሰላም እንዲወርድ ጸሎት ይደረጋል።

ኢሬቻ የኦሮሞ ህዝብ ባህላዊ ሀብት ቢሆንም፣ የኃይማኖትና የብሔር ልዩነት ሳይደረግ ማንኛውም ኢትዮጵያዊና የውጭ ሀገር ዜጋ የሚሳተፍበት፣ የአብሮነት እሴት ያለው በዓል እንደሆነ አቶ አለማየሁ ያስረዳሉ፡፡ የልዩነት ሳይሆን የጠበቀ አንድነት፣ የፍቅርና የሰው ልጅ አብሮነት የሚታይበት በዓል ነው፡፡ ፈጣሪውን የሚያመልክ ማንኛውም ሰው ከኦሮሞ ህዝብ ጋር በኢሬቻ ፈጣሪውን ማመስገን ይችላል፡፡ ይህም ኢሬቻ የልዩነት ሳይሆን የአንድነትና የአብሮነት በዓል መሆኑን ያሳያል፡፡ እንኳን በአንድ ሀገር የሚኖሩ የተሳሰሩ ኢትዮጵያዊያን፣ የውጭ ዜጎችም መጥተው ቢታደሙ የሚከለክላቸው የለም፡፡ ኦሮሞ በባህሉ በሞጋሳና ጉዲፈቻ አማካኝነት ባዕዳ አስጠግቶ ባህሉን በማውረስ፣ ሀብትና ንብረቱን በማካፈል አብሮ ይኖራል፤ ዝምድናውንም ያጠናክራል፡፡ ኢሬቻ አካታች፣ ህዝብን የማይለያይ፣ በጋራ ለፈጣሪ ምስጋና የሚቀርብበት በዓል ነው ይላሉ፤ አቶ አለማየሁ፡፡

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የፎክሎር ትምህርት ክፍል መምህር ፊሌ ጃለታ (ዶ/ር) ከዚህ ቀደም የኢሬቻን ፋይዳ በተመለከተ ለዝግጅት ክፍላችን በሰጡት መረጃ፣ ኢሬቻ በህዝቦች መካከል ትስስርና ማህበራዊ መስተጋብር የሚጠናከርበት በዓል ነው፡፡ በተለይ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በሆራ ፊንፊኔ የተለያዩ ብሔሮችና ብሔረሰቦች፣ በውጭ የሚኖሩ ትውልደ ኢትዮጵያውያን እንዲሁም ከጎረቤት ሀገር ኬንያ ድረስ ተሳታፊዎች እየመጡ እያከበሩት መሆኑን ለዚህ በማሳያነት ያነሳሉ፡፡

ብዙ ጊዜ የሲዳማ ብሔር የዘመን መለወጫ በዓል ፊቼ ጨምበላላ ሲከበር አባገዳዎች፣ ሀደ ሲንቂዎች፣ ወጣቶች እየተጋበዙ ወደ ሀዋሳ እየሄዱ ይሳተፋሉ። ኢሬቻ ላይም የሲዳማ ብሔር ተወላጆች በተመሳሳይ ተገኝተው ያከብራሉ። የከምባታ፣ ሀዲያ፣ ወላይታ፣ ጉራጌና ሌሎችም ብሔሮችና ብሔረሰቦች በቡድን ሰብሰብ ብለው በየራሳቸው ባህላዊ አልባሳት ተውበው፤ መገልገያ ቁሳቁሶችን ይዘው በመምጣት ኢሬቻን ያደምቃሉ፤ ያስውባሉ፡፡ እንዲህ ዓይነት ግንኙነቶች በህዝቦች መካከል ያለው ማህበራዊ ትስስርና መስተጋብር እየተጠናከረ እንዲሄድ ያግዛል፡፡

የፎክሎር ምሁሩ ፊሊ (ዶ/ር) እንደሚገልፁት፣ በኢሬቻ በዓል በህዝቦች መካከል ያለው ማህበራዊ ትስስር ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መጥቷል። በበዓሉ አጋጣሚ የሚገናኙ የተለያዩ ብሔሮችና ብሔረሰቦች የባህል መሪዎችና ሽማግሌዎች ዕርስ በዕርሳቸው ልምድ ይለዋወጣሉ፡፡ በበዓላት ላይ ተዋውቀው እስከ ጋብቻ የደረሱም አሉ፡፡ ከአንድ አካባቢ የሚመጡ ተሳታፊዎች የጉጂ፣ ቦረና፣ የሜጫ፣ ቱለማ፣ ራያ አዘቦ ወይም ሌላ ማህበረሰብ የባህል አልባሳትን ገዝተው ይሄዳሉ። የኢሬቻ ብቻ ሳይሆን የገዳ መገለጫ የሆኑትን እንደ ቦኮ፣ ሽረሮ፣ ጨሌ፣ ኢሌላ ይገዛሉ፡፡

የኦሮሞ ተወላጆችም በተመሳሳይ ፊቼ ጨምበላላ ላይ ሲሳተፉ የሲዳማ መገለጫ የሆኑ ቁሳቁሶችን ይሸምታሉ፡፡ በዚህም ዕርስ በዕርስ ልምድ እና የጥበብ ዲዛይን ይለዋወጣሉ። ወጣቱ ትውልድም ከዚህ ተምሮ ትውፊቱን ወደ ቀጣይ ትውልድ እንዲያሸጋግረው ይረዳል። ቁሳቁሶችን መለዋወጥ ግንኙነትን ያጠናክራል። ሌሎችም ባህላዊ መገለጫዎች ከፍተኛ ዋጋና ትርጉም ያላቸው ናቸው፡፡ በዚህ መንገድ ዕርስ በዕርስ ይማማራሉ፤ ግንኙነታቸውም እየጠነከረ ይሄዳል።

የኢሬቻ እሴቶች የሆኑት አንድነትን፣ ሰላምን፣ ፍቅርን፣ ህብረትን በማጠናከር ለሀገር ግንባታ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያላቸው በመሆኑ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፉ አባ ገዳዎችን ጨምሮ የሁሉም ባለድርሻ አካላት ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ የህዝቡን ባህላዊ ማንነትና ጥንታዊ እሴቶች ጠብቆ ከዘመኑ ጋር አብሮ መሄድ አስፈላጊ መሆኑንም አሰምረውበታል፡፡

# አዲስ አበባ በ"ዲጂታል ኢትዮጵያ 2030" መነፅር




ግራፊክስ:- በእዮብ ተፈራ

አዲስ አበባ በልዩ ትኩረት ከምታከናውናቸው ስራዎች መካከል ከተማዋን የዲጂታል ኢትዮጵያ 2030 ማዕከል ማድረግ ተጠቃሽ ነው

**በስንታየሁ ምትኩ**

በኢትዮጵያ የአስር ዓመት መሪ የልማት እቅድ ትኩረት ከተሰጣቸው ቁልፍ ጉዳዮች መካከል የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት አንዱና ዋናው ነው። ዘርፉ ለዲጂታል ኢኮኖሚ ግንባታ መሠረት በመጣል፣ የሌሎችን የኢኮኖሚ ዘርፎች እንቅስቃሴ በማሳለጥ እና ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ ረገድ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡ ባለፉት ዓመታት በዚህ ረገድ በተከናወኑ ተግባራትም አበረታች ውጤት ተመዝግቧል፡፡

በተለይም ከሰባት ዓመታት በፊት ይፋ ተደርጎ፤ ትግበራው የተጠናቀቀው የ"ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025" ስትራቴጂ በሀገር አቀፍ ደረጃም ሆነ በአዲስ አበባ በርካታ ተጨባጭ ስኬቶች እንዲመዘገቡ መንገድ ጠርጓል፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ የሳይበር ሴኪዩሪቲ ዳይሬክተር አቶ ዮናስ ደምሰው ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለጹት፤ በመዲናዋ በስትራቴጂው የተያዙ ግቦችን ከማሳካት አኳያ ከተጠበቀው በላይ አበረታች ውጤት ማምጣት ተችሏል፡፡

ዳይሬክተሩ ከተመዘገቡ ውጤቶች መካከል ማሳያ ይሆኑ ዘንድ የተወሰኑትን ጠቅሰዋል፡፡ የመንግስትና የህዝብ አገልግሎት ክፍያዎች ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ ከጥሬ ገንዘብ ንክኪ ነጻ በሆኑ እንደ ቴሌብር፣ ሲቢኢ ብር እና የባንክ ዲጂታል መተግበሪያዎች አማካኝነት እንዲፈጸሙ ማድረግ ተችሏል፡፡ ይህም የአገልግሎት ቅልጥፍናን ከማሳደግ ባሻገር ህገ ወጥ የገንዘብ ዝውውርንና እንግልትን ቀንሷል፡፡ አዲስ አበባን ዘመናዊና ለነዋሪዎቿ ምቹ ለማድረግ የተከናወኑት የኮሪደር እና

> "ከሰባት ዓመታት በፊት ይፋ ተደርጎ፤ ትግበራው የተጠናቀቀው የ'ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025' ስትራቴጂ በሀገር አቀፍ ደረጃም ሆነ በአዲስ አበባ በርካታ ተጨባጭ ስኬቶች እንዲመዘገቡ መንገድ ጠርጓል"

የወንዝ ዳርቻ ልማት ፕሮጀክቶች ወደ ስማርት ከተማነት የሚያሸጋግሩ የዲጂታል የከተማ ልማት ስራዎች ናቸው።

ሌላው በዲጂታል ስትራቴጂው ትኩረት የተሰጠውና ውጤት የተገኘበት በመንግስት አገልግሎት አሰጣጥ የሚታየውን እንግልት፣ ሰልፍና ወረፋ እንዲሁም ብልሹ አሰራር ለመቀነስ አገልግሎቶችን በዲጂታል ቴክኖሎጂ አስደግፎ መሰጠቱ እንደሆነ የሚገልጹት የሳይበር ሴኪዩሪቲ ዳይሬክተሩ አቶ ዮናስ፣ ለምሳሌ፡- በአዲስ አበባ ከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የሚሰጡ አገልግሎቶች ዘመናዊ፣ ግልጽ፣ ቀልጣፋና ከብልሹ አሰራር የፀዱ ለማድረግ የሚያስችል የተቀናጀ የመሬት ይዞታ ማስተዳደሪያ ሥርዓት (Integrated tenure management system) የተሰኘ ቴክኖሎጂ ለምቶ ወደ ስራ እንዲገባ ተደርጓል፤ በዚህም ተገልጋዩ ከማመልከቻ ጀምሮ ጉዳዩን በኦንላይን የሚከታተልበት ስርዓት ተፈጥሯል፡፡ የታክስ ማሳወቅና ክፍያ፣ የንግድ ፈቃድ፣ ምዝገባና እድሳት፣ የሲቪል ምዝገባና የነዋሪነት አገልግሎት እና ሌሎችም በዲጂታል ቴክኖሎጂ ተደግፈው እየተሰጡ እንደሚገኙ አብራርተዋል፡፡

የተለያዩ የመንግስት አገልግሎቶችን ዜጎች ያለ እንግልት በአንድ ማዕከል በዲጂታል ቴክኖሎጂ በመታገዝ ማግኘት የሚችሉበት የአዲስ መሶብ ዲጂታል የአንድ ማዕከል አገልግሎትም ወደ ስራ እንዲገባ የተደረገ ሲሆን በአሁኑ ወቅትም 11 ቅርንጫፍ የአገልግሎት ማዕከላትን በሁሉም ክፍለ ከተሞች ማዳረስ ተችሏል። ነዋሪዎች በአንድ ማዕከል ከ150 በላይ አገልግሎቶች ማግኘት የሚችሉበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ በተጨማሪም የቴሌ፣ የመብራት፣ የውልና ማስረጃ፣ የአውቶብስ አገልግሎቶችን በዲጂታል ቴክኖሎጂ አስደግፎ በመስጠት ውጤት ማምጣት እንደተቻለ አቶ ዮናስ ያብራራሉ፡፡

በዲጂታል ቴክኖሎጂ ታግዘው በሚሰጡ አገልግሎቶች የተገልጋዩን እርካታ ስንመለከትም ለምሳሌ በአዲስ መሶብ ዲጂታል የአንድ ማዕከል አገልግሎት ዲጂታል ቴክኖሎጂን በመጠቀም በተደረገው የዳሰሳ እርካታ 99 ነጥብ 6 በመቶ ተገልጋዮች በአገልግሎቱ መርካታቸውን ያሳያል፡፡ ይህም የአገልግሎት አሰጣጡን በማሻሻል በተሰራው ስራ ትልቅ ለውጥ መምጣቱን፣ በዲጂታል ኢትዮጵያ ስትራቴጂክ እቅድ ውስጥ ከተካተቱት ውስጥ አንዱ የሆነውን "ስማርት ገቨርናንስ" በትክክል መተግበሩንና ውጤታማ መሆን መቻሉን አቶ ዮናስ ያስረዳሉ፡፡

ከዚህ ባሻገር አቅመ ደካሞች፣ በሽተኞች፣ አካል ጉዳተኞች ቤታቸው ሆነው አገልግሎት ማግኘት የሚችሉበት ስርዓት ለመፍጠር እየተሰራ ይገኛል፡፡ በአሁኑ ወቅት በተንቀሳቃሽ አውቶቡስ አማካኝነት በተለያዩ ቦታዎች በመዘዋወር ሰዎች በብዛት በሚንቀሳቀሱባቸው አካባቢዎች የአዲስ መሶብ አገልግሎቶች እየቀረቡ ነው፡፡ ቴክኖሎጂን በትክክል መጠቀምንና መላመድን እንዲሁም ፈጠራን በመፍጠር ጭምር ውጤታማ ስራዎች ተከናውነዋል፡፡

መስከረም 20 ቀን 2019 ዓ.ም የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ባካሄደው መስራች ጉባኤ ላይ የአዲስ አበባ ከንቲባ ሆነው የተሾሙት አዳነች አቤቤ እንደተናገሩት፣ የከተማ አስተዳደሩ በቀጣይ ልዩ ትኩረት ከሚሰጣቸው ተግባራት መካከል የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ሥራዎችን በማፋጠን አዲስ አበባን የ"ዲጂታል ኢትዮጵያ 2030 ርዕይ" ዋና ማዕከል ማድረግ አንዱ ነው፡፡

አቶ ዮናስ እንደገለፁት፣ የ"ዲጂታል ኢትዮጵያ 2030" ትኩረት ከቴክኖሎጂ ተጠቃሚነት ወደ ቴክኖሎጂ ፈጣሪነት መሸጋገር ነው፡፡ በአዲስ አበባ ደረጃ ሁሉም የመንግስት አገልግሎቶች በቴክኖሎጂ ተደግፈው (በኦንላይን) ወይም ከወረቀት ነጻ በሆነ መንገድ የሚሰጡበትን ሁኔታ መፍጠር አንደኛው ትኩረቱ ነው፡፡ ይህንንም ለመፍጠር የአዲስ አበባ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ አቅሙን በማሳደግ ላይ ይገኛል፡፡

ሌላኛው የስትራቴጂው ትኩረት ሁሉንም ዜጎች የቴክኖሎጂ ዕድል እኩል ተጠቃሚ ማድረግ ሲሆን ከዚህ አኳያ አብዛኛው የከተማዋ ነዋሪ የኢንተርኔት፣ የስልክና ኔትዎርክ አገልግሎት ተጠቃሚ ነው፡፡

ከመንግስት አገልግሎት አኳያ ሌላው በስትራቴጂው ትኩረት የተሰጠው የፋይዳ መታወቂያ ነው፡፡ እንደ አዲስ አበባ ከተማሪ ጀምሮ ማንኛውም ዜጋ የዲጂታል መለያ (ፋይዳ መታወቂያ) እንዲኖረው የማድረግ ስራ ተሰርቷል፡፡ በአዲስ መሶብ የሚሰጡትንና ቀጣይ በዲጂታል ታግዘው የሚሰጡ አገልግሎቶች ከፋይዳ መታወቂያ ጋር እንዲገናኙ በማድረግ የማረጋገጥ ስራው ተጠናክሮ እንደሚቀጥልም የሳይበር ሴኪዩሪቲ ዳይሬክተሩ አቶ ዮናስ ጠቁመዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በሰው ሰራሽ አስተውሎት (Artificial Intelligence) የታገዙ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የተለያዩ ስራዎችን ለማከናወን ታቅዶ ወደ ትግበራ ተገብቷል። ለምሳሌ፡- የመንገዶችን የአገልግሎት ሁኔታና የትራፊክ ፍሰት የመከታተል፣ የትራፊክ ህግ ተላላፊዎችን በዲጂታል መንገድ የመለየት እንዲሁም የተሽከርካሪዎችን እንቅስቃሴ በቀጣይነት በመቆጣጠር ፍሰቱን ቀልጣፋ፣ ደህንነቱ የተጠበቀና የተሳለጠ ለማድረግ ይሰራል፡፡

ዜጎች ያለ እንግልት እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር ያሉ የተለያዩ የመንግስት አገልግሎቶችን በአንድ ቦታ በፍጥነት እንዲያገኙ ለማስቻል በተያዘው ዓመት ተጨማሪ 20 የአዲስ መሶብ ዲጂታል የአንድ ማዕከል አገልግሎት ቅርንጫፎችን ለመክፈት ታቅዶ እየተሰራ እንደሚገኝም አቶ ዮናስ ጠቁመዋል፡፡

በዲጂታል ኢትዮጵያ 2030 ስትራቴጂ መሠረት፣ ቀልጣፋ የዲጂታል አገልግሎትን ለመስጠት የሚያስችል የመሠረተ ልማት ግንባታ ትኩረት ተሰጥቶት እየተከናወነ ይገኛል። ከዚህ አኳያ "ሲቲኔት" (CityNet) በተሰኘ የኔትዎርክ ሥርዓት የከተማ አስተዳደሩን

ወደ ገጽ 21 ዞሯል

ከጥንት ከጠዋቱ እንግዳ ተቀባይነታችን የተመሰከረልን!
ሰላም ወተው ሰላም እንዲገቡ የምንተጋ!
እንደ ሀገር የእስማርት ሲቲ ትግበራ ቀደምት የሆንን!
የኮንፍረንስ ቱሪዝም ማዕከል የሆንን!
የአዳዲስ ህሳቤ ትግበራ እና የተለያዩ እኒሼቲቭ ማዕከል የሆንን!
የከተማ ግብርናን በስፋት እውን ያደረግን!
በውብ ተፈጥሮ የተሞላን!
የቱሪስት መናገሻ ውብ ከተማን የገነባን ነን፡፡

## እንኳን ለ2019 ኢሬቻ በዓል በሰላም አደረሳቹ!

አዳማ ከተማ በቀጨማ እና በቦሰት ተራሮች ተከባ ድንቅ ተፈጥሮዋዊ አቀማመጥን ተጎናጽፋ ከመዲናችን አዲስ አበባ በስተምስራቅ በ87.5 ኪ.ሜ ርቀት የምትገኝ የንግድ ማዕከል፤ የኮንፍረንስ ቱሪዝም ከተማ ናት ፡፡
አዳማ ከተማ በ2015 ጀምሮ ወደ ሪጂኦፖሊ ከተማ ማደጓን ተከትሎ ከተማይቱን የኢንዱስትሪ ማዕከል ለማድረግ እና እስማርት ሲቲን ለመተግበር ሰፋፊ ክንውኖች ተከናውኗል፡፡
አዳማ ከተማ መስተዳድር የአስር አመት የብልጽግና ጉዞ ዕቅድን ለማሳካት ከተቀመጡ የከተማ ልማት ግቦች መካከል የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ፤ ኢንተርፕሩነር በስፋት መፍጠር፤የተለያዩ ሞያዎችን ማስፋፋት እና ጠንካራ የመንግስት መዋቅር (E-Governace) እውን ለማድረግ፤ የስራ ባህልን በማሻሻል ቀን ከሌት በመትጋት እና ህብረተሰቡን እንዲሁም ባለሀብትን በማሳተፍ የቤተሰብ ብልጽግናን ለማረጋገጥ ደበል የሚያሰኝ ውጤታማ ስራዎችን አከናውኗል፡፡
በተለይም አሁን ላይ መስተዳድሩ የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት በተሻለ ደረጃ የሚያረጋግጡ ፤ የመንግስት የአገልግሎት አሰጣጥን ዲጂታላይዝድ በማድረግ አገልግሎቱ የተሳለጠ እንዲሆን ማድረግ የቻለበት እና አዳማ ከተማ የተሞክሮ ማዕከል ማድረግ ተችሏል፡፡
የከተማዋን የእድገት ጉዞ በደበልጥ ለማሳለጥ የኮሪደር ልማት ግንባታ ባጠረ ጊዜ ተገንብቶ ለአገልግሎት ክፍት በማድረግ ለከተማዋ ልዩ እይታን እና ለነዋሪዎቿ ምቹ ሁኔታን ከመፍጠር ባሻገር የኢኮኖሚ እንቅስቃሴን ለማሳለጥ ምቹ ሁኔታን መፍጠር ተችሏል፡፡
በተጨማሪም በመንግስት በጀት፤ በህዝብ ተሳትፎ እና በዜግነት አገልግሎት የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ ፕሮጀክቶች ገንብቶ ለአገልግሎት ክፍት በማድረግ የነዋሪውን የልማት ጥያቄ ባጠረ ጊዜ በመመለስ ላይ ይገኛል፡፡
ከተማችን በግብርና፣ በቤት ተኮር፣ በኮሪደር እና መሰል ስራዎች ህብረተሰባችንን ተጠቃሚ ያደረጉ ስራዎችን በላቀ ደረጃ ማከናወን ችሏል፡፡
የፍቅር፣ የመተሳሰብና የአንድነት ከተማ የስምጥ ሸለቆ ዕንቁ ወደ ሆነችው የሰላም አምባሳደር አዳማ ከተማ በመምጣት ባለው ምቹ መንግስታዊ አስተዳደር፣ ምቹ የዐየር ጠባይ እና ገቢ የማሰባሰብ አቅማችን ከአመት አመት እየጎለበተ የመጣ የንግድና ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ተመራጭ ወደ ሆነችው ከተማችን ጎራ ይበሉ፡፡

ኑ አዳማን በጋራ እናልማ!

## የአዳማ ከተማ አስተዳደር መልካም የኢሬቻ በዓል!






# የመዲናዋ ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች









ፎቶ- ከገፀ ድር

በመዲናዋ በሳምንቱ ከሚካሄዱ የጥበብ መሰናዶዎች በከፊል

**በአብርሃም ገብሬ**

ባሳለፍነው ሳምንት በመዲናችን አዲስ አበባ የተለያዩ ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች ለጥበብ አፍቃሪያን ሲደርሱ ቆይተዋል፡፡ ዛሬን ጨምሮ በሚቀጥሉት ቀናትም መሰል መሰናዶዎች ይቀርባሉ፡፡ ከእነዚህ መሰናዶዎች መካከል የአዳዲስ መጻሕፍት ህትመት፣ የሙዚቃ ዝግጅት እና የቴአትር መርሃ ግብር ይገኙበታል። ለመረጃ ይሆንዎት ዘንድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እንደሚከተለው አዘጋጅቷቸዋል፡፡

## መጽሐፍ

ቴክኖሎጂ ነክ ዝግጅቶችን በቴሌቪዥን በማቅረብ የሚታወቀው የደራሲና ጋዜጠኛ ሰለሞን ሙሉጌታ ካሳ አዲስ መጽሐፍ ለንባብ በቅቷል፡፡ "አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ" በሚል ርዕስ ለንባብ የበቃው ይኸው የደራሲው መጽሐፍ፣ የአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ምንነትና ወደፊት በሰው ልጆች ሕይወት ላይ ምን አይነት ሚና እንደሚኖረው በጥልቀት ይዳስሳል፡፡ ደራሲው ከዚህ በፊት ከኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ጋር የተያያዙ መጽሐፍትን ለንባብ ያበቃ ሲሆን፣ አሁን ደግሞ በዚህ ዘመን ትልቅ ተጽዕኖ እያሳደረ በሚገኘው የአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ላይ ያተኮረ መጽሐፍ ለንባብ አብቅቷል፡፡ መጽሐፉ በተለያዩ የመጻሕፍት መደብሮች የሚገኝ ሲሆን፣ በቀጣይ የምረቃ እና የፊርማ መድረኮች ይካሄዳሉ ተብሏል፡፡

## ሙዚቃ

"ሴቷ ጌታቸው መኩሪያ" በሚል ቅጽል ስም የምትታወቀው ሳክስፎኒስት ይርጋሸዋ ደብሩ የፊታችን ሐሙስ መስከረም 28 ቀን 2019 ዓ.ም ከእቴጌ የሴቶች የጃዝ ባንድ ጋር በመሆን የሙዚቃ ሥራዎቿን ታቀርባለች፡፡ በዚሁ መድረክ ላይ አንጋፋው ሙዚቀኛ ግርማ በየነም ሥራዎቹን ያቀርባል ተብሏል፡፡ የሙዚቃ ድግሱ የሚቀርበው ሀያት ረጀንሲ ሆቴል በሚገኘው ፈንድቃ የባህል ማዕከል ከምሽቱ 2፡00 ሰዓት ጀምሮ ነው፡፡

## ሥዕል

በአሊያንስ ኢትዮ ፍራንሴስ አዲስ የሥዕል አውደ ርዕይ ሊከፈት ነው፡፡ ሰዓሊ ሙሉ ለገሰ "I Carry – Je Porte" በሚል ርዕስ በተለያዩ ጊዜያት የሳለቻቸው የሥዕል ሥራዎች የሚቀርቡበት ይሄው አውደ ርዕይ፣ የፊታችን ሐሙስ መስከረም 28 ቀን 2019 ዓ.ም. በይፋ ይከፈታል፡፡ ሰዓሊዋ ረቂቅ የአሳሳል ዘይቤ በመጠቀም የሳለቻቸው የጥበብ ሥራዎች እስከ ጥቅምት 21 ቀን 2019 ዓ.ም ድረስ ለዕይታ ክፍት ሆኖ ይቆያል፡፡ የጥበብ አፍቃሪያንም በሥፍራው ተገኝታችሁ እንድትታደሙ ተጋብዛችኋል፡፡

## የቴአትር መርሃ-ግብር

በመዲናችን አዲስ አበባ ቅዳሜ እና እሁድ የተለያዩ ቴአትሮች ይታያሉ። በብሔራዊ ቴአትር ቤት ቅዳሜ 7፡30 ሰዓት "12ቱ እንግዶች" እንዲሁም በ11:30 ሰዓት "በር የሌለው ቤት" ይታያሉ። እሁድ ደግሞ በ7፡30 ሰዓት "ንጉስ አርማሕ" እንዲሁም በ11፡30 ሰዓት "እምዬ ብረቷ" ለጥበብ አፍቃሪያን ይቀርባሉ፡፡ ተመልካቾችም ጊዜያቸውን ለመቆጠብ የ"ሁሉ በጄ" መተግበሪያን በመጠቀም ትኬቶችን አስቀድመው መግዛት እንደሚችሉ ተገልጿል።

በአዲስ አበባ ቴአትርና ባህል አዳራሽ ደግሞ "እሳት ወይ አበባ" ዘወትር ቅዳሜ በ11፡00 ሰዓት እንዲሁም "ባልቻ አባነፍሶ" እሁድ በ8:00 ሰዓት የሚታዩ ሲሆን ትኬቱን በኦንላይን የክፍያ ስርዓት መቁረጥ እንደሚቻል ተጠቁሟል፡፡

ቦሌ ፍላሚንጎ በህፃናትና ወጣቶች የቴአትርና ሲኒማ ኮምፕሌክስ እሁድ ጠዋት 4፡00 ሰዓት "የንባብ ከተማ" የተሰኘው የልጆች ቴአትር ለእይታ ይበቃል፡፡ እሁድ በ8፡00 ሰዓት "ወህኒ አምባ"፣ በ11፡30 ሰዓት ደግሞ "አትጥሪኝ" የተሰኑ ቴአትሮች ለተመልካች ይደርሳሉ።

እንዲሁም በሀገር ፍቅር ቴአትር ረዕቡ በ11፡00 ሰዓት "አሉ"፣ ሐሙስ 11፡30 ሰዓት "ነገሩ አይቆምም"፣ እሑድ በ8፡00 ሰዓት "ሰዴታ" (በአፋን ኦሮሞ) እና በ12፡00 ሰዓት "የመጨረሻው ፍርድ" ለቴአትር አፍቃሪያን ይቀርባሉ፡፡

# የቁጥር ጨዋታ

## የባለፈው ሳምንት ጥያቄ መልስ

ውድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ አንባቢዎቻችን ባለፈው ሳምንት የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችሁ ነበር፡፡ የጥያቄው ትክክለኛ አሰራርና መልስ የሚከተለው ነው፡፡ ዲያግራሙ ላይ በአጠቃላይ አምስት ቁጥሮች አሉ፡፡ የመሃለኛውን ቁጥር ትተን በግራ በኩል ወደ ቁልቁል ያሉ ሶስቱ ቁጥሮች ለብቻ እንደምራለን፡፡ ከዚያ በቀኝ በኩል የቀሩት ሁለቱ ቁጥሮች እንደዚሁ እንደምራለን፡፡ ከዚያ በኋላ በቀኝ በኩል ያሉት የሁለቱ ድምር ውጤት ከመጀመሪያው ድምር ውጤት ላይ በመቀነስ ትክክለኛውን መልስ ማግኘት እንችላለን። በሌላ በኩል የመሀለኛውን ቁጥር መልስ እንዴት ማግኘት ይቻላል? የሚለውን ነው ምንመልሰው፡፡ በዚህ መሰረት የመጀመሪያው ዲያግራም መልስ፤ 6 + 11 + 2 = 19 ይሆናል፡፡ 5 + 4 = 9 ይሆናል፡፡ 19 – 9 = 10 ይሆናል፡፡ በዚህ አመክንዮ መሰረት የጥያቄው ትክክለኛ መልስ እንደሚከተለው ይሆናል፤ 11 + 3 + 14 = 28 ይሆናል። ከዚያ አስር ከስንት ቁጥር ጋር ብንደምረው ነው 18 የሚመጣው የሚለውን ለመመለስ በጥያቄው ምልክት ቦታ መግባት ያለበት 0 ይሆናል፡፡ 10 + 0 = 10 ይሆናል፡፡ በመጨረሻም 28 - 10 = 18 ይሆናል፡፡ በዚህ መሰረት የጥያቄው ትክክለኛ መልስ **0** ይሆናል፡፡




## የዚህ ሳምንት የቁጥር ጨዋታ

ውድ አንባቢዎቻችን ከታች በምስሉ ላይ የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችኋል፡፡ በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛው ቁጥር ስንት ነው? በጥያቄው ራስዎን እየፈተኑ ይዝናኑ፡፡ የጥያቄውን መልስ በቀጣይ ሳምንት ዕትማችን ይዘን እንቀርባለን፡፡



# የባህል አልባሳቱ መታያ መድረክ

**በደረጀ ታደሰ እና አብርሃም ገብሬ**



ፎቶ፦ ከገጸ ድር
በበዓሉ ከሚለበሱ አልባሳት መካከል ጥቂቶቹ

ኢትዮጵያ፤ ሕብረ ብሔራዊት ሀገር ነች፡፡ በርካታ ቋንቋዎች፣ ባህሎች፣ ዕምነቶች፣ ልምዶች፣ እሴቶች ... ያሏቸው ሕዝቦች በጋራ እና በአንድነት ለዘመናት የኖሩባት፤ እየኖሩባት የምትገኝም ነች። ብዝሃነት ለኢትዮጵያ ጌጧ፣ ውበቷ፣ ጥንካሬዋ፣ ድምቀቷ፣ ኃይሏ ነው። የብዝሃነትን (ሕብረ ብሔራዊነትን) ጥቅም በብዙ መልኩ እየተነተኑ ለመመልከት መሞከር "አባይን በጭልፋ" ዓይነት ይሆናል፡፡ እናም የሕብረ ብሔራዊነት መገለጫዎች መካከል፡- የባሕል አልባሳትን፣ በተለይም በየዓመቱ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያን በሚታደሙበት የኢሬቻ በዓል ላይ፣ ደምቀውና ተውበው ስለሚታዩበት አልባሳት እና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ለመዳሰስ እንሞክራለን፡፡

ከሰሞኑ በአዲስ አበባ ትልቁ የባህል ልብስ መገበያያ ማዕከል ወደሆነው ሽሮሜዳ አቅንተን ነበር፡፡ ከወርሃ ነሐሴ አጋማሽ ጀምሮ በመስከረም እና ከዚያም በኋላ ባሉት ጥቂት ወራት ውስጥ የሽሮሜዳ የንግድ እንቅስቃሴ በጣም ከፍ የሚልበት ወቅት እንደሆነ፣ በባህል ልብስ ንግድ ሥራ ላይ የተሠማሩ ነጋዴዎች መስክረዋል፡፡ የዝግጅት ክፍላችን ካነጋገራቸው የሽሮሜዳ ነጋዴዎች መካከል አቶ መስፍን በዳዳ አንዱ ናቸው፡፡ ከሱቃቸው ተሰይመው፣ ገዢዎቻቸውን እያስተናገዱ ባሉበት ወቅት ነው ያገኘናቸው፡፡ ከሱቃቸው እንደደረስን የጀመሩትን ግብይት እስኪያጠናቅቁ እየጠበቅን የሱቃቸውን ዙሪያ መለስ መቃኘት ጀመርን፡፡ ሀገርን በአልባሳት ሕያው አድርጎ የሚያሳይ ሙዚየም ይመስላል፡፡ የአልባሳቱ በጥበብ የተገለጸ ውበትን፣ በቀለማት ሕብረት መሰናሰል የተፈጠረ ማራኪነትን፣ በሀገር በቀል አልባሳቱ የሚገለጽ ማንነትን... በተመስጦ እየተመለከትን ቆየን፡፡ ከዚያም ነጋዴው ፋታ ሲያገኙ ወደሳቸው አቀናን። ስለመጣንበት ጉዳይም አሳውቀን፣ መቅረጸ ድምጻችንን ከፍተን ሃሳብና መረጃ ተለዋወጥን፡፡

የባሕል አልባሳት ንግድ ሥራ ከፍና ዝቅ ማለት ከወቅት ጋር ስለመያያዙ በመጥቀስ ሃሳባቸውን ማጋራት የጀመሩት አቶ መስፍን፤ በተለይ ከነሐሴ አጋማሽ ጀምሮ እስከ መስከረም መጨረሻ ድረስ ያለው ጊዜ ለሽሮሜዳ ነጋዴዎች ጥሩ ወቅት መሆኑን አንስተዋል፡፡ የዚህንም ምክንያት ሲያነሱ፤ "ከነሐሴ አጋማሽ ጀምሮ እስከ መስከረም መጨረሻ ድረስ ብዙ በዓላት አሉ፡፡ የእኛ ሰው ደግሞ የባሕል ልብስ ገዝቶ የሚለብሰው በአብዛኛው በዓላት ሲኖሩ ወይም ለሰርግ ነው፡፡ ስለዚህ እኛ ነጋዴዎች ወቅትን መሰረት በማድረግ አስፈላጊ የሆኑ ልብሶችን በተለያየ ዲዛይን እናዘጋጃለን። ለአዲስ ዓመት፣ ለመስቀል ደመራ፣ ለኢሬቻ ሊለበሱ የሚችሉ ልብሶችን እናቀርባለን፡፡ ልብሶቹን መጥተው ሱቅ ከሚገዙ ሰዎች በተጨማሪ፣ ለነባር እና አዳዲስ ደንበኞቻችን በትዕዛዝ ተቀብለን እንሠራለን፡፡ በዚህም የተሻለ ገቢ እናገኛለን፡፡"

ጥቁር፣ ቀይ እና ቀይ-ቡናማ ቀለማት (የገዳ ሥርዓት ቀለማት) በጉልህ የሚታዩባቸው እና በተለያየ ዲዛይን የተዘጋጁና ለኢሬቻ የሚለበሱ የባሕል አልባሳት የአቶ መስፍን ዲባባን ሱቅ ጨምሮ በሽሮሜዳ በሚገኙ የባሕል አልባሳት መሸጫ ሱቆች ውስጥ ተመልክተናል፡፡ ወይዘሮ ጤናዬ ታዬ፣ በሽሮሜዳ ካለው የባሕል ልብስ መሸጫ ሱቃቸው የኢሬቻ በዓልን ጨምሮ ወቅትን ያገናዘበ የባሕል አልባሳትን ለገበያ አቅርበዋል፡፡ እሳቸውንም በወርሃ መስከረም የሚከወኑ እንደ ኢሬቻ ያሉ ሕዝባዊ በዓላት፣ ለንግድ ሥራቸው ምን ዕድል ይዞ እንደሚመጣ የጠየቅናቸው ሲሆን፤ ከአቶ መስፍን በዳዳ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ሃሳብ አጋርተውናል። "የባሕል ልብስ ገበያ ወቅታዊ ነው፡፡ ተጠቃሚው እንደ ዘይት፣ ጤፍ፣ ልብስ ሁልጊዜ አይገዛም፡፡ በተለይ የባሕል ልብስ ሲሆን ወቅትን ይጠብቃል። መስከረም ለባሕል ልብስ ነጋዴዎች በጣም የተሻለ ጊዜ ነው፡፡ ምክንያቱም ኢሬቻን ጨምሮ አዲስ ዓመት፣ መስቀል በዚህ ወር ነው የሚከበሩት፡፡ እኛም ይህንን ታሳቢ በማድረግ እንዘጋጃለን፡፡ በግል እና በቡድን ከሚመጡ ደንበኞች በሚፈልጉት ዲዛይንና ጥራት ትዕዛዝ ተቀብለን እንሠራለን፡፡"

በኢሬቻ ላይ የሚለበሱ የኦሮሞ ባህላዊ አልባሳት ከተፈጥሮ ጥጥ በእጅ የተሸመኑ ሲሆኑ፣ ነጭ ቀለም የበዛባቸው እና በዳርቻቸው ላይ ጥቁር፣ ቀይ እና ቀይ-ቡናማ ቀለማት (የገዳ ሥርዓት ቀለማት) በስፋት የሚታይባቸው ናቸው። በዓሉ የክረምት ማብቂያና የለመለመው መስከረም መባቻ በመሆኑ አልባሳቱ የተፈጥሮን ውበትና ሕይወትን ያንጸባርቃሉ። ከዚህ ጋር በተያያዘ በወለጋ ዩኒቨርሲቲ የፎክሎር መምህርና ተመራማሪ ግርማ በቀለ (ዶ/ር) ምሁራዊ ማብራሪያ ሰጥተውናል፡፡

እንደ ግርማ (ዶ/ር) ገለጻ፤ ለኢሬቻ በዓል የሚለበሱ አልባሳት በዋናነት የሴቶች እና የወንዶች ተብለው በሁለት ይከፈላሉ፡፡ ለሴቶች የሚዘጋጀው የባሕል ልብስ ወንደቦ ይባላል፡፡ ወንደቦ፡- ረጅም ቀሚስ ሆኖ፣ በደረት፣ በወገብ እና በታችኛው ዳርቻ ላይ ውብ እና ደማቅ የጥልፍ ሥራዎች ተካትተውበት የሚዘጋጅ እጅግ ማራኪ እና የተከበረ ልብስ ነው። ይህ ልብስ በባህላዊ መንገድ በእጅ ከተሸመነ "ቡልኮ" ወይም "ጋቢ" መሳይ ለስላሳ የጥጥ ጨርቅ የሚሰራ ሲሆን፣ በላዩ ላይ የሚሰሩት ጥልፎች የኦሮሞን ባህላዊ ምልክቶች (እንደ ኦዳ ዛፍ) ያሳያሉ። በተመሳሳይ፤ የወንዶች ባህላዊ ልብስ በኢሬቻ በዓል ላይ በስፋት ይለበሳል፡፡ በወንዶች ከሚለበሱ የባሕል አልባሳት መካከል፡- ጎንፋ ይጠቀሳል፡፡ ይህ የባሕል ልብስ ወንዶች በትከሻቸው ላይ የሚደርቡት እና እንደ ካባ የሚያገለግል፣ ከፍተኛ ክብርንና ባለሥልጣንነትን (በተለይ የገዳ መሪዎችን ወይም የሀገር ሽማግሌዎችን) የሚያሳይ ነው። ከዚህ በተጨማሪም የበዓሉን ትርጉም እና እሴት ሳይለቁ በተለያየ ዲዛይን ተሠርተው የሚለበሱም አሉ። አሁን አሁን እንደዚህ ዓይነቱ ልምድ በወጣቱ ዘንድ በስፋት እየተስተዋለ ይገኛል፡፡

ሌላኛው አስተያየት ሰጪ የባህል አልባሳት ዲዛይነርና ሻጭ ፀጋዬ ስሜነህ ነው፡፡ መርካቶ ሸማ ተራ ውስጥ ለዓመታት የባህል አልባሳት ሰርቷል። አሁን ላይ ቀጨኔ መድኃኒዓለም ቤተ ክርስቲያን አካባቢ የባህል አልባሳት ዲዛይን ያደርጋል፡፡ ዲዛይን ያደረጋቸውን ልብሶች ለለባሽ ብቻ ሳይሆን የባህል አልባሳት ለሚሸጡ ሱቆች ጭምር በጅምላ ይሸጣል፡፡

ዲዛይነር ፀጋዬ "መስከረም ወር ለእኛ ለባህል ልብስ ዲዛይነሮችና ሻጮች እጅግ የተመቸ ወር ነው፡፡ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በአዲስ አበባ በድምቀት መከበር የጀመረው የኢሬቻ በዓል በዚህ ረገድ ለሀገር ባህል አልባሳት ዲዛይነሮችና ሻጮች ተጨማሪ ገቢ እንዲያገኙ አስችሏል፡፡" ሲል ለአዲስ ልሳን ዝግጅት ክፍል ሃሳቡን አጋርቷል፡፡

ኢሬቻን ለማክበር በቡድንና በተናጠል በመሆን የባህል አልባሳት ለብሶ መታየት እየተለመደ መምጣቱን በማስታወስ፣ የባህል አልባሳት ተፈላጊነታቸው እጅግ ጨምሯል፡፡ እንደ አንድ ዲዛይነር የኢሬቻን ትውፊት የሚያጎሉ፣ የኦሮሞን ሕዝብ ዕሴት የሚያሳዩና ለዘመኑ ወጣት የቀረቡ ልብሶችን ለመስራት ከፍተኛ ጥረት አደርጋለሁ፡፡ ከምንም በላይ ለደንበኞቼ የባህል አልባሳት ምርጫቸው እንዳይገደብ በተለያዩ ጥለቶችና ዲዛይኖች ባህሉን በጠበቀ መልኩ እሰራለሁ፡፡ አምና እና ካቻምና ለኢሬቻ የሚሆን የባህል ልብስ ዲዛይን አድርጌ የሸጥኩላቸው ወጣቶች፣ ለዚህኛው ለ2019 ዓ.ም የኢሬቻ በዓል ለየት ያለ ልብስ እንዲሰራላቸው አስቀድመው አዝዘውታል፡፡ ከዚህ አንጻር በዓሉ ተጨማሪ የገቢ ምንጭ እየፈጠረላቸው መሆኑን ተናግሯል፡፡

እንደ ዲዛይነር ጸጋዬ ገለጻ፣ የባህል አልባሳት ስራ በዓላት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ የሆኑ ወራት ላይ የባህል አልባሳት ሥራ ይቀዛቀዛል፡፡ ከዚህ አንጻር እንደ መስከረም ባሉ በዓል በሚበዛባቸው

ወደ ገጽ 21 ዞሯል

# ‘ሴራ ደገላ’ እና ‘ሴራ መልካ’ ለሥነ-ምህዳር ጥበቃ

• የገዳ ሥርዓት ለሥነ-ምህዳር ጥበቃ ትልቅ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት ተገልጿል

በቶለሳ መብራቴ



ፎቶ፦ ከገፀ ድር
የገዳ ስርዓት ለተፈጥሮ ጥበቃ ያለው ጥብቅ እሳቤ የኢሬቻ በዓል በውብ እና ለምለም ስፍራዎች እንዲከበር አስችሏል

የገዳ ሥርዓት ከተፈጥሮ ጋር ያለው ግንኙነት በቀላል የአካባቢ ጥበቃ ልምድ የሚገለጽ ሳይሆን፣ የጠለቀ ሥነ-ፍጥረታዊ ፍልስፍና፣ የሕግ ሥርዓት እና የማኅበረሰብ የአኗኗር ዘይቤ አካል ነው። በገዳ ስርዓት ውስጥ ሰው፣ ተፈጥሮ እና ፈጣሪ (ዋቃ) የማይነጠሉ የአንድ ሁለንተናዊ ሥርዓት አካላት ናቸው። የዚህ አመለካከት ዋና ምሰሶ ‘ሰፉ’ (Safuu) የሚለው የሞራል እና የሕግ ድንበር ሲሆን፣ በሰው እና በተፈጥሮ መካከል ፍጹም የሆነ ክብር፣ ሚዛን እና ስምምነት ሊኖር እንደሚገባ ያዝዛል። ሰው የተፈጥሮ የበላይ ወይም አዛዥ ሳይሆን ከተፈጥሮ ጋር አብሮ የሚኖር የሕይወት አካል በመሆኑ ተፈጥሮን ማበላሸት ፈጣሪ የዘረጋውን ሁለንተናዊ ሚዛን እንደ ማፍረስ ይቆጠራል።

የኦሮሞ ሕዝብ የዘመናት ባህላዊ፣ ማኅበራዊ፣ ሥነ-ሕጋዊና ፖለቲካዊ መዋቅር የሆነው የገዳ ሥርዓት ከሰብዓዊ መብቶችና አስተዳደራዊ መመሪያዎች ባሻገር፣ ከአካባቢና ተፈጥሮ ጥበቃ ጋር የተቆራኘ ጥልቅ ፍልስፍናዊ መሠረት ያለው ጥንታዊ የሀገር በቀል እውቀት ሥርዓት ነው። በዚሁ መሠረት በገዳ መዋቅር ውስጥ ያሉ እያንዳንዱ የዕድሜ ክፍሎች በተፈጥሮ ጥበቃ፣ በደን እንክብካቤ፣ በውኃ አካላት አያያዝ እና በሁለንተናዊ የሥነ-ምህዳር ሚዛን ጥበቃ ላይ የየራሳቸው የተወሰኑ ድርሻዎችና ኃላፊነቶች ተጥለውባቸዋል።

በገዳ ሥርዓት ውስጥ የሰው ልጅ እና ተፈጥሮ ተነጣጥለው የሚታዩ ፍጥረታት አይደሉም፤ ይልቁንም የሰው ልጅ ሕልውና ሙሉ በሙሉ ከተፈጥሮ ሀብቶች ጋር የተሳሰረና ተፈጥሮም የሕይወት ሁሉ ምንጭ እንደሆነች ይታመናል። ይህ አስተሳሰብ ‘ሰፉ’ (Safuu) በሚለው ማኅበራዊና መንፈሳዊ ሥነ-ምግባራዊ ሕግ ይመራል። ሰፉ በፈጣሪ (ዋቃ)፣ በሰው ልጅና በተፈጥሮ መካከል ሊኖር የሚገባውን ትክክለኛ ሚዛን፣ ክብርና ሥርዓት የሚያመለክት ሰፊ ጽንሰ-ሀሳብ ነው። ተፈጥሮን መንከባከብ ለሰው ልጅ እንደ ስጦታ የተሰጠ መለኮታዊና ማኅበራዊ ኃላፊነት እንጂ በሥልጣን የሚወሰን ተራ ምርጫ አይደለም።

በገዳ ሥርዓት እይታ ዕፅዋት፣ እንስሳትና ውሃማ አካላት የሰው ልጅ በምድር ላይ ለመኖርና የመኖር ሕልውናውን ለማስቀጠል ወሳኝ የሆኑ መሠረታዊ ሀብቶች ናቸው። የእነዚህ ሀብቶች መደፍረስ ወይም መጎዳት በቀጥታ የሰው ልጅን ሕይወትና ማኅበራዊ መረጋጋት ለአደጋ ይዳርጋል። ስለሆነም በገዳ ስርዓት ውስጥ ለእነዚህ ሦስት የተፈጥሮ ምሰሶዎች ልዩ ጥበቃና ክብር ይሰጣቸዋል። በገዳ ሥርዓት ውስጥ ዛፎችና ደኖች የምግብና ጥላ ምንጭ ከመሆናቸውም በላይ ትልቅ መንፈሳዊና ማኅበራዊ ማዕከል ናቸው። በተለይም “ኦዳ” (Odaa) የተባለው የዛፍ ዓይነት የሰላም፣ የፍትሕና የገዳ ጉባኤዎች የሚካሄዱበት ቅዱስ ምልክት ተደርጎ ይታያል። በእንዲህ ያሉ ዛፎች ሥር የሚደረጉ ጉባኤዎች ተፈጥሮን ማዕከል ያደረገ ውሳኔ የሚሰጥባቸው በመሆናቸው፣ አባ ገዳዎችና ማኅበረሰቡ በእነዚህ ቦታዎች ላይ ዛፍ መቁረጥን፣ ደንን ማጥፋትንና የደን ቃጠሎን ሙሉ በሙሉ ይከለክላሉ።

ፕሮፌሰር ወርቅነህ ቀልቤሳ ‘ሀገር በቀል እውቀትና የአካባቢ ጥበቃ ሥነ-ምግባር’ በሚል ጥናታዊ ጽሑፋቸው እንዳመለከቱት፤ የገዳ ሥርዓት ዛሬ ዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ የሚታገልበትን የከባቢ አየር ለውጥና የሥነ-ምህዳር መበላሸት ችግሮች በቅድመ-ኢንዱስትሪ ዘመን ምላሽ ለመስጠት የቻለ ድቅድቅ የሀገር በቀል እውቀት ማሳያ ነው። ሰው ከምድርና ከተፈጥሮ አካላት የተገኘ ፍጡር በመሆኑ፣ የሕይወቱ ዘላቂነት የሚረጋገጠው ተፈጥሮን በጥንቃቄና በክብር ሲይዝ ብቻ እንደሆነ በገዳ ሥርዓት ውስጥ ድንጋጌ እንዳለው ጥናቱ ያስረዳል።

በተመሳሳይ መልኩ፣ በእንስሳትና በዱር አራዊት ጥበቃ ረገድ በገዳ ሥርዓት ውስጥ አራዊትና የቤት እንስሳት የራሳቸው መብትና የመኖር ድርሻ እንዳላቸው ይታመናል። እንስሳትን ያለ አግባብ ማሰቃየት፣ በእርግዝና ወይም በመራቢያ ወቅት ማደን እና የእንስሳት ግልገሎችን መግደል በጥብቅ የተከለከለ ነው። የዱር አራዊት የአካባቢውና የሥነ-ምህዳሩ አካል እንደሆኑ ተደርገው ስለሚወሰዱ፣ የመኖሪያ አካባቢያቸው እንዳይጠፋ ጥበቃ ይደረግለታል። ይህ የአደንና የእንስሳት ጥበቃ ሕግ በኦሮሞ ማኅበራዊ ሕግ ውስጥ የብዝሃ-ሕይወትን ሚዛን ለመጠበቅ የተዘረጋ ድንቅ ዘዴ እንደሆነ ተመራማሪዎች ይገልጻሉ።

በተመሳሳይ ውሃ የሕይወት ሁሉ ምንጭና ጥራቱ ተጠብቆ ሊኖረው የሚገባ ንጹሕ የተፈጥሮ ስጦታ ተደርጎ ይወሰዳል። ወንዞች፣ ምንጮች እና ሐይቆች በገዳ ሥርዓት ውስጥ ፈጣሪ የሰጠው የሕይወት ደም ሥር እንደሆኑ ይቆጠራሉ። በውሃ አካላት አቅራቢያ የሚገኙ አትክልቶችን ማጥፋት፣ ወንዞችና ምንጮች ዘንድ ቆሻሻ መጣል፣ ወይም ውሃን ማደፍረስ በገዳ ስርዓት ትልቅ ወንጀልና ኃጢአት ተደርጎ ይቆጠራል። ወንዝ ወይም “መልካ” ተብለው የሚጠሩት የወንዝ መሻገሪያዎችና የውሃ ስፍራዎች በቅዱስነታቸው የሚታወቁና ለተለያዩ ሥነ-ሥርዓቶች የሚገለገሉባቸው በመሆናቸው ሁልጊዜም ንጹሕና ተፈጥሯዊ ገጽታቸውን ጠብቀው እንዲቆዩ ይደረጋል።

በጂማ ዩኒቨርሲቲ የታሪክ መምህርና ተመራማሪ ዴሬሳ ዴቡ (ዶ/ር) ከዝግጅት ክፍላችን ጋር በነበራቸው ቆይታ እንደገለጹት፤ በገዳ ሥርዓት የተፈጥሮ ጥበቃ በምኞት ወይም በባህላዊ ምክር ብቻ የሚተው ሳይሆን፣ ግልጽ በሆኑ ሕጎችና የቅጣት ደንቦች የተደገፈ ነው። በገዳ ጉባኤ ከሚወጡ ሕጎች መካከል “ሴራ ደጋላ” (Seera Daggalaa - የደን ሕግ) እና “ሴራ መልካ” (Seera Malkaa - የመልካ ሕግ) ዋና ዋናዎቹ ናቸው። ሴራ ደጋላ ትልልቅና ጥንታዊ ዛፎችን መቁረጥና የደን ቃጠሎ ማድረስን የሚከለክል ሲሆን፣ ይህን ሕግ የጣሰ ሰው በገዳ አባቶች ውሳኔ ማኅበራዊ ማግለልና የገንዘብ ወይም የእንስሳት ቅጣት ይጣልበታል። በተጨማሪም ሕፃናት ገና ከልጅነታቸው ጀምሮ ዛፍ እንዳይቆርጡና ውሃ እንዳይበክሉ በሰፉ መርህ ኮትኩቶ ማሳደግ የሕብረተሰቡ ውስጣዊ የቁጥጥር ሥርዓት መሠረት ነው።

የገዳ ሥርዓት የተፈጥሮ ጥበቃ አስተሳሰብ በተግባር ከሚገለጥባቸው ትልልቅና ደማቅ አገራዊና ባህላዊ በዓላት መካከል የኢሬቻ ሥነ-ሥርዓት ዋናው ማሳያ ነው። ኢሬቻ የኦሮሞ ሕዝብ ለፈጣሪው (ዋቃ) የሚያቀርበው የምስጋናና የሰላም በዓል ሲሆን፣ የክረምቱ ጭጋግማና ጨለማ አልፎ፣ ምድር በለምለምና በተፈጥሮ ውበት ተሸልማ ለምትወጣበት አዲስ ወቅት የሚደረግ ታላቅ ሥነ-ሥርዓት ነው። የኢሬቻ በዓል የሚከበረው በህንጻዎች ወይም በአዳራሾች ውስጥ ሳይሆን፣ በተፈጥሮ ክፍት ቦታዎች፣ በሐይቆች ዳርቻ (እንደ ሆራ ሀርሰዲ እና ሆራ ፊንፊኔ)፣ በወንዞች (መልካ) አካባቢ ሲሆን፣ ይህ እንዲቀጥል ተፈጥሮን መጠበቅ ግዴታ መሆኑን ዴሬሳ (ዶ/ር) አስገንዝበዋል።

በበዓሉ ወቅት ሰዎች አረንጓዴ ሣር (Coqorsa) እና አበቦችን በእጃቸው ይዘው ወደ ውሃ አካላት በማመራት ለፈጣሪያቸው ምስጋና ያቀርባሉ፤ ውሃውንና አካባቢውን ይባርካሉ። ይህ ሥነ-ሥርዓት በከፍተኛ ተፈጥሯዊ ለዛና ውበት እንዲከበር ያስቻለው በገዳ ሥርዓት አማካይነት ቀደም ሲል ተፈጥሮ ተጠብቃ በመቆየቷ ነው። የኢሬቻ በዓል የሚከበርባቸው ሆራዎችና መልካዎች ዓመቱን በሙሉ ከአፈር መሸርሸር፣ ከቆሻሻ ብክለትና ከደን ጭፍጨፋ ተጠብቀው እንዲቆዩ የገዳ ሥርዓቱ እንደሚያዝ የታሪክ ምሁሩ ተናግረዋል።

ሰዎች ሣርና አበባ ይዘው ውሃውን ሲነከሩ፣ ተፈጥሮ የፈጣሪ ታላቅ ሥራ መሆኗንና የሰው ልጅ የዚህ ተፈጥሮ አካል መሆኑን ለማረጋገጥ ነው። ስለሆነም ኢሬቻ በዓል ብቻ ሳይሆን፣ ዓመታዊ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃን የሚያድስ፣ የሰው ልጅ ከተፈጥሮ ጋር ያለውን ቁርኝት የሚያጠናክር እና ለቀጣዩ ትውልድ የአካባቢ ጥበቃን መልእክት የሚያስተላልፍበት ሕያው አካባቢ-ተኮር ባህል ነው።

ዴሬሳ (ዶ/ር) እንደገለጹት፤ በአሁኑ ወቅት ዓለማችን በካርቦን ልቀት መጨመር፣ በደን መጨፍጨፍ፣ በብዝሃ-ሕይወት መጥፋት እና በዓለም አቀፍ የሙቀት መጨመር ሳቢያ ከፍተኛ ሥነ-ምህዳራዊ ውጥረት ውስጥ ትገኛለች። የመንግሥታት ፖሊሲዎችና ዓለም አቀፍ ስምምነቶች አካባቢን ለመጠበቅ የተለያዩ ሕጎችን ቢያወጡም፣ ማኅበረሰብ-አቀፍና ባህላዊ መሠረት በመጎደላቸው የሚፈለገውን ያህል ስኬት ለማስመዝገብ ሲቸገሩ ይስተዋላል። በዚህ ረገድ የገዳ ሥርዓት ሀገር በቀል የአካባቢ ጥበቃ ፍልስፍና ለዘመናዊው ዓለም ትልቅ ትምህርት ይሰጣል።

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የትምህርት፣ የሳይንስ እና የባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) በፈረንጆቹ 2016 የገዳ ሥርዓትን የማይጨበጥ የዓለም አቀፍ የሰው ልጅ ባህላዊ ቅርሳ ቅርሶች መዝገብ ውስጥ የመዘገበበት አንደኛውና ዋናው ምክንያት ይህ ሥርዓት ለሰብአዊ መብቶች፣ ለዲሞክራሲ፣ ለሰላም እና ለተፈጥሮ ጥበቃ የሚሰጠው የላቀና ዘላቂ መዋቅራዊ አስተዋፅኦ በመሆኑ ነው። የገዳ ሥርዓት የሚያስተምረን ተፈጥሮን መጠበቅ የሕግ አስገዳጅነት ብቻ ሳይሆን፣ የውስጣዊ ሥነ-ምግባርና የማኅበራዊ ሕልውና ጉዳይ እንደሆነ ነው። ይህ አቀራረብ በአፍሪካና በሌሎች የዓለም ክፍሎች ዘላቂ የልማት ግቦችን በተለይም የካርቦን ቅነሳንና የምድር ላይ ሕይወት ጥበቃን ለማሳካት አጋዥ የሆኑ የሀገር በቀል እውቀቶችን አጠቃቀም የሚያሳይ ጥሩ ሞዴል እንደሆነ የዩኔስኮ መረጃ ያመላክታል።

የገዳ ሥርዓት የሰው ልጅ ከምድርና ከተፈጥሮ የተገኘ ፍጡር መሆኑን በመገንዘብ፣ የሕይወቱ ምንጭና መሠረት የሆኑትን ዕፅዋት፣ እንስሳትና ውሃማ አካላት በጥብቅ ሕግና ሥነ-ምግባር (ሰፉ) ሲጠብቅ የኖረ አጠቃላይ የተፈጥሮ ጥበቃ ሥርዓት ነው። የገዳ ሥርዓት ቀደም ብሎ የጣላቸው ጥብቅ የተፈጥሮ ጥበቃ ድንጋጌዎችና ማኅበራዊ እሴቶች አካባቢው ሳይደፈረስ፣ የሥነ-ምህዳር ሚዛኑ ሳይዛባ እና ውበቱ ሳይጠፋ ለትውልድ እንዲሸጋገር አድርገዋል።

ይህ አስቀድሞ የተደረገ የተፈጥሮ ጥበቃ ጥረት ደግሞ የኢሬቻ ሥነ-ሥርዓት በየዓመቱ በሆራዎች፣ በወንዞችና በታላላቅ አረንጓዴ ቦታዎች ላይ ባማረና በተፈጥሯዊ ለዛ እንዲከበር መሠረት ሆኗል። በመሆኑም የገዳ ሥርዓት ሀገር በቀል ጥበቃ ፍልስፍናን ከዘመናዊ የአካባቢ ጥበቃ ሳይንስና ፖሊሲዎች ጋር በማቀናጀት ለዓለማችን የአየር ንብረት ለውጥ መፍትሔ አድርጎ መጠቀም እንደሚያስፈልግ የታሪክ ምሁሩ አሳስበዋል።


SIKET BANK
Baga Ayyaana Irreecha
Hora Finfinnee fi Hora Harsadee
nagaan geessan!
Ayyaana Gaarii!
እንኳን ለሆረ ፊንፊኔ እና ሆረ ሃርሰዴ
የኢሬቻ በዓል በሰላም አደረሳችሁ!
መልካም በዓል!
www.siketbank.com
8342
THE BASIS OF YOUR SUCCESS!
SWIFT
SSHCETAA


ቡና ባንክ
BUNNA BANK
Bank of the Visionaries!
Baga Ayyaana Irreechaa
bara 2019 Geessan
IRREECHAA
www.bunnabanksc.com
VISIT OUR WEBSITE
Call
Now
8501

# ልጆች፣ ስለኢሬቻ እሴቶች ምን ያህል ታውቃላችሁ?

**በፋንታነሽ ተፈራ**

ልጆች፤ እንዴት ናችሁ? ኢሬቻ በኦሮሞ ህዝብ ዘንድ በታላቅ ድምቀት የሚከበር በዓል ነው፡፡ ይህን መነሻ በማድረግ ስለበዓሉ ምንነት፣ የልጆች ተሳትፎ እና ከእሴቱ እናንተ ልጆች ምን ልትማሩ እንደሚገባ ያነጋገርናቸው አባገዳ ሀሳባቸውን እንደሚከተለው አስተላልፈውላችኋል፡፡

አባገዳ ፈቃዱ ወንድሙ እባላለሁ። የፊኒፊኔ ቱለማ አባገዳዎች የጽህፈት ቤትና የግቢ ኃላፊ ነኝ፡፡ ኢሬቻ የኦሮሞ ሕዝብ ከዘመን ወደ ዘመን በሰላም ላሸጋገረው ፈጣሪ ምስጋና የሚያቀርብበት ታላቅ የምስጋና በዓል ነው፡፡ በዚህ በዓል ላይም የተለያዩ ባህሎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡



ፎቶ- ከገፀ ድር
የሆራ ፊንፊኔ በዓል አከባበር ከፊል ገፅታ

በበዓሉ ላይ ከሚታዩ የኦሮሞ ባህሎች አንዱ ምስጋና ማቅረብ ነው፡፡ በዓሉ በዋናነት ክረምቱ ወይም ጨለማው አልፎ ወደ ብርሃን በመሸጋገራችን፣ ዘመድና ዘመድ የሚገናኝበት በመሆኑ ፈጣሪን ማመስገኛ ወቅት ነው። "የሰላም ጊዜ አድርግልን፤ የሞላው ውሃ ጎድሎ ከቤተሰቦቻችን እንድንገናኝ ያደረግከን ፈጣሪ ምስጋና ይድረስህ" እየተባለ በዝናቡና በአፈሩ የበቀለውን ሳር በመያዝና ውሃውን በመርጨት ምስጋና ይቀርባል፡፡

ሌላኛው የበዓሉ እሴት እርቀ ሰላም ማውረድ ነው፡፡ ከኢሬቻ በዓል በፊት ሰዎች በተለያዩ ምክንያቶች እርስ በርሳቸው ሊቀያየሙ፣ ላይስማሙ ይችላሉ፡፡ በኢሬቻ በዓል ግን ሽማግሌዎች ተሰባስበው ይቅር እንዲባባሉ ይደረጋል፡፡ በዓሉ የሚከበረውም ከታረቁ በኋላ ነው፡፡ ቂም ይዞ በዓሉን ማክበር አይቻልም፡፡

ልጆች እናንተም የበዓሉን እሴቶች በሚገባ አውቃችሁ እና ተረድታችሁ ተግባራዊ ብታደርጉ በብዙ ትጠቀማላች።

ልጆች እናንተም ከጓደኞቻችሁ ጋር ተስማምታችሁ ኑሩ፤ ፈጣሪያችሁንም አመስጋኝ ሁኑ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ አብሮ የመኖር ልምድን አዳብሩ፡፡ ታላላቆቻችሁን አክብሩ፣ በሁሉም ነገር ቅድሚያ ስጡ። ይህ ሲሆን እናንተም መወደድና መከበርን ታተርፉላችሁ፡፡ ደስታም በውስጣችሁ ይሰፍናል፡፡ በሀገራችን ያሉ በዓላትን በአግባቡ እወቁ፣ አክብሩ፡፡

በበዓሉ ያሉ እሴቶችን መተግበር ለእናንተም፣ ለቤተሰብ፣ ለማህበረሰም ሆነ ለሀገር ፋይዳው ትልቅ ነው፡፡ ከዚህ ለመጠቀም ደግሞ በአግባቡ ማወቅና ተግባራዊ ማድረግ ከእናንተ ከልጆች ይጠበቃል እያልኩ መልካም የኢሬቻ በዓል እንዲሆንላችሁ መልዕክቴን አስተላልፋለሁ።

## ከገዳ ሥርዓት የሚመነጨው የእርቅ እና የሰላም መገለጫ ኢሬቻ





ኢትዮጵያ የዓለም ቅርሶች በዩኔስኮ በማስመዝገብ በአፍሪካ ቀዳሚዋ ሀገር ነች። እነዚህም በባህላዊ እና በተፈጥሮ ቅርሶች የተከፈሉ ናቸው፡፡

ከባህላዊ ቅርሶች ውስጥ ረቂቅ የሰው ልጅ የባህል ቅርሶች (Intangible Cultural Heritage) መካከል የገዳ ስርዓት አንዱ ነው፡፡ በ2009 ዓ.ም በዩኔስኮ የተመዘገበው የገዳ ስርዓት የኦሮሞ ህዝብ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ እና የማህበራዊ ህይወቱን ለዘመናት የመራበት ጥንታዊና ዲሞክራሲያዊ የአስተዳደር ስርዓት ነው።

የኢሬቻ በዓል ደግሞ ከገዳ ሥርዓት የሚመነጭ የእርቅ እና የሰላም መገለጫ ነው፡፡ ኢሬቻ በተለምዶ የኦሮሞ ህዝቦች ብሔራዊ የምስጋና ቀን ነው፡፡ በኦሮሞ ህዝቦች ዘንድ በድምቀት የሚከበር ቱባ የኢትዮጵያ ባህላዊ ክበረ በዓልም ነው።

ኢሬቻ ስላለፈው ዓመት በረከት ፣ ምሕረትና ሰላማዊ የወቅቶች ሽግግር ለዋቃ(ፈጣሪ) ምስጋና የሚቀርብበት ዕለት ብቻ ሳይሆን ፤ አዲሱ ዓመት የተሻለ እና የላቀ ምህረት እና በረከት ይዞ እንዲመጣ ፈጣሪ በአንድ ልብ የሚለምንበት ዕለት ነው፡፡

የዘንድሮው ሆራ ፊንፊኔ ዛሬ እየተከበረ ሲሆን፤ ነገ ደግሞ ሆራ አርሰዲ በቢሾፍቱ ይከበራል፡፡

የኢሬቻ በዓል አከባበር የተባበሩት መንግስታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) ለማስመዝገብ የተለያዩ ስራዎች እየተሰሩ መሆኑን መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

የተለያዩ የመረጃ ምንጮች

## 10 ልዩነቶችን ፈልጉ



## እንቆቅልሽ

### ያለፈው ሳምንት ጥያቄ

**ሲወለድ የሚጠቁር፤ ሲያረጅ የሚቀላ**

**መልስ፡-** ለ. በርበሬ

### የዚህ ሳምንት ጥያቄ

**እግሩ አንድ ጭቅላቱ ሦስት ?**

ሀ. ዶማ

ለ. ቀንበር

ሐ.መንሽ

**ልጆች፤ መልሱን ከጓደኞቻችሁ እና ከቤተሰቦቻችሁ ጋር ተወያዩበት።**

# የባንዳነት መልክና የኢትዮጵያውያን ብርቱ ክንድ

- ሕዝቡ ለውጭ ጠላቶች የሚገዙ ባንዳዎችን አሰላለፍና ግብ ከመረዳት አልፎ ተግባራዊ ምላሽ መስጠት እንዳለበት ተመላክቷል

**በመለሰ ተሰጋ**

‘ባንዳ’ የሚለው ቃል ጣሊያንኛ ሲሆን፣ ቀጥተኛ ፍቺው ‘ቡድን ወይም ስብስብ’ ማለት ነው፡፡ በኢትዮጵያ የታሪክና የፖለቲካ አውድ ግን “ከወራሪ ኃይል ጋር የተባበረ” የሚል አሉታዊ ትርጉም ይዟል። በተለይም እ.ኤ.አ ከ1935 እስከ 1941 በነበረው የጣሊያን ፋሺስት ወረራ ወቅት ከወራሪው ጋር የተሰለፉ፣ የአርበኞችን መረጃ አሳልፈው የሰጡና ለጠላት ቁሳዊ ድጋፍ ያቀረቡ አካላትን ለመግለጽ የዋለ ቃል ነው፡፡ ታዲያ እነዚህ ባንዳዎች ሀገር በጠላት ክንድ እንድትወድቅ ቢመኙም፣ እኩይ ተግባራቸው በታሪክ መዝገብ ላይ በውርደት ተመዝግቦ ይገኛል፡፡

በታሪክ መዝገብ ላይ ለሀገራቸው እስከ ደም ጠብታ ድረስ ከቆሙ ጀግኖች በታች ዝቅ ብለው ትውልድ ይማርበት ዘንድ ከጠላት ጎን የተሰለፉትም አጸያፊ ተግባር ይሰፍራል፡፡ ሀገር ስትወረር ግድ የማይሰጣቸው፣ ለግል ጥቅማቸው ሲሉ የውጭ ጠላትን ከሀገራቸው የሚያስበልጡ አካላት መኖራቸው የብዙ ሀገራት ታሪክ ክስተት ነው፡፡ አሜሪካዊው የታሪክ ምሁር ፕሮፌሰር ሮበርት ኦ. ፓክስተን እ.ኤ.አ በ1972 “Vichy France: Old Guard and New Order, 1940–1944” በሚል ርዕስ ባሳተሙት መጽሐፋቸው እንደገለጹት፣ ፈረንሳይ በናዚ ጀርመን ስትወረር ከሀገራቸው ጠላት ጋር የተባበሩ የፖለቲካ ኃይሎች ነበሩ፡፡ ምሁሩ እንደሚያስረዱት፣ ሀገር በውጭ ኃይላት ስትጠቃ በጽናት ከሚታገሉት በርካታ ዜጎች ባሻገር ከጠላት ጎን የሚቆሙ አካላት አይጠፉም፡፡

በኢትዮጵያም የባንዳነትን ታሪክ ለመረዳት ወደ 1888 ዓ.ም የዓድዋ ድል መመለስ አስፈላጊ ነው፡፡ ከዓድዋ ታላቅ ገድል ባሻገር ከወራሪዎች ጎን የተሰለፉ ባንዳዎች እንደነበሩ ታሪክ ይመሰክራል፡፡ ባንዳነት ማለት ጠመንጃ ይዞ ከወራሪው ጎን ተሰልፎ መዋጋት ብቻ ሳይሆን፣ የወራሪውን አስተዳደር ማገዝ፣ መረጃ መስጠት ወይም የፖለቲካ ቁጥጥሩን ማጠናከርም ያካትታል፡፡

ለአብነትም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ለ85ኛው የጀግኖች አርበኞች በዓል ባስተላለፉት መልዕክት አርበኝነት ማለት ለሀገር ያለ ዋጋ የሚከፈል ከራስ ወዳድነት የነጻ መሥዋዕትነት ነው። ዓላማውም ሀገርን እና ሕዝብን ብቻ ማዕከል ያደረገ ነው። እናትና አባት አርበኞች ከፋሺስት ጋር የተዋጉት ለሀገር እና ለወገን ብለው ነው። በግል ጥቅም ለማግኘትማ ከአርበኝነት ይልቅ ባንዳነት አቋራጭ ነበር፤ ግን አላደረጉትም። የአርበኝነት ትግሉ ከሦስት ጠላቶች ጋር የተደረገ ነበር፤ ከራስ ፍላጎት፣ ከባንዳ እና ከወራሪ ፋሺስት ጋር። አርበኝነት የራስን ጥቅም ለሀገር ጥቅም ሲባል መተው ነው፤ ባንዳዎች ማለት ራሳቸውን ማሸነፍ ያቃታቸው ናቸው ማለታቸው ይታወሳል።

የግል ጥቅምን እና ክብርን ማሸነፍ ሲያቅታቸው የሀገራቸውን ክብር እና ጥቅም ይሸጣሉ ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ባንዳነት ማለት ሀገርን ለራስ ጥቅም በመሸጥ የሚከናነቡት የውርደት ካባ ነው። አርበኞች ከባንዳዎች ጋር ታግለዋል። ባንዳዎች በአንድ በኩል “ሀገራችሁን ሸጣችሁ እንደኛ በግል ተጠቀሙ” ይሏቸዋል፤ በሌላ በኩል መንገድ እየመሩ ወራሪውን ያመጡባቸዋል። ያም አልሆን ሲላቸው ሕዝቡን በሐሰተኛ ወሬ ልቡን ይሰልቡታል። ዛሬም ሦስቱም ጠላቶች አሉ፤ መልክና ስም ብቻ ቀይረዋል። በሌላም በኩል ዛሬም በየመስኩ የተሠማሩ ኢትዮጵያውያን አርበኞች አሉ። የኢትዮጵያ ብልጽግና እንዲሳካ ብሔራዊ አርበኞችን ይፈልጋል፤ የራስ ፍላጎትን፣ ባንዳነትን እና ወራሪን እምቢ የሚል አርበኝነት፣ ማለታቸው አይዘነጋም።

በሌላ በኩል ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ በልዩ ዘመቻዎች ዕዝ የ2018 የበጀት ዓመት የሥራ አፈፃፀም ውይይት ማጠቃለያ ላይ ተገኝተው ወቅታዊ ጉዳይን በማስመልከት ባስተላለፉት መልዕክት ሻዕቢያ ከጅምሩ ኢትዮጵያን ከባሕር በር ለማራቅ ከታሪካዊ ጠላቶቻችን ጋር ፅምዶ ፈጥሮ ኢትዮጵያ ላይ ደባ የሠራ ኃይል መሆኑን አስታውሰዋል።

ሕገ ወጡ ህወሃትም የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም አሳልፎ የሸጠና ለ27 ዓመታት ሥልጣን ይዞ ኢትዮጵያ የሕህር በር እንድታጣ ጠንክሮ የሠራ ቅጥረኛ፣ የገዛ ሀገሩን ሠራዊት ያጠቃ የክህደት ኃይል ነው ብለዋል። ኢትዮጵያ በተደጋጋሚ በህወሃት ክህደት የተፈተነች ነገር ግን ፀንታ የቆመች፣ የልዩ ዘመቻ ሠራዊት የመሰሉ ጠንካራ አርበኛ ልጆች ያሏት ሀገር ስለሆነች ጉዞዋን ቀጥላለች ሲሉ አጽንኦት ሰጥተዋል።

ፅንፈኞቹን የጥፋት ኃይሎች በባዕዳን ስትራቴጂ ሥር ተሰልፈው ኢትዮጵያን የማዳከምና የማፍረስ ፅምዶ የተባለ ጥምረት ቀርፀው ሕዝባችንን ለስቃይና መከራ በመዳረግ ደካማ ኢትዮጵያን ለማየት ጓጉተው ቢሠሩም፣ ይህ ፍላጎታቸው መቼም ሊሳካ እንደማይችል አሳይተናቸዋል ነው ያሉት።

ህወሃት የኢትዮጵያን ሕዝብ በመከፋፈል እርስ በእርሱ እንዳይተማመን ያደርግ እንደነበረ አውስተው፣ ዛሬ ላይ ያ ሁሉ ሴራ ከሽፎ የትግራይ ሕዝብን ጨምሮ አጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ የዚህን መሰሪ ቡድን መጥፎ ተግባር በመረዳቱ፣ ወያኔ ከሕዝብ ተነጥሎ መንጠልጠያ ሲያጣ የቀድሞ ጠላቶቹን ሽኔንና ፅንፈኛ ፋኖን አቅፎ፣ ሻዕቢያን ደግሞ አዝሎ የትላንት ክህደቱን በአደባባይ እየደገመው ይገኛል ማለታቸው ይታወሳል።

ከአዲስ ልሳን ጋዜጣ ጋር ቆይታ ያደረጉት የታሪክ ምሁሩ አሕመድ ዘካሪያ እንደሚያስረዱት፣ ኢትዮጵያ በታሪኳ ለውጭ ወረራና ችግሮች በአንድነት የመቆም ታላቅ ባህል አላት፡፡ ሀገራዊ ሉዓላዊነቷ አደጋ ላይ በወደቀበት ወቅት ሁሉ ሕዝቧ እንደ አንድ ሰው ሆኖ መመከት እንደሚችል የታሪክ ድርሳናት ይመሰክራሉ፡፡ ከመካከለኛው ዘመን የኦቶማን ቱርክና የፖርቹጋል ሽኩቻ፣ በዘመነ መሳፍንት የነበሩ የግብፆችና የእንግሊዞች ሙከራዎች፣ እንዲሁም የፋሺስት ጣሊያን ወረራዎችን ለአብነት ያነሱት ፕሮፌሰሩ፣ በእነዚህ ሁሉ አጋጣሚዎች ኢትዮጵያውያን የውስጥ የፖለቲካ ልዩነቶች ቢኖሯቸውም ሀገር ሲነካ ግን ልዩነታቸውን ወደ ጎን በመተው ለነፃነታቸው በአንድነት መቆማቸውን ገልጸዋል፡፡

በዘመናዊው የፖለቲካ ምህዳር የውጭ ጠላቶች ቀጥተኛ ወረራ ከማካሄድ ይልቅ የውስጥ ደካማ ጎኖችን፡- ብሔርን፣ ኃይማኖትንና ቋንቋን መሣሪያ በማድረግ የውክልና ጦርነት ማካሄድን መርጠዋል። በጥቅም የተደለሉ አሊያም ሳያውቁት የውጭ ጠላቶች መጠቀሚያ የሚሆኑ አካላት መኖራቸው የሀገሪቱን ሰላምና እድገት ይጎዳል፡፡ በአሁኑ የቴክኖሎጂ ዘመን የሚካሄደው የሀሰት መረጃና የወሬ ጦርነት ሕዝብን በማደናገር በኩል ትልቅ አደጋ ደቅኗል፡፡ በመሆኑም ይህንን ለመመከት የመንግስትና የሚዲያ ተቋማት እውነተኛና ጥራት ያለው መረጃ ለሕዝቡ ማቅረብ እንዳለባቸው መክረዋል፡፡

ሀገር ልትፀና የምትችለው የፖለቲካም ሆነ የኢኮኖሚ ነፃነት ሲረጋገጥ እንደሆነ የሚናገሩት የታሪክ ምሁሩ አሕመድ፣ ወጣቱ ትውልድ ሥራ ፈጣሪና ችግር ፈቺ ሊሆን እንደሚገባው ገልጸዋል፡፡ የተፈጥሮ ሀብትን በፍትሐዊነት በመጠቀም፣ የውስጥ ልማትን በማሳደግና የፖለቲካ መረጋጋት በማምጣት የውጭ ጫናዎችን ማሸነፍ ይቻላል፡፡

በአፍሪካ ህብረት የ2063 አጀንዳ መሠረት አህጉራዊ አንድነትን ለመገንባት መሠረቱ በሀገር ደረጃ ጠንካራ አንድነትና የኢኮኖሚ ነፃነት መገንባት እንደሆነም አመልክተዋል፡፡ “ሀገር ካለች ሁሉም ይሳካል፤ ሀገር ከታጣች ግን ተገዢ መሆን አይቀሬ ነው” በማለት፣ የውስጥ ልዩነቶችን በተቋማዊ አሰራር በመፍታት ሀገራዊ ህልውናን ማስጠበቅ የወቅቱ ጥሪ እንደሆነም አጽንኦት ሰጥተዋል፡፡

በጂማ ዩኒቨርሲቲ የታሪክ መምህርና ተመራማሪው ዴሬሳ ዴቡ (ዶ/ር)፣ በኢትዮጵያ የታሪክ ሂደት ውስጥ በውጭ ጠላቶች ወረራ ወቅት ሕዝቡ የውስጥ ልዩነቶችን ወደ ጎን በመተው በጋራ የመቆም ታሪካዊ እሴት እንዳለው ያስረዳሉ፡፡ ሆኖም በዚህ ታላቅ የተጋድሎ ታሪክ ውስጥ አልፎ አልፎ የግል ጥቅማቸውን ከሀገር አስበልጠው ከባዕዳን ጎን የሚቆሙ ባንዳዎች አለመታጣታቸውንም ይጠቅሳሉ፡፡

ለአብነትም በ1860ዎቹ እና 70ዎቹ መጨረሻ ግብፆች 85 በመቶ የአባይ ምንጭ የሆነችውን ኢትዮጵያን ለመቆጣጠር በተንቀሳቀሱበት ወቅት፣ በጉንደትና በጉራ ጦርነቶች አብዛኛው ሕዝብ ጠላትን ቢመክትም የተወሰኑ ባንዳዎች ከታሪካዊ ጠላት ጋር ተሰልፈዋል፡፡ በዶጋሊ ጦርነት ወቅትም ጥቂት አካላት ወደ ጣሊያን ቢጠጉም፣ አብዛኛው ሕዝብ ዘምቶ ሀገሩን ጠብቋል። በዓድዋ ጦርነት ወቅትም ከዳር እስከ ዳር ያለው ሕዝብ ዘምቶ ታሪካዊ ድል የተቀዳጀ ሲሆን፣ ከ40 ዓመታት በኋላ በሁለተኛው የጣሊያን ወረራ ወቅትም አብዛኛው ሕዝብ በደፈጣ ውጊያና በአርበኝነት ታግሎ ሀገሩን ነጻ አውጥቷል።

ዶ/ር ዴሬሳ እንደሚሉት፣ በአርበኝነት ውስጥ በግንባር ከሚዋጉት ባሻገር “የውስጥ አርበኞች” የሚባሉት ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል፡፡ የውስጥ አርበኞች ከጠላት ጋር አብረው የሚሰሩ አስመስለው በመቅረብ ለአርበኞች ወሳኝ የመረጃና የምግብ ድጋፍ ያደርጉ ነበር፡፡ በዓድዋም ሆነ በ5 ዓመቱ የፋሺስት ወረራ ዘመን እንደ አዋሎም ያሉ ታዋቂ ግለሰቦችና አያሌ ሴቶች የውስጥ አርበኛ በመሆን ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል፡፡

ታሪክ እንደሚያስተምረን ጠላት ዋና ዓላማው የራሱን ሀገራዊ ጥቅም ማስከበር ብቻ ነው፡፡ ለራሱ ጌታ ያልታመነን ሰው ጠላትም አያምነውምና ጥቅሙን ካስከበረ በኋላ አገልጋዮቹን ወይም ባንዳዎችን መጣሉ የማይቀር ነው፡፡ በመሆኑም ከምንም በላይ ሀገራዊ ጥቅምን ማስቀደሙ የሁልጊዜም ትኩረት ሊሆን እንደሚገባ ዶ/ር ዴሬሳ አሳስበዋል፡፡



ፎቶ- ከፋይል

በኢትዮጵያ የታሪክ ሂደት ውስጥ አብዛኛው ሕዝብ የውስጥ ልዩነቶችን ወደ ጎን በመተው ጠላትን በጋራ የመመከት ታላቅ ሀገራዊ እሴት አለው


አዋሽ ባንክ
AwashBank
Nurturing Like The River
እንኳን
ለኢሬቻ
በዓል በሰላም አደረሳችሁ
በዓሉ የሰላም፣ የበረከትና የምስጋና
እንዲሆንላችሁ እንመኛለን!
Nurturing Like The River
www.awashbank.com


ተደራሽ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኃ/የተ/የህ/ስ/ማህበር
Tederash Saving & Credit Cooperative Society Ltd.
እንኳ ን ለ2019 ዓ.ም
ለኢሬቻ በዓል በሰላም አደረሳችሁ!
ተደራሽ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኃ/የተ/የህ/ስ/ማህበር በዓሉ የሰላም
የጤናና የፍቅር እንዲሆንላችሁ ይመኛል።
አቶ አለማየሁ በየነ የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ
የምንሰጣቸው አገልግሎቶች
1 የቁጠባ አገልግሎት
• መደበኛ ቁጠባ
• የፍቃደኝነት ቁጠባ
• የጊዜ ገደብ ቁጠባ
• የንግድ/የቀን ገቢ ቁጠባ
• የቤት ቁጠባ
• የመኪና ቁጠባ
• የሴቶች ልዩ ቁጠባ
• የወጣቶች/ተማሪዎች ቁጠባ
• የህጻናት/ልጆች ቁጠባ
• የድርጅት ቁጠባ
• የኤሌክትሪክ መኪና ባትሪ ቁጠባ
2. ከወለድ ነፃ የፋይናንስ አገልግሎት/ Interest Free Service
3. የብድር አገልግሎት
• በአዲስ ንግድ ስራ ለሚሰማሩ እና ለነባር ንግድ ማስፋፊያ
• ለቤት ግንባታ፤ ግዥና እድሳት
• ለኮንዶሚኒየም ክፍያ
• ለመኪና ግዥ
• ለኢንቨስትመንት
• ለስራ ፈጠራ
• ለማህበራዊ ጉዳይ፦ ለሕክምና፤ ለትምህርት ስልጠና፣ ለንብረት ግዥና ዕድሳት፤ ለቀለበትና ጋብቻ
• ለብድር መድህን ዋስትና እንዲሁም የተለያዩ ኑሮን ለማሻሻል ለሚያስችሉ ጉዳዮች መበደር ይችላሉ።
መልካም በዓል!
ስልክ 7078/0970444411/88/00,
አድራሻ ዋና ቢሮ አራት ኪሎ ኢትዮጵያ ፖስታ ቤት
ትንሽ ቆጥበው ትልቅ ይሁኑ!
ተደራሽ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኃ/የተ/የህ/ስ/ማህበር

ከአዲስ አበባ ኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ በየሳምንቱ የሚቀርብ

# የመዲናዋ የቴክኖሎጂ መሰረተ-ልማት አቅሞች

**በደረጀ ታደሰ**

አዲስ አበባን ዘመናዊና ምቹ ስሉጥ ከተማ (Smart City) ለማድረግ በርካታ ግዙፍ ሥራዎች ተሠርተዋል፤ እየተሠሩም ናቸው፡፡ ከሥራዎቹ መካከል በመዲናዋ የሚከናወኑት ሰፋፊ የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ (ICT) ልማቶች የሚጠቀሱ ሲሆን፤ እነዚህም በከተማዋ ሁለንተናዊ ዕድገት ላይ ከፍተኛ ሚና እየተጫወቱ ይገኛሉ። ለዚህ ደግሞ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ድርሻው የላቀ ነው፡፡ ምክንያቱም ቢሮው፤ በምርምርና ጥናት የተደገፉ የመረጃ ቴክኖሎጂ መሰረተ-ልማቶችን በመገንባት፣ የሳይበር ደህንነቱ የተረጋገጠ አሠራርን በመዘርጋት እና ዲጂታል አገልግሎቶችን በማስፋፋት የከተማዋን ነዋሪዎችና ጎብኝዎች ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ተልዕኮ ይዞ፤ ይህንን ለማሳካት ትኩረት አድርጎ ስለሚሠራ ነው፡፡

ቢሮው፣ ተልዕኮውን በውጤታማነት ለማሳካት፣ ዘላቂነቱ በተረጋገጠ መልኩ ለማስቀጠል የሚያስችሉ አደረጃጀቶችን እና አሠራሮችን ተግባራዊ አድርጓል፡፡ በተለይ የከተማዋን ሁለንተናዊ የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ጉዞ ለማሳካት፣ የስትራቴጂ፣ የልማት እና የኦፐሬሽን አገልግሎት ዘርፎች ላይ በማተኮር እየሠራ ይገኛል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ቀደም ባሉት የጋዜጣችን ዕትሞች ባቀረብናቸው ጽሑፎች መረጃዎችን ለማጋራት ሞክረናል፡፡ በዚህ ዕትም ደግሞ፤ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ወጥቶባቸው፣ የከተማዋን የስሉጥ ከተማነት ሂደት ለማሳካት ለአገልግሎት የበቁ የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ውጤቶች እና መሰረተ ልማቶች (ሀርድ ዌርም እና ሶፍት ዌርም) ደህንነታቸው ተጠብቆ፣ በዘላቂነትና በውጤታማነት አገልግሎት እንዲሰጡ በማስቻል ረገድ የቢሮውን ሚና እንቃኛለን፡፡

ከላይ ለመጥቀስ እንደሞከርነው፤ በጥናት ላይ በተመሰረተ አግባብ በራስ አሊያም በውጭ አቅም ለምተው፣ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ወጥቶባቸው፣ የከተማዋን የስሉጥ ከተማነት ሂደት ለማሳካት ለአገልግሎት የበቁ የኢንተርኔትና የሶፍትዌር መሰረተ-ልማቶችን በይፋ በመረከብ ቀጣይነታቸውን እና ዘላቂነታቸውን ማረጋገጥ ቁልፍ ጉዳይ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ ለዚህም ነው ይህንን ወሳኝ ኃላፊነት የሚወጣ ክፍል በቢሮው ሥር ተደራጅቶ በሥራ ላይ የሚገኘው፡፡ እኛም ስለ ሥራ ክፍሉ ተግባርና ኃላፊነት፣ በሥራ እንቅስቃሴ ውስጥ የሚያጋጥሙትን ፈተናዎችና የወሰዳቸውን የመፍትሄ እርምጃዎች በተመለከተ፣ በቢሮው የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ (ICT) የኦፐሬሽንና ጥገና ዳይሬክተር አቶ ድርሻዬ ካሰኝ ጋር ቆይታ አድርገናል፡፡



ፎቶ፡- ከፋይል

የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ የኦፕሬሽንና ጥገና ባለሙያዎች የተቋማትን የአይሲቲ መገልገያዎች ሲጠግኑ

በቢሮው በልዩ ሁኔታ ተጠንተውና ለምተው የሚወጡ የኢንተርኔትና የሶፍትዌር መሰረተ-ልማቶችን በመረከብ ቀጣይነታቸውን የማረጋገጥ ወሳኝ ኃላፊነት እንዲወጣ የተቋቋመውን ክፍል የሚመሩት እና የሚያስተባብሩት አቶ ድርሻዬ እንዳብራሩት፤ ዳይሬክቶሬቱ ኃላፊነቱን በውጤታማነት ለማሳካት በስሩ የክላውድ (Cloud) እና የኦፐሬሽንና ጥገና የተሰኙ ሁለት ትላልቅ ንዑሳን ክፍሎች ተደራጅተዋል፡፡ በእነዚህ አደረጃጀቶች ሥር ያሉ ሙያተኞች ከማዕከል ጀምሮ በ11ዱም ክፍለ ከተሞችና ወረዳዎች የሚገኙ የዳታ ሴንተሮችን፣ ተቋማዊ አውታሮችንና ሶፍትዌሮችን በቅርበት ይከታተላሉ። ችግሮችም ሲያጋጥሙ አፋጣኝ መፍትሄ ይሰጣሉ፡፡

እንደ አቶ ድርሻዬ ገለጻ፤ በመንግሥትና በሕዝብ አገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ውስጥ የቴክኖሎጂ መሰረተ-ልማቶች በተለያየ ምክንያት መስተጓጎል ሊገጥማቸው ይችላል፡፡ የቴክኖሎጂ መሰረተ-ልማቶች ላይ የሚከሰቱ ችግሮች ምክንያታቸው፡- ከቆይታ ብዛት፣ ከአጠቃቀም ጉድለት ወይም ከድንገተኛ አደጋዎች ሊፈጠር ይችላል። እንደ መቀየሪያዎች (Switches) መቃጠል፣ የፋየርዎል (Firewall) መስተጓጎል እና የኔትዎርክ መስመሮች መቆራረጥ ያሉ ችግሮች በዋናነት ይጠቀሳሉ። ዳይሬክቶሬቱ እነዚህንና መሰል ችግሮች ሲከሰቱ አፋጣኝ መፍትሄ ለመስጠት የሚያስችሉ በቴክኖሎጂ የተደገፉ ዘመናዊ አሠራሮችን ይከተላል፡፡

**በከተማ አስተዳደር ደረጃ በዲጂታል ቴክኖሎጂ አገልግሎት ላይ ሊከሰት የሚችለውን ችግር በውስጥ አቅም እንዲሁም ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር በቅንጅት በመሥራት እንዲፈቱ በመደረግ ላይ ነው**

በከተማ አስተዳደር ደረጃ በዲጂታል ቴክኖሎጂ አገልግሎት ላይ ሊከሰት የሚችለውን ችግር በቢሮው የውስጥ አቅም እንዲሁም ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር በቅንጅት በመሥራት የሚፈታ መሆኑን የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ (ICT) የኦፐሬሽንና ጥገና ዳይሬክተሩ ጠቁመዋል፡፡ ለሥራው ስኬት በአጋዥነት ጥቅም ላይ ስለዋሉ ዘመናዊ አሠራሮችና አተገባበራቸው በተመለከተ እንዳስረዱት ከሆነ፤ በማዕከልና በክፍለ ከተማ ደረጃ ያሉ ተጠቃሚዎች የቴክኖሎጂ መስተጓጎል ሲገጥማቸው በአካል መሄድ ሳይጠበቅባቸው፣ "የአይቲ ኤስ ኤም (IT Service Management -ITSM) በተሰኘው የሶፍትዌር መተግበሪያ ላይ የችግሩን ሁኔታ በቀጥታ ይመዘግባሉ። ይህ ሲስተም በኢንተርኔት እንዲሁም በወረዳ ኔት (Wereda Net) የሚሠራ ስለሆነ፤ ባለሙያዎች ችግሩ ወዳለበት ቦታ ሳይንቀሳቀሱ በሲስተም አማካኝነት ፈጣን ምላሽ እንዲሰጡ ያስችላቸዋል፡፡ ከውጪ መስመር ጋር የተያያዙ የኔትዎርክ መቆራረጦች ሲፈጠሩ ደግሞ ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር በቅርብ ርቀት በመቀናጀት በአስቸኳይ ጥገና እንዲደረግላቸው ይደረጋል።

አዲስ አበባን ወደ ሙሉ ስሉጥ ከተማነት (ስማርት ሲቲ) (ዘመናዊ ከተማ) የመቀየር ሂደት ከፍተኛ ስኬት እያሳየ መሆኑን ያነሱት ዳይሬክተሩ፤ ይህን በዘላቂነት የማስቀጠል አቅም እየገነቡ መሄድ ያስፈልጋል፡፡ ይህን ታሳቢ በማድረግ ቢሮው አዳዲስ ግዙፍ የቁጥጥር ማዕከላትን ገንብቶ ወደ ሥራ ማስገባቱን ጠቁመዋል፡፡

እንደ ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ ቢሮው ወደ አገልግሎት ያስገባቸው ግዙፍ የቁጥጥር ማዕከላት፡- የ-NOK (Network Operating Centre) እና የ-SOK (Security Operating Centre) ማዕከላት ዋና ዋናዎቹ ናቸው። የ-NOK (Network Operating Centre) ማዕከል በመላው ከተማዋ የሚገኙ የቴክኖሎጂ እና የኔትዎርክ መሰረተ-ልማቶችን በአንድ ማዕከል ሆኖ ለመቆጣጠርና የትኛው ክፍለ ከተማ ወይም ሴክተር ላይ የሲስተም ብልሽት እንዳለ በግልጽ ለመከታተል የሚያስችል ነው፡፡ በተጓዳኝ የተገነባው የ-SOK (Security Operating Centre) ማዕከል ደግሞ በከተማዋ የዲጂታል አውታር ላይ የሚሰነዘሩ ማንኛቸውንም አይነት የሳይበር ጥቃቶችና ያልተፈቀዱ የደህንነት መግለጫዎችን (Intruders) በቅድሚያ በመለየትና በመከላከል የደህንነት ጋሻ ሆኖ በማገልገል ላይ ይገኛል።

በከተማ አስተዳደሩ ሥር የሚገኙ የመንግሥት ተቋማት ውስጥ ተበላሽተው የተቀመጡ የ-IT ዕቃዎችን (ኮምፒዩተሮች፣ ፕሪንተሮች፣ ላፕቶፖችና ኮፒ ማሽኖች) በራስ አቅም (የውስጥ ባለሙያዎች) ጠግኖ ወደ አገልግሎት መመለስ ላይ የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ (ICT) የኦፐሬሽንና ጥገና ዳይሬክቶሬት ሚና በጉልህ የሚነሳ ስለመሆኑ አቶ ድርሻዬ ተናግረዋል፡፡ ቢሮው በዚህ አሠራሩ በ2017 በጀት ዓመት ከ130 ሚሊዮን ብር በላይ፣ እንዲሁም በ2018 በጀት ዓመት ከ62 ነጥብ 2 ሚሊዮን ብር በላይ የመንግሥትንና የሕዝብን ገንዘብ ከብክነት ማዳን መቻሉ በማሳያነት የሚጠቀስ ነው፡፡ ከዚህ ባሻገር ዳይሬክቶሬቱ ከተለያዩ የሀገሪቱ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት (እንደ ጎንደር፣ ሚዛን ቴፒ፣ ሐረማያና ደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲዎች) የሚመጡ የ-IT እና የኮምፒውተር ሳይንስ ተማሪዎችን በተግባር በመደገፍና የተቋማትን ችግር የሚፈቱ አዳዲስ ሶፍትዌሮችን (ለምሳሌ የ-IP Management Tool) በጋራ እንዲያለሙ አድርጓል፡፡ በዚህም የሰው ኃይል ልማትንና ክህሎትን የማሳደግ ድርብ ስራዎችን በስኬት እያከናወነ እንደሚገኝ አስረድተዋል፡፡

የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ (ICT) የኦፐሬሽንና ጥገና ዳይሬክቶሬት የተሰጠውን ኃላፊነትና ተግባር በአግባቡ እንዲሁም በብቃት ለመወጣት የሚያደርገውን ጥረት አጠናክሮ እንደሚቀጥል የገለጹት አቶ ድርሻዬ፤ "የከተማዋን የቴክኖሎጂ ዕድገት አስተማማኝ ለማድረግ እያንዳንዱ የመንግሥት ተቋም በየደረጃው ያሉትን የኔትዎርክ መሰረተ-ልማቶችና የኮምፒዩተር ዕቃዎች እንደ ራሱ የግል ንብረት በጥንቃቄ ሊይዛቸውና ሊጠብቃቸው ይገባል። አዳዲስ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችና ዲጂታል አሰራሮች በከተማዋ ውስጥ በስፋት ሲዘረጉ፣ ማህበረሰቡና የመንግሥት ሰራተኞች ቴክኖሎጂዎቹን በአግባቡ መልመድ፣ መጠቀምና ራሳቸውን ማሻሻል ይኖርባቸዋል። ይህ ዓይነቱ ንቁ ተሳትፎ እና ኃላፊነት የሚሰማው አጠቃቀም ሲጎለብት አዲስ አበባን በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ተሟላና ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ስማርት ሲቲነት ማሸጋገር እንደሚቻል በጽኑ ይታመናል።" ብለዋል፡፡



**ግራንድ አፍሪካን** የተቋማትና የአመራር ሽልማት ድርጅት ህጋዊ ፈቃድ ኖሮት በሀገራችን በአምራችነትም ሆነ በአገልግሎት ሰጪነት የሰሩ ተቋማት ለሀገር እና ለህዝብ ለሰሩት ስራ ምስጋና፣ ሽልማትና እውቅና በመስጠት የላቀ ስራ በመስራት እንዲዘልቁ ለማድረግ የተቋቋመ ብቸኛ የሽልማት ድርጅት ነው። ድርጅታችን ላለፉት 32 ዓመታት በነበሩት ሽልማቶች የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ ኦሮሚያ ባንክ፣ የካቲት 12 ሆስፒታል፣ አባሃዋ ትሬዲንግ፣ የኦሮሚያ ኮንስትራክሽን ስራዎች ኮርፖሬሽን፣ የኢትዮጵያ ግብርና ስራዎች ኮርፖሬሽን፣ ኮምቦልቻ ጨርቃጨርቅ፣ አድማስ ዩኒቨርስቲ፣ ሀሌሉያ ሆስፒታል፣ አዲስ የመድሃኒት ፋብሪካ፣ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ አሰር ኮንስትራክሽን፣ ስቲሊአርኤም ብረታ ብረት፣ ጎንደር ዩኒቨርስቲ፣ ሙገር ሲሚንቶ፣ ቀርጫንሺ ግሩፕ፣ ሌሶ ኢትዮጵያ፣ ኤስሳራ ቡና ላኪ፣ ግሎባል ባንክ ኢትዮጵያ፣ አሚን ሆስፒታል፣ ዘመን ኢንሹራንስ፣ ታደሰ ደስታ አስመጪና ላኪ፣ ሮያል ፎም፣ ቲኬ ግሩፕ ማኑፋክቸሪንግ ኤንድ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማ፣ ኢትዮ-ኢንጂነሪንግ ግሩፕ የፓወር ኢክፕመንት ማምረቻ ኢንዱስትሪ፣ አስመን ኃ/የተ/የግ/ማ፣ የክርስቲያን በጎ አድራጎት እና ልማት ማኅበራት ህብረት፣ የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን፣ ኦሮሚያ ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን፣ ኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል፣ ኢንዲያና ት/ቤት፣ የኦሮምያ ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል እና ኪነ-ጥበብ ቢሮ፣ ኦሮሚያ ግብርና ቢሮ፣ የኢትዮጵያ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻሕፍት አገልግሎት፣ የኦሮሚያ ገቢዎች ቢሮ፣ ፋና ሚዲያ ኮርፖሬሽን አ.ማ፣ የኢትዮጵያ አርክቴክቶች ማህበር፣ ኢፌድሪ የመንግስት ሰራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር፣ የቢሾፍቱ ከተማ አስተዳደር፣ ጸሜክስ ግሎባል ኢንተርፕራይዝ ኃ/የተ/የግ/ማ፣ ኢፌድሪ የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኢንስቲትዩት፣ ቀስተ ደመና ፕላስቲክ ኢንደስትሪ ኃ/የተ/የግ/ማ፣ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት፣ ቤዛ ፓስቴሪቲ የልማት ድርጅት እና ሌሎችም ተሸልመዋል። የ2018 ዓ.ም ማጠናቀቂያም ዜና የተሰራላቸው የግራንድ አፍሪካን የተቋማትና አመራር ሽልማት ድርጅት ተሸላሚዎች ጥቅምት 1 ቀን 2019 ዓ.ም ይሸለማሉ። በተጨማሪም የእህት ኮባንያችን የወርልድ ክላስ የጥራት ሽልማት ድርጅት ተሸላሚዎች ጥቅምት 8 ቀን 2019 ዓ.ም ይሸለማሉ። ሌላው የሽልማት ድርጅታችን እህት ኩባንያ አቢሲኒያ የከፍተኛ ክብር የሎሬት ሽልማት ድርጅት በልዩ ድምቀት ህዳር 6 ቀን ግለሰብ ሎሬቶችን ይሸልማል።

# እንኳን ለ2019 ዓ.ም

## ለኢሬቻ በዓል በሰላም አደረሳችሁ!

## ግራንድ አፍሪካን የተቋማትና የአመራር ሽልማት ድርጅት!






**ለተጨማሪ መረጃ**

**+251911 – 24 83 68 / +251911 – 24 23 88 ይደውሉ።**



# እንኳን ለ2019 ዓ.ም. የኢሬቻ በዓል አደረሳችሁ!

ተፈጥሮ ልብሷን ለብሳ ምድር ለምለም ሆና፣ የምስጋናና የመተሳሰብ ድባብ በአካባቢያችን ተሰፋፍቶ፤ ኢሬቻ የምስጋና፣ የሰላምና የአንድነት መልዕክቱን ይዞ በድምቀት ሲከበር፤ ላይፍ ቁጠባና ብድርም ለማህበረሰቡ የተሻለ ነገን ለመገንባት አዳዲስ የቁጠባና የብድር አማራጮችን እያበረከተ ይገኛል። በመቶ ሺዎች ካፒታል ሥራውን ሀ ብሎ የጀመረው ላይፍ ቁጠባና ብድር፣ አባላቱን በቤት፣ በመኪናና በንግድ ህልማቸውን እያገዘ ከስኬት ማማ ላይ ደርሷል። ዛሬም አንድ ቢሊየን ብር ተቀማጭ ካፒታል በማሳካት የአባላቱን እምነት በተግባር እየመለሰ ይገኛል።

## ኢሬቻ የምናመሰግንበት፣ የምንተሳሰብበትና የነገን ተስፋ የምንገነባበት በዓል ነው።

እርስዎም በዚህ የምስጋና በዓል የነገ ህልምዎን ዛሬ ይጀምሩ።

ለቤት፣ ለመኪና፣ ለንግድ ማስጀመሪያና ማስፋፊያ በአጭር ጊዜና ቀልጣፋ አሠራር፣ እስከ 20 ሚሊየን ብር የሚደርስ የብድር አማራጭ ከእኛ ያገኛሉ።

በዚህ ኢሬቻ ከልብ ለሚወዷቸው ሰዎች የወደፊት ስኬትን በስጦታ ያበርክቱ።

የቤት ቁጠባ፣ የመኪና ቁጠባ፣ የንግድ ማስጀመሪያ ወይም ማስፋፊያ ቁጠባ እንዲሁም የሕፃናት ቁጠባ፣ ዛሬ የሚጀምሩት ቁጠባ የነገ ስኬትዎ መሠረት ነው።

### ከእኛ ጋር አዲስ ቤተሰብ ለመሆን የትኛው ቅርንጫፍ ይቀርብዎታል?



### ዋና መሥሪያ ቤት – 6 ኪሎ

ቅርንጫፎቻችን፦

አራዳ ጊዮርጊስ፣ ደጃች ውቤ፣ ሀያ ሁለት፣ ጀሞ 1፣ ቡራዩ፣ ለገጣፎ

በክልል ከተሞች፦ አዳማና መቀሌ

መልካም የኢሬቻ በዓል ይሁንላችሁ!

ላይፍ ኃ/የተ/መ/ ቁጠባና ብድር የህብረት ሥራ ማህበር



ከተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ጋር በመተባበር በየወሩ የሚቀርብ

# ከወርቃማው ሰኞ ወርቃማ ተሞክሮ

**በፋንታነሽ ተፈራ**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በየጊዜው የሚያፈልቃቸው አዳዲስ እሳቤዎች የአገልግሎት አሰጣጡ የተቀላጠፈ እንዲሆንና ሰራተኞች በቅንነትና በታማኝነት ያገለግሉ ዘንድ ምቹ መደላድል እየፈጠሩ ይገኛሉ፡፡ ከነዚህም መካከል "ወርቃማው ሰኞ" አንዱ ነው። ይህም የሳምንቱ የስራ መጀመሪያ የሆነውን ቀን በብሩህ አዕምሮና መንፈስ ለመጀመር የራሱን አዎንታዊ አበርክቶ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

"ወርቃማው ሰኞ" የሚል መጠሪያ የተሰጠውና በሳምንቱ መጀመሪያ ቀን ሰኞ ጠዋት የሚካሄደው የመማማሪያ መርሃ ግብር ከሁለት ዓመት በላይ አስቆጥሯል፡፡ ይህ በአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ ሐሳብ አመንጭነትና መሪነት የተጀመረው መርሃ ግብር የ'ጥቁር ሰኞ' እሳቤን ወደ 'ወርቃማ ሰኞ' የቀየረ ሆኗል።

ከንቲባ አዳነች አቤቤ መርሃ ግብሩ የጀመረበትን ሁለተኛ ዓመት ባከበሩበት ወቅት ሳምንታችንን አጨልመን አንጀምርም፤ የሳምንቱ መጀመሪያ ሰኞ ለእኛ ፍካትና ተስፋ የሚሰጠን ቀን ነው ማለታቸውም ይታወሳል፡፡ 'ወርቃማ ሰኞ' ሦስት ግቦችን ማለትም ከተማችንን የብልጽግና ተምሳሌት እናደርጋለን፣ ስንተባበር ለውጥ እናመጣለን እና እዚህ ያለነው ለማገልገል ነው የሚል መሪ ሀሳብ በማንገብ የተጀመረ መሆኑ የሚታወስ ነው፡፡



ፎቶ፦ ከገፀ ድር

በተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ የቀድሞው ተማሪ አቶ ተድላ ተሾመ በወርቃማው ሰኞ ላይ የእውቀት ሽግግር ሲያደርጉ

ይህ ተሞክሮ በተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ምን ያህል ተግባራዊ እየተደረገ ነው? ሲል የአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ለመቃኘት ሞክሯል። "በወርቃማ ሰኞ የተለያዩ ልምዶችን ቀስሜበታለው" የሚሉት በኮሌጁ የጋርመንት ስልጠና ዘርፍ አሰልጣኝና የISO ኳሊቲ ማናጀር አቶ ሚካኤል ጎአ ናቸው። በወርቃማው ሰኞ ላይ ያላቸውን ተሳትፎ ሲናገሩ፤ "በመድረኩ ላይ ሁልጊዜ እሳተፋለሁ፡፡ የእውቀት ሽግግሩ የሚደረግልን ከወር አንድ ጊዜ ከውጭ በሚጋበዙ የኮሌጁ የቀድሞው ተማሪዎች እና ቀሪውን ደግሞ በኮሌጁ ሰራተኞች ነው፡፡ ከወርቃማው ሰኞ በፊትም በኮሌጁ ውስጥ የእውቀት አስተዳደር ስርዓት ስላለ የተለያዩ ልምዶችን እና ተሞክሮዎችን ሰራተኞች ለሌሎች እንዲያካፍሉ ይበረታታል፡፡ ይህንንም ለማስቀጠል ወርቃማው ሰኞ መድረክ አጋዥ ነው" ይላሉ፡፡

"ወርቃማው ሰኞ ላይ በመሳተፌ ብዙ ጥቅም አግኝቻለሁ" የሚሉት አቶ ሚካኤል፤ "የተለያዩ ሰዎች በህይወት ጉዟቸው የተለያየ አይነት የህይወት ተሞክሮ እንዳላቸው፣ ዋጋ ከፍለው አሁን ያሉበት ደረጃ ላይ እንደደረሱ እና እኔም እንደነሱ መሆን እንደምችል ተምሬበታለሁ፡፡ አዕምሮዬን የሚያነቃቁ ትምህርቶችን አግኝቼበታለሁ፡፡ በየሳምንቱ ከተለያዩ ሰዎች እውቀት ስለማገኝ ስራዎቼን እንዴት ማሳካት እና ህይወቴንም ጭምር በምን መንገድ መምራት እንዳለብኝ አስተምሮኛል፡፡

በወርቃው ሰኞ የቀድሞው የኮሌጁ ተማሪዎችን ልምድ መካፈል መቻሌ አሁን ለምሰራው ስራም ሆነ ለወደፊት ግብዓት ይሆነኛል፡፡ የስራ ብቃቴን እንዳሳድግ፣ አዳዲስ የአሰራር ዘዴዎችን እንዳውቅ፣ የተማርኩትንም በየዕለቱ ስራዬ ላይ ለመተግበር እንድጥር አድርጎኛል" ሲሉ አቶ ሚካኤል አብራርተዋል፡፡

"በስራ ላይ የሚያጋጥሙኝን ችግሮች ለመፍታት፣ ከሌሎች ሰራተኞች ልምድ መማር ትልቅ ጥቅም እንዳለው ተረድቻለሁ" ያሉት አቶ ሚካኤል፤ የተለያየ ሃሳብ ማዳመጥ የተሻለ መፍትሔ ለማግኘትና በስራቸው ላይ በመተግበር ለተገልጋዮች የተሻለና ፈጣን አገልግሎት ለመስጠት እንደሚያስችላቸው ገልጸዋል።

"በእውቀት ሽግግር መድረክ ላይ ብዙ ትምህርት ማግኘት ይቻላል" ያሉት አቶ ሚካኤል፤ ከመድረኩ ያገኙትን በስራቸው ላይ ተግባራዊ እያደረጉት መሆኑን ነግረውናል፡፡ በቡድን መስራት ያለውን ጥቅም በተመለከተ ካገኙት ተሞክሮ በመነሳትም ከሚመሯቸው የቡድን አባላት ጋር ስራዎችን ተግባብተው እየሰሩ እንደሚገኙ፣ አብሮ መስራትና እውቀትን መለዋወጥ ውጤታማ እንደሚያደርግ እንዳስተማራቸውና ከባልደረቦቻቸው ሀሳብ ማዳመጥና የራሳቸውንም ሀሳብ ማካፈል የተሻለ የቡድን ሥራ እንዲሰሩ እንዳገዛቸው አብራርተዋል፡፡

ተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ባለፉት መቶ ዓመታት እንደነ የቀድሞው የኢፌዴሪ ፕሬዝዳንት ግርማ ወ/ጊዮርጊስ፣ ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ፣ ሀዲስ ዓለማየሁ እና የዓለም ሎሬት አፈወርቅ ተክሌ ያሉ የአገሪቱን የፖለቲካ፣ የጥበብና የሳይንስ ምሰሶዎችን ያፈራ እና በማፍራት ላይ ያለ አንጋፋ ተቋም ነው።

"የትምህርት ጉዞ በተለያየ ጊዜ የተለያዩ ደረጃዎች ማለፍ ይጠይቃል" ያሉት የኮሌጁ የቢዝነስ አሰልጣኝ እና የወርቃማው ሰኞ ሰብሳቢ አቶ ነገሰ ተፈረደኝ ናቸው፡፡ ወርቃማው ሰኞ ሰራተኞች ስራቸውን ከሰኞ እስከ ቅዳሜ ወደውት እንዲሰሩ፣ ሰልጣኞችም ትምህርታቸውን በደስታ እንዲማሩና ውጤታማ እንዲሆኑ መቀስቀሻና ማንቂያ መድረክ ነው፡፡ በመድረኩም የተለያዩ ትምህርቶች፣ ልምዶች፣ የህይወት ተሞክሮዎች ይተላለፉበታል፡፡

የተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ የወርቃማው ሰኞን ለየት የሚያደርገው ትልልቅ የስራ ዘርፍ ላይ ያሉ የቀድሞው የኮሌጁ ተማሪዎች በወር አንድ ጊዜ ልምዳቸውንና ተሞክሯቸውን ለሰልጣኞችና ለሰራተኞች ማካፈል መቻላቸው ነው ያሉት አቶ ነገሰ፤ ከእነዚህ የቀድሞው ተማሪዎች ውስጥ የህዳሴው ግድብ ዋና ተደራዳሪ ኤክስፐርት ኢንጅነር ጌድዮን አስፋው አንዱ ናቸው፡፡ በመድረኩም ሰፊና አስተማሪ የህይወትና የስራ ልምዳቸውን አጋርተዋል። ሌላኛው በቀድሞ የተፈሪ መኮንን ተማሪ፣ በገንዘብና በገቢዎች ሚኒስቴር ከፍተኛ ባለስልጣን፣ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት (UN) ዓለም አቀፍ አገልጋይ እንዲሁም በኡጋንዳና ቦትስዋና የሰሩት አንጋፋ ሰው አቶ ተድላ ተሾመ ናቸው። ለኮሌጁ ሰራተኞች በስራ ዘመናቸው ያጋጠሟቸውን እውነተኛ ታሪኮችም አካፍለዋል፡፡

በ2018 በጀት ዓመት በተከታታይ 45 ሰኞዎችን እና በአዲሱ በጀት ዓመት ደግሞ ይህ መረጃ እስከተጠናቀረበት ድረስ ለ8ኛ ጊዜ የተለያዩ ርዕሶችን ይዘው በሚቀርቡ አንጋፋ ሰራተኞች እና እንግዶች የእውቀት ሽግግር መደረጉን የገለጹት አቶ ነገሰ፤ የሳምንቱ መጀመሪያ ቀን ሰራተኞች የእውቀትና ልምድ ሽግግር ማድረጋቸው በርካታ ጥቅሞች አሉት። ጠቃሚ ልምዶችንና መረጃዎችን በመለዋወጥ ሰራተኞች ሳምንቱን ግልጽ በሆነ ዕቅድና ትኩረት እንዲጀምሩ ያደርጋቸዋል።

አቅራቢዎቹ ፈተናዎችን እንዴት እንደተሻገሩና አሁን ያለው ማህበረሰብ እንዴት ማለፍ እንዳለበት ልምዳቸውን ያካፍላሉ፡፡ ይህም አንዱ ሰራተኛ ከዚህ ቀደም ያጋጠመውን ችግርና የፈታበትን መንገድ ለሌሎች ሲያካፍል ሌሎች ተመሳሳይ ስህተት እንዳይሠሩና ጊዜ እንዳያባክኑ ይረዳል።

ሌላኛው የወርቃማው ሰኞ ፋይዳ በጋራ የመስራት ባህልን ያሳድጋል። ሰራተኞች ዕርስ በዕርስ የሚማማሩበት መድረክ መኖሩ በቡድኑ መካከል ጠንካራ ግንኙነት፣ መከባበርና ግልጽነት እንዲፈጠር ያደርጋል። አዳዲስ እውቀትን ያስገኛል፡፡ ልምድ ያላቸው ሰራተኞች እውቀታቸውን ለአዳዲስ ሰራተኞች ሲያስተላልፉ ሰራተኞች አዳዲስ ክህሎቶችንና መረጃዎችን እንዲቀስሙ በመርዳት በራስ መተማመናቸውንና የሥራ ተነሳሽነታቸውን ያሳድጋል። አንዱ የአንዱን ተሞክሮ በመውሰድ በህይወቱ ተግባራዊ እንዲያደርገው ይረዳዋል። በአጠቃላይ ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና የቴክኖሎጂ እውቀትን ጭምር የሚያስገኝ ነው፡፡ ይህንንም ራሳቸውን በምሳሌነት በመጥቀስ አቶ ነገሰ ነግረውናል፡፡

በአጠቃላይ በኮሌጁ በየደረጃው የሚገኙ አመራሮችና ሰራተኞች ከአንድ ዓመት በላይ በተደረገው የእውቀት ሽግግር መላው የቢሮው ማህበረሰብ ዕርስ በዕርስ የተደጋገፈበት፣ ሰፊ ዕውቀት የተገኘበት እና መሰል ተቋማዊ ባህሎችን በመውሰድ ስራ ላይ እየዋለ ያለበት ነውም ብለዋል፡፡

## ከሚመሰረተው ... ከገጽ 6 የዞረ

ሁለቱም ኢኮኖሚውን እየፈተኑ ይገኛሉ። እነዚህን ችግሮች ለመፍታት በጥናት የተመሰረተ ኢንቨስትመንት በኢኮኖሚው ላይ እንዲካሄድ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ከሚመሰረተው መንግስት ይጠበቃል። ኢንቨስትመንት ሲያድግ፣ ምርት እና ምርታማነት እንዲሁም አቅርቦት ይጨምራል፤ በተቃራኒው የዋጋ ግሽበት ይቀንሳል፡፡ የዋጋ ግሽበትን ለመቀነስ በጥናት ላይ የተመሰረተ መፍትሔ ማምጣትም እንዲሁ ከሚመሰረተው መንግስት ይጠበቃል፡፡

በጥናትም "በኢኮኖሚ ግሽበት እንዲመጣ ያደረገው ማነው? የገንዘብ ስርጭት አሊያም ሌላ ከሆነ እርምጃ መወሰድ እንደሚገባ" ሞላ (ዶ/ር) ያነሳሉ፡፡ የውጭ ምንዛሪ ገበያውን በደንብ መከታተል፣ በብር እና በዶላር ምንዛሪ መካከል ያለውን አቅርቦትና ፍላጎት ማጥበብ ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም የውጪ ንግድን ማጠናከርና ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ መተካት ላይ በደንብ መስራት ይገባል። የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲው የተረጋጋ መሆን ለአንድ ሀገር የኢኮኖሚ እድገት ወሳኝ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ የስራ ዕድል ፈጠራ፣ የዋጋ ግሽበት፣ የወጪ ገቢ ንግድ ሚዛን ላይ ያለውን አፈጻጸም፣ ገበያውን በየጊዜው መገምገምና የእርምት እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም የሚመሰረተው መንግስት ጠንካራ የሆነ የማይክሮ ኢኮኖሚ ባለሙያዎች ቡድን ሊኖረው እንደሚገባም አብራርተዋል፡፡

መንግስት ያቀዳቸውን ስራዎችን ለማከናወን ሀብትና በጀት እንደሚያስፈልገው ያነሱት ከፍተኛ ተመራማሪው ሞላ (ዶ/ር)፣ ለዚህም የሰው ሀይልን በአግባቡ መጠቀም ያስፈልጋል። ከታክስና ከተለያዩ መንገዶች ገቢን ለማሳደግ የተጀመሩ ስራዎችንና አማራጮችን ማስፋት ተገቢነት አለው። ከሁለት እና ሶስት ዓመታት ወዲህ የታክስ አማራጮችን ለማስፋት የሚደረገው ጥረት አበረታች ነው፡፡ የሚገኘውን ሀብት ብክነትን በመቀነስ፣ ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ጉዳዮች ቅድሚያ በመስጠት፣ በአግባቡ ስራ ላይ በማዋል የተሻለ የኢኮኖሚ እድገት ማምጣት እንደሚቻል ተናግረዋል፡፡

ከፍተኛ ተመራማሪው ሞላ (ዶ/ር) እንደሚገልጹት፣ በኢትዮጵያ እየተመዘገበ ያለውን የኢኮኖሚ እድገት ለማስቀጠል በሀገር በቀል የኢኮኖሚ እድገት ማሻሻያ ፖሊሲ ትግበራ የተገኙ እምርታዎችን አጠናክሮ ማስቀጠል ይገባል፡፡ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ በመተካት፣ የወጪ ንግድን በማሳደግ በተለይ በ"ኢትዮጵያ ታምርት" ንቅናቄ ተጨባጭ ውጤት ማምጣት ተችሏል። የተገኙ ውጤቶችን ከዚህም በላይ ለማሳደግ ጠንካራ ስትራቴጂ በመንደፍ መስራት ያስፈልጋል፡፡ በሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፖሊሲ የተነደፉ የኢኮኖሚ ማሻሻያዎችን በአግባቡ በመተግበር የተሻለ የኢኮኖሚ እድገት ማምጣት ይቻላል፡፡

## አዲስ ... ከገጽ 9 የዞረ

ወረዳዎች፣ ክፍለ ከተሞችና የዘርፍ ተቋማትን ለማገናኘት ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር እየተሠራ ይገኛል። በአሁኑ ወቅት የመሠረተ ልማት ዝርጋታው ተጠናቆ በሙከራ ደረጃ ላይ ይገኛል።

የሳይበር ሴኪዩሪቲ ዳይሬክተሩ አቶ ዮናስ እንደሚገልጹት፤ ይህ ቴክኖሎጂ የከተማ አስተዳደሩ ተቋማት የማይቋረጥና ከፍተኛ አቅም ያለው የኔትዎርክ ሥርዓት እንዲኖራቸው ያደርጋል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ መረጃዎችን በዘመናዊ መንገድ ለማከማቸትና ለማስተዳደር የሚያስችል የክላውድ ዳታ ማዕከል (Data Cloud Center) አስፈላጊ በመሆኑ፣ አዲስ አበባ የራሷ የዳታ ማዕከል እንዲኖራት በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል።

ይህም ለከተማዋ የመንግሥት ተቋማት ብቻ ሳይሆን ለግሉ ዘርፍም የሰርቨር፣ የመረጃ ማከማቻ እና የኔትዎርክ እጥረቶችን ይቀርፋል። በተጨማሪም አገልግሎቶችን ዲጂታላይዝ ለማድረግና የኃይል እንዲሁም የሥርዓት (System) መቋረጥ ችግሮችን ለመፍታት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው አቶ ዮናስ አብራርተዋል።

ለዲጂታል ኢትዮጵያ 2030 ስኬት ሌላው ወሳኝ ጉዳይ የህብረተሰቡን የቴክኖሎጂ አጠቃቀም እውቀት ማሳደግ ሲሆን፣ ይህም በከተማዋ የ'ስማርት ሲቲ' ስትራቴጂካዊ እቅድ ውስጥ ተካትቷል፡፡ የስትራቴጂው ዋና ዓላማ ዜጎች ከቴክኖሎጂ ተጠቃሚነት አልፈው ወደ ቴክኖሎጂ ፈጣሪነት እንዲሸጋገሩ ማስቻል ነው፡፡ ለዚህም በ5 ሚሊዮን ኮደሮች ንቅናቄ ወጣቶችና ህብረተሰቡ በስፋት እንዲሳተፉ በማድረግ የዲጂታል ክህሎታቸውን ማሳደግ እንዲሁም ለተቋማት የተለያዩ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን በመስጠት ቴክኖሎጂ መፍጠር የሚችል ዜጋ ለመቅረፅ እየተሰራ ይገኛል፡

አቶ ዮናስ እንደገለጹት፣ ባለንበት ዘመን የዲጂታል ቴክኖሎጂን መጠቀም አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- አንድ ሰው የተሽከርካሪ ዓመታዊ የቴክኒክ ምርመራ (ቦሎ) ለማደስ ቢፈልግ፣ እንደ ድሮው ቢሆን የመኪናው ፋይል ወደሚገኝበት የአቃቂ ቃሊቲ አሽከርካሪና ተሽከርካሪ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ድረስ መሄድ ይኖርበታል። አገልግሎቱ በቴክኖሎጂ ያልተደገፈ በመሆኑም ረጅም ሰዓት በሰልፍ ለመጠበቅ ይገደድ ነበር፡፡ በአሁኑ ወቅት ግን ተገልጋዮች በፈለጉበትና በአቅራቢያቸው በሚገኝ የአዲስ መሶብ ዲጂታል የአንድ ማዕከል አገልግሎት ማግኘት የሚችሉበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ ይህም ጊዜንና ወጪን በከፍተኛ ደረጃ ይቆጥባል፡፡

ሰዎች ባሉበት ቦታ ወይም በአቅራቢያቸው ያለምንም እንግልት አገልግሎቱን በፍጥነት ማግኘታቸው ምርታማነትን ይጨምራል፡፡ በተጨማሪም አገልግሎቱ ከአሰራር ብልሹነት የጸዳና ቀልጣፋ መሆኑ በመንግሥትና በሕዝብ መካከል ያለውን እምነት ያጠናክራል፡፡

አቶ ዮናስ እንደገለፁት፣ የ"ዲጂታል ኢትዮጵያ 2030" ስትራቴጂን በመተግበር አዲስ አበባ አገልግሎቶቿን በጥራትና በተጠያቂነት ስሜት በመስጠት ለነዋሪዎቿና ለጎብኚዎቿ የተመቸች እና ሰው ተኮር ከተማ እንድትሆን እየተሠራ ይገኛል፡፡

## የባህል ... ከገጽ 12 የዞረ

ወራት በሙሉ ሃይሉ እንደሚሰራ፣ በስሩ ከሚያሰራቸው ሰራተኞች በተጨማሪ ለእነዚህ በዓላት በጊዜያዊነት ረዳት ዲዛይነሮችን ቀጥሮ እንደሚያሰራ አጫውቶናል፡፡ ከምንም በላይ ወጣቶች የባህል ልብሳቸውን በኩራት ለብሰው በአደባባይ መታየታቸው ከኢኮኖሚያዊ ፋይዳው ባለፈ ትልቅ ሀገራዊ ጠቀሜታም እንዳለው ተናግሯል፡፡

ኢሬቻ እና መስል የአደባባይ በዓላት ለሀገር የሚሰጡት አበርክቶ በጣም ሰፊ መሆኑን የጠቆሙት የቱሪዝም መምህሩና ተመራማሪው አያሌው ሲሳይ (ዶ/ር)፤ ከአደባባይ በዓላት ጋር በተያያዘ አዲስ አበባ ከሁሉም የኢትዮጵያ ከተሞች የተሻለ የመጠቀም እድል እንዳላት አንስተዋል፡፡ እሳቸው እንደሚሉት፤ አዲስ አበባ ፈጣን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ያለባት ከተማ ናት፡፡ የአደባባይ በዓላቱ ደግሞ ይህንን ኢኮኖሚያዊ ዕድሏን የበለጠ ያሰፋላታል። በዓላቱን ለማክበርና ለመታደም ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሰው ከሀገር ውስጥም ከውጪም ወደ ከተማዋ ይመጣሉ፡፡ እነዚህ ደግሞ ከባሕላዊ አልባሳት ጀምሮ የተለያዩ አገልግሎቶችን እና ሸቀጦችን በብዛት ይጠቀማሉ፡፡ ነጋዴውና የከተማው ነዋሪ እነዚህን ምርት እና አገልግሎቶች በጥራትና በብዛት በማቅረብ ተጠቃሚ እንደሚሆን ባለፉት ዓመታት ያየናቸው ውጤቶች ምስክር ናቸው፡፡ ስለዚህ የበዓሉ ታዳሚዎች በበዓሉ ላይ ደምቀውና ተውበው ከሚቀርቡባቸው አልባሳት፣ መዋቢያና ማጌጫ ቁሳቁሶች በተጨማሪ፣ በዕለቱ የሚፈልጓቸው አገልግሎቶች እና ሸቀጦች በብዛት ስለሚኖሩ፤ ይህንን ታሳቢ ያደረገ ዝግጅት ማድረግ እንዳለባቸው መክረዋል፡፡

የኢሬቻ በዓል በአልባሳት ግብይትም ሆነ ሌሎች የምርት እና አገልግሎት አቅርቦት ጋር በተያያዘ የሚፈጥረውን ኢኮኖሚ በአግባቡ ለመጠቀም እየታየ ያለው ጅምር አበረታች መሆኑን ነጋዴዎች እና ምሁራን ያረጋግጣሉ፡፡ ይሁን እንጂ ጅምሩን የበለጠ ውጤታማ ከማድረግ አንጻር ብዙ ሥራዎች እንደሚጠበቁ ይስማማሉ፡፡ በኢሬቻ እና ሌሎች የአደባባይ በዓላት ወቅት ከፍተኛ ፍላጎት የሚታይባቸው የባሕል አልባሳት ጊዜውን ባገናዘበ መልኩ ባህላዊውን አሠራር ከዘመናዊ የፋሽን ዲዛይን (Modern/Casual Wear) ጋር በማዋሃድ አዳዲስ የልብስ ስታይሎች የሚቀርቡበትን ሁኔታ መፍጠር ይገባል፡፡ ይህ በሀገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ የአልባሳት ኢንዱስትሪና ግብይት ውስጥ ዘልቆ እንዲገባ አቅዶ መሥራት እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡

የባህልና ሰላም ተመራማሪ ወሰን ባዩ (ዶ/ር) በበኩላቸው፣ የባህል አልባሳት የማንነት አንዱ መገለጫ ነው፡፡ እንደ ኢሬቻ ባሉ በዓላት ላይ የሚለበሱ አልባሳት ለዘመኑ ወጣት ፍላጎት እንዲመቹ ተደርገው ዲዛይን መደረጋቸው የባህል ዕሴቶች መሰረታቸውን ሳይለቁ ማዘመን እንደሚቻል ማሳያ ናቸው፡፡ ከአደባባይ በዓላት ባሻገር በሰርግና በመልስ ጊዜ ሳይቀር የባህል አልባሳት እየተመረጡ ናቸው፡፡ ይህም ሀገራዊ እውቀትና የግለሰቡ ጥረት ከተጣመሩ ብዙ ሀገራዊ ጉዳዮቻችንን ዘመኑን እንዲዋጁ ለማድረግ ጥሩ ማሳያ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ዲዛይነር ጸጋዬ እንዳጫወተን፣ ይህ በወጣቶች ዘንድ የታየው የባህል አልባሳት ፍላጎት መጨመር ለከተማዋ የባህል ልብስ ዲዛይነሮች እና አልባሳት አዘጋጆች ትልቅ የንግድ እድል ከፍቷል። ከበዓሉ ሳምንታት አስቀድሞ በዲዛይን መደብሮች እና በልብስ ስፌት ቤቶች ውስጥ የሚታየው ስራ የበዛበት እንቅስቃሴ የዘርፉን አቅም ያሳያል። ዲዛይነሮች የወጣቶችን ወቅታዊ ምርጫ ያገናዘቡ አዳዲስ የጥለት ዓይነቶችንና የልብስ ዲዛይኖችን በመፍጠር ደንበኞቻቸውን ይስባሉ። ይህም በዓሉ በየዓመቱ ሲመጣ ለዘርፉ ባለሙያዎች አስተማማኝ የሆነ የገቢ ምንጭ እንዲሆን አድርጎታል።

ከፍተኛውን ድርሻ የሚወስዱት ወጣቶች ባህሉን ከዘመናዊ የፋሽን ዘይቤ ጋር አዋህደው መልበሳቸው የባህል አልባሳትን ተፈላጊነት ያሳድጋል። ባህላዊ አልባሳት አልፎ አልፎ ለሚደረጉ ኩነቶች ብቻ የሚለበሱ ሳይሆኑ፣ በወጣቱ ትውልድ ዘንድ ተወደውና ዘመናዊ መልክ ይዘው እንዲቀጥሉ ያደርጋሉ። ይህ የወጣቶች ፍላጎት ዲዛይነሮች ፈጠራቸውን እንዲያሳድጉና ከባህላዊው አሰራር ወጥተው አዳዲስ አቀራረቦችን እንዲሞክሩ ትልቅ ብርታት ሆኗቸዋል።

በተጨማሪም የኢሬቻ በዓል የፈጠረው የባህል አልባሳት ፍላጎት በዲዛይነሮች ብቻ የተገደበ ሳይሆን፣ በአጠቃላይ የጨርቃ ጨርቅና በሕብረ ቀለማት የታጀቡ ጥለቶች ለሚያቀርቡ ዜጎች የራሱ አስተዋጽኦ ያደርጋል። ከዚህ አንጻር የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የዚህ የኢኮኖሚ እሴት ሰንሰለት ተጠቃሚ ይሆናሉ። ሀገር በቀል ጥበብና ቁሳቁስ ላይ የተመሰረተው ይህ እንቅስቃሴ የአካባቢውን ኢኮኖሚ ከማነቃቃቱም በላይ ለብዙ ወጣቶች ጊዜያዊና ቋሚ የስራ እድል በመፍጠር ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ አለው።

**የጠፋ ካርታ በጋዜጣ እንዲወጣ ስለመጠየቅ**

ከላይ በርዕሱ ለመግለጽ እንደተሞከረው የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት በ እመቤት አድሀኖም ስም የተመዘገበ ኮንዶሚንየም/ይዞታ መለያ ቁጥሩ AA00005120743351403013 የሆነና የተሰጠበት ቀን 25/05/2013 የሆነ የሙብት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት እንደጠፋባቸው በቁጥር 396/19 በቀን 07/01/2019 ዓ.ም የሚገልጽ ማስረጃ በማቅረብ አመልክተዋል፡፡ ይህም በጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣልኝ ሲሉ ያመለከቱ ስለሆነ ካርታውን አይቻለው ወይም ሙብት አለኝ የሚል በ 30 ቀናት ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅ/ጽ/ቤት ቀርቦ እንዲያሳውቅ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ምትክ ሰርተፍኬት የምንሰጥ መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ/ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ወ/ሮ/ወ/ሪት/አቶ/እነ/ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ወረዳ 08 ክልል ውስጥ በመሰረት አለማየሁ ደስታ በይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000070804072 በሴሪ ቁጥር L-0125901 የተመዘገበው የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለጠፋባቸው በማንኛውም መልኩ በእጁ ይገኛል የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው መቅረብ የሚችሉ መሆኑን እያሳወቅን ይህ ካልሆነ በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ ሙብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አመልካች በአራዳ ክፍለ ከተማ በቀድሞ ወረዳ 13 ቀበሌ 11 በአዲሱ ወረዳ 07 የቤት ቁጥር የለም ፪ አለቃ አባቴነህ ካሳ ስም የወጣው ቁጥሩ 5950 ሴሪ ቁጥር የለም የሆነ የይዞታ ማረጋገጫ ዋና ካርታ የጠፋባቸው በመሆኑ በምትኩ ካርታ ተዘጋጅቶ እንዲሰጣቸው 14/01/2019 በተፃፈ ማመልከቻ በመጠየቃቸው ጋዜጣ ማሳወጅ አስፈልጓል፡፡

በመሆኑም የጠየቁትን አገልግሎት ለመስጠት ያመቻ ዘንድ ከላይ በተጠቀሰው የተመዘገበውን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ይዤዋለሁ የሚል ማንኛውም አካል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ አራዳ ክ/ከ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ድረስ እንዲያቀርቡ እያሳወቀን ካልቀረቡ ግን የጠየቁትን አገልግሎት የምንሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአራዳ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ቅድስት ጥላሁን ተሾመ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ወረዳ 3 የይዞታ ልዩ መለያ AA00006100745509060I ሴሪ ቁጥር C 241638 ሴሪ ቁጥር የሆነው በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ/ ይዤዋለሁ የሚል ኣካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፍኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የቦሌ/ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ወ/ሮ/ወ/ት/አቶ/ ምስራቅ ብርሃኑ ካሳ ስም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ክ/ከተማ ወረዳ 02 የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ቁጥር AA000080203721 ሴሪ ቁጥር 0101886 የሆነው ይዞታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት (ካርታ) ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ በካርታ ቁጥር ለ/ከራ09/35/4/42744/052/13/00 ሴሪ ቁጥር 1675858 ሽታዬ ወርቁ ተሰማ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ቤት ማህደር ከለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በማህደር ክፍላችን ተፈልጎ ባለመገኘቱ ማህደራቸውን ተደራጅቶ በመመሪያ መሰረት ለማስተናገድ በሂደት ላይ ስለሆንን ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ተቃውሞውን እንዲያቀርቡ እያሳሰብን፣ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተቃውሞ የማያቀርቡ ከሆነ በምትኩ መመሪያው በሚፈቅደው መሰረት ተገቢውን ምላሽ የምንሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ ኃይሌ ክንፈ እና ሕይወት ጳውሎስ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 በካርታ ቁጥር ቦሌ12/92/7/6/266700/269765/01 ሴሪ ቁጥር 1659566 የሆነው የጋራ መኖሪያ ቤት በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ/ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

**የጠፋ ካርታ በጋዜጣ እንዲወጣ ስለማሳወቅ**

ከላይ በርዕሱ ለመግለፅ እንደተሞከረው የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ወረዳ 09 ወንድይፍራው ታረቀኝ ክፍሉ ስም የተመዘገበ ይዞታ የይዞታው ልዩ መለያ ቁጥር AA000050906834 የተሰጠበት ቀን 24/10/2018 ዓ/ም የሙብት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት እንደጠፋባቸው በቁጥር የካፖ/ለ/ቀ/15/812/18 በቀን 22/11/2018 ዓ.ም የሚገልፅ መረጃ በማቅረብ አመልክተዋል፡፡

ይህን በጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣልኝ ሲሉ ያመለከቱ ስለሆነ ካርታውን አይቻለው ወይም ሙብት አለኝ የሚል በ30 ቀናት ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ቀርቦ እንዲያሳውቅ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካቹ ምትክ ሰርተፍኬት የሚሰጥ መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ሽምሱ ጀማል አህመድ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በን/ስ/ላ/ክ/ከ/ወረዳ 1 የሚገኘው ካርታ /የይዞታ ልዩ መለያ/ቁጥር AA00008011561I ሴሪ ቁጥር 052674 በጽ/ቤታችን በስማቸው የተመዘገበ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት/ ካርታ/ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝታችሁ /ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የንፋስ ስልክ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አመልካች ወ/ሮ አድና ፍስሀ በቀን 14/1/2019 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ ባመለከቱት በካርታ ቁጥር የካርታ ቁጥር ቦሌ10-1/96/3/10/30070/00 የሴሪ ቁጥር 068809 ወረዳ 10 የቤቱ ስፋት 60.45 ሜ.ካ የቤቱ ቁጥር B2-F-17 የሆነው ካርታ በእኛ ተቋም የተሰጠ መሆኑ ይታወቃል፡፡

ይሁንና ከላይ የተጠቀሰው ካርታ ጠፍቶብናል ብሎ ያመለከቱ ስለሆነ በዚህ ምክንያት ለ30 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግላቸው እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገላቸው በኋላ በመመሪያው መሰረት ካርታ የምናዘጋጅ መሆኑን እናሳውቃለን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኋላ ማህደሩን የምናደራጅ እና ሀላፊነት የማንወስድ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ጻሀይ ሀይሉ ገብረማርያም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 10 የሚገኘው የጋራ መኖሪያ ካርታ/የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000061007346449021б ሴሪ ቁጥር -C 086489 የሆነው በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ /የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት /ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ / ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፍኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ አዱኛ በቀለ ገብረህይወት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 03 የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA00006030069I ሴሪ ቁጥር L 0107059 የሆነው በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት/ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ/ይዤዋለሁ የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፍኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08 ሰንሻይን ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የሆነው ይዞታ በካርታ ቁጥር ቦሌ8/54/9/4/48292/00 ሴሪ ቁጥር 121306 ስም የሚገኘው ይዞታ ማረጋገጫ የቤት ባለቤትነት ካርታ ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ/ ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፍኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአመልካች ኪሩቤል ደስታ በቀን 20/1/2019 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ ባመለከቱት በካርታ ቁጥር ለ/ኩራ 03/10/4/11909/029/4/00 የሴሪ ቁጥር 0256387 ወረዳ 03 የቤቱ ስፋት 200 ካ.ሜ የቤቱ ቁጥር አዲስ የሆነው ካርታ መጥፋቱ ተገልጾ ለፖሊስ እንዲጻፍልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

ይሁንና ከላይ የተጠቀሰው ካርታ ጠፍቶብናል ብሎ ያመለከቱ ስለሆነ በዚህ ምክንያት ለ30 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግላቸው እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገላቸው በኋላ በመመሪያው መሰረት ካርታ የምናዘጋጅ መሆኑን እናሳውቃለን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኋላ ማህደሩን የምናደራጅ እና ሀላፊነት የማንወስድ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ ኃይሌ ክንፈ እና ሕይወት ጳውሎስ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 በካርታ ቁጥር ቦሌ12/92/7/13/266700/269701/01 ሴሪ ቁጥር 1659564 የሆነው የጋራ መኖሪያ ቤት በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ/ይዤዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የቦሌ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

## በልደታ ክ/ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት የልደታ ሰላም አንደኛ እና መካ/ደረጃ ት/ቤት

## ግልጽ የጨረታ ማስታወቅያ

**ግዥ መለያ ቁጥር 001/2019 ዓ.ም**

በልደታ ክ/ከተማ በወረዳ 1 ስር የሚገኘው የልደታ ሠላም የመ/ደ/ት/ቤት በ2019 ዓ.ም በጀት ዓመት የሚፈልጋቸውን፡-

ሎት 1. የደንብ =ልብስ የጨረታ ማስከበሪያ 10,000.00

ሎት 2. ለአላቂ የቢሮ ዕቃዎች የጨረታ ማስከበሪያ 5,000.00

ሎት 3. ለህትመት የጨረታ ማስከበሪያ 818.00

ሎት 4. አላቂ የዕክምና ዕቃዎች የጨረታ ማስከበሪያ 300.00

ሎት 5. አላቂ የትምህርት ዕቃዎች የጨረታ ማስከበሪያ 7,000.00

ሎት 6. ለሌሎች አላቂ ዕቃዎችና አቅርቦቶች የጨረታ ማስከበሪያ 10,000.00

ሎት 7. ልዩ ልዩ መሳሪያዎች የጨረታ ማስከበሪያ 3,000.00

ሎት 8. ለፕላንት ማሽነሪና መሳሪያዎች ጥገና ማስከበሪያ 1,500.00

ሎት 9. ለህንፃ ለቁሳቁሰ እና ለተገጣጣሚዎች ዕድሳት ጥገና 1,500.00

ሎት 10. ለፕላንት ማሽነሪና እና መሳሪያዎች መግዣ 10,000.00

ሎት 11. ለህንፃ ለቁሳቁስ ለተገጣጣሚዎች መግዣ 4000.00

ሎት 12. ልዩ ልዩ ክፍያዎች 3097.00

መስሪያ ቤቱ ባወጣው ግልፅ ጫረታ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያማሉ ተጫርኞች መወዳደር ይችላሉ፡፤

1. በጨረታው ለመወዳደር ፍላጎት ላላቸው ተጫራቾች የታደሰ የንግድ ፍቃድ ያላቸው የዘመኑን ግብር የከፈሉ በመንግስት ግ/ን/አስ/ኤጀንሲ ድረ ገጽ በአቅራቢዎች ምዝገባ ዝርዝር የተመዘገቡ የቲንና የቫት ተመዝጋቢ የሆኑና የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ፡፡
2. የተጫራቾች የጨረታ ማስከበርያ በባንክ የተረጋገጠ ቼክ /ሲፒኦ/ ከጨረታ ሰነዶቻቸው ጋር አያይዘው ማቅረብ አለባቸው
3. የጨረታ አሸናፊ 10% የጨረታ ዋስትና ማስያዝ ይኖርበታል፡፡
4. ተጫራቾች በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ከወጣበት ዕለት አንስቶ በተከታታይ አስር የስራ ቀናት የማይመለስ ብር 200.00 (ሁለት መቶ ብር ብቻ) በልደታ ሠላም አንደኛ እና መካ/ደ/ት/ቤት በቢሮ ቁጥር 15 በመምጣት የጨረታ ሰነድን መግዛት ይቻላል፡፡
5. ተጫራቾች የመጫረቻ ሰነዶቻቸውን በታሸገ ኤንቨሎፕ ማስታወቅያው ከወጣበት ዕለት ጀምሮ በተከታታይ 10 የሥራ ቀናት በልደታ ሠላም አንደኛ እና መካ/ደ/ት/ቤት ቢሮ ቁጥር 15 ለጨረታ በተዘጋጀው ሣጥን ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
6. ጨረታውን ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በ10ኛው ቀን ታሽጎ በማግስቱ (በ11ኛው) ቀን ከቀኑ 4፡00 ሰዓት በልደታ ሠላም አንደኛ እና መካ/ደ/ት/ቤት በቢሮ ቁጥር 15 ይከፈታል። የመክፈቻው ቀን ቅዳሜና እሁድ (የበዓል ቀን) ከሆነ በሚቀጥለው የሥራ ቀን በተመሣሣይ ሰዓት ታሽጎ በማግሰቱ ይከፈታል፡፡
7. ተጫራቾች የጨረታ ሣጥኑን ከመከፈቱ በፊት የተወዳደሩባቸውን ሎት1፣ ሎት2፣ ሎት3፣ ሎት4፣ ሎት5፣ ሎት6፣ ሎት7፣ ሎት9፣ ሎት10፣ ሎት11 ናሙና ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
8. ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው ባይገኙም ት/ቤቱ ጨረታውን የመክፈት መብቱ የተጠበቀ ነው።
9. ተጫራቾች የሚወዳደሩባቸውን ዕቃዎች ለእያንዳንዱ ከቫት ጋር ያለውን ዋጋ ማስቀመጥ ይኖርባቸዋል።
10. የዘገየ ጨረታና በጨረታ መክፈቻ ላይ ያልተነበበ ጨረታ ተቀባይነት የለውም፡፡
11. አሸናፊ ተጫራቾች ያሸነፉቸውን ዕቃዎች በራሣቸው ትራንስፖርት ግዥ ፈፃሚው መሥሪያ ቤት ድረስ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
12. መሥሪያ ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
13. ት/ቤቱ ዕቃዎችን 20% የመቀነስ 20% የመጨመር መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**አድራሻ፡-** አዲሱ ደሴ ሆቴል በተሠራው መንገድ ወረድ ብሎ ልደታ ፀበል አካባቢ ነው፡፡

ስልክ 0113690439 / 0113692257

**በልደታ ክ/ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት የልደታ ሰላም አንደኛ እና መካ/ደረጃ ት/ቤት**

## ግልጽ የጨረታ ማስታወቅያ

## የጨረታ መለያ ቁጥር 001/2019 ዓ.ም

በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ አንድ መስከረም አንድ ቅድመ አንደኛ፤ አንደኛና መካከለኛ ደ/ት/ቤት ለ2019 በጀት አመት ለመማር ማስተማር አገልግሎት የሚያስፈልጉ

ሎት 1. አላቂ የቢሮ ዕቃዎች የጨረታ ማስከበሪያ ብር 30011

ሎት 2. አላቂ የፅዳት ዕቃዎች የጨረታ ማስከበሪያ ብር 10000

ሎት 3. የደንብ ልብስና ጫማ የጨረታ ማስከበሪያ ብር 23823.4

ሎት 4. የደንብ ልብስ ስፌት የጨረታ ማስከበሪያ ብር 5000

ሎት 5. ለህትመት የጨረታ ማስከበሪያ ብር 5000

ሎት 6. ቋሚ ዕቃዎች ፈርኒቸር የጨረታ ማስከበሪያ ብር 15000

ሎት 7. የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች የጨረታ ማስከበሪያ ብር 15000

ሎት 8. የሻይ ቡና የጨረታ ማስከበሪያ ብር ያስገቡትን ዋጋ 2%

ሎት 9. የኤሌክትሮኒክስ ጥገና የጨረታ ማስከበሪያ ብር ያስገቡትን ዋጋ 2%

ሎት 10. የጥገናና ዕድሳት የጨረታ ማስከበሪያ ብር ያስገቡትን ዋጋ 2%

ብቃት ያላቸውን በመስኩ የተሰማሩ ተጫራቾችን አወዳድሮ ግዥ መፈፀም ይፈልጋል፡፡

**በዚህም መሰረት**

1. በጨረታው ለመወዳደር ፍላጎት ያላቸው ተጫራቾች የታዳሰ ንግድ ፍቃድ ያላቸው፤ የዘመኑን ግብር የከፈሉ፤ በመንግስት ግ/ን/አ/ኤጀንሲ ድህረ ገጽ ላይ በአቅራቢዎች ምዝገባ ዝርዝር የተመዘገቡ፤ የቲንነምበር ያላቸው፤ ቫት ተመዝጋቢ የሆኑና የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ
2. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ በባንክ የተረጋገጠ /ሲ.ፒ.ኦ/ ከጨረታው ሰነድ ጋር አያይዘው ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
3. ተጫራቾች ጨረታው በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ከወጣበት እለት አንስቶ ባሉት 10 ተከታታይ የስራ ቀናት የማይመለስ ብር 200 (ሁለት መቶ ብር) ለእየአንዳንዱ ሎት በመክፈል መስከረም አንድ ቅድመ አንደኛ፤ አንደኛና መካከለኛ ደ/ት/ቤት ቢሮ ቁጥር 5 በመምጣት የጨረታ ሰነዱን መግዛት ይችላሉ፡፡
4. ተጫራቾች የመጫረቻ ሰነዳቸውን በታሸገ ኤንቨሎፕ ማስታወቂያው ከወጣበት እለት አንስቶ ለተከታታይ 10 የስራ ቀናት መስከረም አንድ ቅድመ አንደኛ፤ አንደኛና መካከለኛ ደ/ት/ቤት ግዢ ክፍል ለጨረታ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ኦሪጅናልና ኮፒ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
5. ጨረታው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በአስረኛው ቀን በ11፡00 ሰዓት ታሽጎ በማግስቱ ከቀኑ 4፡30 በት/ቤቱ የተማሪዎች መመገቢያ አዳራሽ ይከፈታል፡፡ የመክፈቻ ቀኑ ቅዳሜና እሁድ ወይም የበአል ቀን ከሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን በተጠቀሰው ሰዓት ይከፈታል፡፡
6. ተጫራቾች የጨረታ ሳጥን ከመከፈቱ በፊት ለተወዳደሩባቸው ዕቃዎች ናሙና ለተጠየቀባቸው ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
7. ተጫራቾች የሚወዳደሩባቸውን ዕቃዎች ለእያንዳንዱ ከቫት ጋር ያለውን ዋጋ ማስቀመጥ ይኖርባቸዋል።
8. የዘገየ ጨረታና በጨረታ መክፈቻ ላይ ያልተነበበ ጨረታ ተቀባይት ለውም፡፡
9. አሸናፊ ተጫራቾች ያሸነፉባቸውን ዕቃዎች በራሳቸው ትራንስፖርት ግዥ ፈፃሚው መስሪያ ቤት ድረስ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
10. ለጨረታ ከቀረቡት ዕቃዎች ዝርዝር ውስጥ ት/ቤቱ እስከ 20% ጨምሮ ወይም ቀንሶ የመግዛት መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው ፡፡
11. መስሪያ ቤቱ የተሸለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።

**ለበለጠ ማብራሪያ**

- መስከረም አንድ ቅድመ አንደኛ፤ አንደኛና መካከለኛ ደ/ት/ቤት
- ስልክ ቁጥር 0115577296 /0115579044
- አድራሻ፡- ልደታ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፊት ለፊት ገባ ብሎ

**በል/ክ/ከ/ት/ጽ/ቤት የመስከረም አንድ ቅድመ አንደኛ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት**

በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ በቀድሞ--- ቀበሌ --- በአዲሱ ወረዳ 07 የቤት ቁጥር --- በካርታ ቁጥር 9840/25676/27373/20422/03 በአቶ/ወ/ሮ/እነ ሙላቷ ባልቻ ስም ተመዝግቦ ተሰጥቶ የነበረ ካርታ የጠፋ ስለሆነ በማንኛውም ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል አካል ማስታወቂያው በጋዜጣ ከወጣበት እስከ 20 ቀን ድረስ ለንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ድረስ በመቅረብ አቤቱታ እንዲቀርብ፡፡ ይዤዋለሁ የሚል ከሌለ ተለዋጭ ሌላ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የን/ስ/ላ/ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

# የጽናት ተምሳሌትነት




ፎቶ- ከፋይል

አትሌት ትዕግስት አሰፋ በበርሊን ከተማ በተካሄደው የማራቶን ውድድር የደረሰባትን ጉዳት ተቋቁማ ለሶስተኛ ጊዜ አሸናፊ በመሆን ታሪካዊ ድል ባስመዘገበችበት ወቅት

**በሳህሉ ብርሃኑ**

የረጅም ርቀት ሩጫ ማለት ኢትዮጵያ፣ ኢትዮጵያ ማለት ደግሞ የረጅም ርቀት ሩጫ ሆኖ ለዓመታት ቆይቷል። ይህ ግንኙነት የተፈጠረው ደግሞ እንዲሁ በአጋጣሚ ሳይሆን በርካታ አትሌቶች በጽናትና በትጋት ሰርተው ባገኙት ድል ምክንያት ነው። የአትሌቲክስ ስኬት የኢትዮጵያውያን አንድነትና ተስፋ መገለጫ ሆኖ የቆየ ሲሆን፣ የአትሌቶች ድል ሲከበር፣ የሀገሪቱ ባንዲራ ከፍ ብሎ ሲውለበለብ፣ መላው ሕዝብ በአንድ ይቆማል። በተለይ የአንዳንድ የኢትዮጵያውያን አትሌቶች ድሎች የተገኙበት መንገድ ከስፖርታዊ ውጤታቸው ባሻገር ብዙ ቁም ነገር ገላጮች ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡

ሰሞኑን በተካሄደው የበርሊን ማራቶን ላይም ዓለም የተመለከተው ይህንኑ ሀቅ ነው፡፡ እንደ አትሌቲክስ ዊክሊ ዘገባ ኢትዮጵያዊቷ የማራቶን ሯጭ ትዕግስት አሰፋ በቀኝ እግሯ ጅማት ላይ በደረሰባት ከፊል የመቀደድ ጉዳት ውድድሩን ማቋረጥ እንደነበረባት ብዙዎች ይገልጻሉ። በመጨረሻዎቹ 200 ሜትር ገደማ ሰውነቷ "ይህ ነገር ይቅርብን፤ ይበቃል" እንዳላት ከፊት ገጽታዋ ላይ በግልጽ ማየት ይቻላል፡፡ ጀግኒት ግን አልፈቀደችም፡፡ እጅ ሊሰጥ ይታገላት የነበረው ሰውነቷን ለጀግናው አዕምሯዋ እጅ ሰጥቶ በድል አጠናቀቀች፡፡

አንጋፋው አሰልጣኝ ገመዱ ደደፎ እንደተናገሩት፣ የትዕግስት አሰፋ የቀኝ ጅማት (Achilles tendon) የማጠናቀቂያው መስመር 11 ኪሎ ሜትር ሲቀረው የማስጠንቀቂያ ምልክቶችን ማሳየት ጀምሮ ነበር። በተፈጥሮ የፅናት ስሜቷ እየተመራች፣ አዲስ የዓለም ክብረ ወሰን የማስመዝገብ ፍጥነቷን ለመጠበቅ ስትል ያንን አሰቃቂ ሕመም ውጣ ተወዳድራለች። ሆኖም ትልቁ አደጋ የደረሰው 40ኛ ኪሎ ሜትር ላይ ጅማቷ ሙሉ በሙሉ የተበጠሰ ሲሆን፣ ይህም የሰውነት ጥንካሬዋን ሙሉ በሙሉ ያደከመ ነበር።

ጀግናዋ አትሌት ትዕግስት በበርሊን ማራቶን አብዛኛውን ርቀት የዓለም ክብረ ወሰን (ከ2፡09፡56 በታች) ለመስበር በሚያስችል አስደናቂ ፍጥነት ስትመራ የነበረ ቢሆንም፣ ወደ ውድድሩ ማጠናቀቂያ አካባቢ በገጠማት ጉዳት ፍጥነቷ ቀንሶ ውድድሩን 2፡11፡04 በሆነ ጊዜ አጠናቃለች። አትሌት ትዕግስት አሰፋ በጀርመኗ መዲና በርሊን ከተማ በተካሄደው የማራቶን ውድድር የደረሰባትን የጉዳት ፈተና ተቋቁማ ለሶስተኛ ጊዜ አሸናፊ በመሆን ታሪካዊ ድል አስመዝግባለች።

ሆኖም ግን ውድድሩ ሊጠናቀቅ ሁለት ኪሎ ሜትር ብቻ ሲቀረው በ40ኛው ኪሎ ሜትር ላይ በገጠማት የጡንቻ ጉዳት ምክንያት ቀሪውን ርቀት በማነከስ ለማጠናቀቅ ተገድዳለች። አትሌቷ በጉዳት ውስጥ ሆናም ያሳየችው ድንቅ የጽናት መንፈስ ውድድሩን በ2 ሰዓት ከ11 ደቂቃ ከ04 ሰከንድ እንድታጠናቅቅ ያስቻላት ሲሆን፣ ይህም በሴቶች ማራቶን ታሪክ የዓለም 3ኛው ፈጣን ሰዓት ሆኖ ተመዝግቦላታል። የትዕግስት የጽናት አሸናፊነት በስፖርት አፍቃሪዎችና በመስኩ ባለሙያዎች ዘንድ ከፍተኛ አድናቆትን አትርፎላታል።

የአትሌቷ ማናጀር ጂያኒ ዴማዶና ለፑራ ቪዳ ስፖርትስ አፍሪካ እንደገለጹት፤ በአትሌቷ የቀኝ እግር ጅማት ላይ ጉዳት እንደደረሰ አረጋግጠው፣ ውድድሩን የጨረሰችበት ጽናትና ጀግንነት አስደናቂ ስለመሆኑ ይገልጻሉ፡፡ ትዕግስት አሰፋ በዓለም ማራቶን ታሪክ ታላቅ ስም ያላትና የዓለም ክብረ ወሰን ባለቤት ብትሆንም፣ በውድድር መድረክ ላይ ያሳለፈቻቸው አንዳንድ ሁነቶች በአትሌቲክስ አፍቃሪዎች ዘንድ እጅግ አሳዛኝና የኢትዮጵያዊነት ፅናት መገለጫ ተደርገው ይወሰዳሉ።

የሶስት ጊዜ የበርሊን ማራቶን ባለድሏ አትሌት ትዕግስት አሰፋ ከዚህ ቀደምም በገጠማት ከባድ የአቺሊስ ጅማት (Achilles tendon) ጉዳት ምክንያት "ከእንግዲህ በኋላ ወደ ስፖርቱ የመመለስ እድልሽ በጣም ጠባብ ነው፤ ሩጫ ማቆም አለብሽ" ተብላ ነበር። ይህ የሆነው እ.ኤ.አ በ2019 በቫሌንሺያ የግማሽ ማራቶን ውድድር ላይ በደረሰባት ከፍተኛ ጉዳት ወቅት ሲሆን፣ በስፔንና በኢጣሊያ ያሉ የሕክምና ባለሙያዎች ተስፋ አስቆራጭ ነገር ነግረዋት ነበር። ሆኖም ግን፣ እሷና አሰልጣኟ ተስፋ ሳይቆርጡ በጽናት በመታገላቸው ወደ ሩጫው በመመለስ አስደናቂ የድል ታሪኮችን አስመዝግባለች። በ2023 የበርሊን ማራቶንን በ2 ሰዓት ከ11 ደቂቃ ከ53 ሰከንድ በማጠናቀቅ በወቅቱ የዓለም ክብረ ወሰንን በብቃት ሰብራለች። በ2026 የለንደን ማራቶንን በበላይነት አሸንፋለች፤ እንዲሁም በ2024 የፓሪስ ኦሎምፒክ ለሀገሯ የብር ሜዳሊያ አስገኝታለች።

> የስፖርት ድል ትልቁ ምሰሶ አካላዊ ብቃት ብቻ ሳይሆን የማይበገረው የአዕምሮ እና የልብ ጥንካሬ ጭምር ነው

እንደዚህ ያሉ እምባ በዓይን፣ ልብን በኩራት የሚሞሉ ታሪኮችን ከኢትዮጵያ የአትሌቲክስ ታሪክ መዝገብ ላይ እንደልብ መግለጥ ይቻላል፡፡ በስፖርቱ ዓለም እንደ ትዕግስት አሰፋ ሁሉ ከባድ የጤና እክልን፣ አሰቃቂ ህመምን እና ተስፋ አስቆራጭ የዶክተሮችን የጤና ሁኔታ ትንበያ በጽናት አሸንፈው ታሪክ የሰሩ ድንቅ አትሌቶችም አሉ። የተወሰኑትን በማሳያነት እንጥቀስ።

የጀግናዋ አትሌት ደራርቱ ቱሉ የለንደንና የኒውዮርክ ማራቶን ተአምር ተጠቃሽ ነው፡፡ የኦሎምፒክ ሻምፒዮን ደራርቱ ቱሉ በረጅም ርቀት ሩጫ ላይ በተደጋጋሚ የጉልበትና የጡንቻ (Hamstring) ጉዳቶች ትሰቃይ ነበር። በተለይም ልጅ ከወለደች በኋላ ወደ ስፖርቱ መመለስ እንደማትችል ብዙዎች አስበው ነበር። ሁሉንም ክፉ ቀናት በትዕግስት አሳልፋ፣ በ2001 የለንደን ማራቶንን በአስደናቂ ብቃት አሸነፈች። ይበልጥ ዓለምን ያስገረመው ግን እ.ኤ.አ በ2009 የኒውዮርክ ማራቶን ላይ ሲሆን፣ በ37 ዓመቷ በዕድሜና በጉዳት ሳትበገር ታላላቅ ወጣት አትሌቶችን ቀድማ አንደኛ በመውጣት የጽናት ተምሳሌትነቷን አሳይታለች።

ለአንድ አፍታ በምናብ ወደ ኋላ ወደ አስገራሚው የሮም ድል መለስ ስንል በሻምበል አበበ ቢቂላ ልብ ውስጥ የነበረው ያልሸነፍ ባይነት ስሜት እናገኛለን፡፡ አበበ በሮም አስፋልት ላይ በባዶ እግሩ ሲሮጥ፣ የሚረግጠው ድንጋዩንና ትኩሱን አስፋልት ብቻ አልነበረም፤ "ጥቁር ህዝብ አይችልም" የሚለውን የዓለምን የተሳሳተ አመለካከት ጭምር እንጂ። የሮም ኦሎምፒክ ማራቶን ሊጀመር ጥቂት ደቂቃዎች ሲቀሩ፣ ዓለም አቀፍ ጋዜጠኞችና ታዛቢዎች በአንድ ነገር ግራ ተጋብተው ነበር። አንድ ቀጭን ኢትዮጵያዊ ሯጭ፣ በዘመናዊው ስፖርት ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ መልኩ ያለምንም ጫማ በመነሻ መስመር ላይ ቆሟል። ያኔ ብዙዎች አበበ ቢቂላን እንደ አንድ ሯጭ ብቻ ሳይሆን፣ 'ጫማ የሌለው ምስኪን አፍሪካዊ' አድርገው ነበር የቆጠሩት።

ይሁንና አበበ የሮምን አውራ ጎዳናዎች በባዶ እግሩ አቆራርጦ በቀዳሚነት ሲገባ፣ ዓለምን ያስገረመ ታሪክ ተሰራ። ታዋቂው የታሪክ ተመራማሪ ፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንክረስት፣ የአበበን ድል ከአክሱም ሐውልት መመለስ ጥያቄ ጋር አያይዘውት ነበር። ፓንክረስት፣ ድሉ ለኢትዮጵያውያን የሰጠውን የሞራል ልዕልና ሲገልጹ፣ "አበበ ቢቂላ በባዶ እግሩ መሮጡ፣ ኢትዮጵያ ካሏት ሀብቶች ይልቅ በውስጣዊ ወኔና በሰው ኃይል ማንኛውንም ተግዳሮት ማሸነፍ እንደምትችል ለዓለም ያስመሰከረበት ክስተት ነበር" ብለዋል።

ትውልደ ኢትዮጵያዊት ለኔዘርላንድስ የምትሮጠው ሲፋን ሐሰን የቶኪዮ ኦሎምፒክ (በ2021) አጋጣሚ ጠቅሰን ጽሑፋችንን እንቋጭ፡፡ በወቅቱ በ1 ሺህ 500 ሜትር ማጣሪያ ውድድር ላይ የመጨረሻው ዙር ሲጀምር በድንገት ተሰናክላ መሬት ላይ በከፍተኛ ሁኔታ ወደቀች። ውድድሩ ሊያልቅ ጥቂት ሜትሮች ብቻ ስለቀሩ ለማሸነፍ ቀርቶ ውድድሩን ለመጨረስ እንኳ የማይታሰብበት ቅጽበት ነበር። ሲፋን በድንገት ከመሬት ተነስታ በሚያስገርም ፍጥነት ከፊት የነበሩትን 11 አትሌቶች አንድ በአንድ በመቅደም ውድድሩን በአንደኝነት አጠናቀቀች፡፡ ይባስ ብሎም ያንን አካላዊ ስቃይ ተቋቁማ በዚያው ኦሎምፒክ የ5 ሺህ እና የ10 ሺህ ሜትር የወርቅ ሜዳሊያዎችን እንዲሁም የ1 ሺህ 500 ሜትር የነሐስ ሜዳሊያ በመውሰድ በኦሎምፒክ ታሪክ ታይቶ የማይታወቅ ታሪክ ሰራች።

የእነዚህ አትሌቶች ታሪክ እንደሚያስተምረን፣ የስፖርት ድል ትልቁ ምሰሶ አካላዊ ብቃት ብቻ ሳይሆን የማይበገረው የአዕምሮ እና የልብ ጥንካሬ ጭምር መሆኑን ነው። ልክ እንደ አትሌት ትዕግስት አሰፋ ሁሉ፣ እነ ደራርቱ ቱሉ፣ ኃይሌ ገብረስላሴና መሰል አትሌቶች የህመም ስቃይ፣ በተስፋ አስቆራጭ የህክምና ሁኔታ ትንበያዎች እና በድንገተኛ ውድቀቶች ውስጥ አልፈዋል። ሆኖም ግን፣ ተስፋ ከመቁረጥ ይልቅ ጽናትን፣ ከመሸነፍ ይልቅ ዳግም መነሳትን መርጠው በታሪክ የማይሻር አሻራቸውን አኑረዋል። ይህ አስገራሚ ታሪካቸው የሰው ልጅ ሊደረስበት የማይችል የሚመስለውን ማንኛውንም ከባድ ፈተና በጽናት እና በትጋት ማሸነፍ እንደሚችል ለዓለም ያሳየ ትልቅ ምስክርነት ነው።